አንዱን በግዢ አንዱን በስጦታ አግኝቷል። በ1947 ዓ.ም. ተጨማሪ ሳብ ሳፊር አይሮፕላኖችም ተገዝተዋል።

ለመጀመሪያ ጊዜ ከስዊድን የተላኩት ከፍተኛ መኰንን ጄኔራል ሆርድ የአየር ኃይል አዛዥነቱን ተረክበው ከ1946 ዓ. ም. ጀምሮ ማስተዳደር ሲጀምሩ፣ ቮን ሮዘን ደረጃ በደረጃ ኃላፊነታቸውን እያስረከቡ ብዙም ሳይቆዩ ለሁለተኛ ጊዜ ለተተኩት አዛዥ ጄኔራል ኒልሰን፣ ጨርሰው አስረክበው ወደ ስዊድን ተመልሰዋል። ከዚያም በናይጄሪያ የቢያፍራ የርስ በርስ ጦርነት አጋዥ ሆነው በትንሽ አይሮፕላን ቦንብ እየጣሉ ተዋግተዋል።

የናይጄሪያ ጦርነት በጃንሆይ አስታራቂነት (የአንድ ክፍለ ሀገር መገንጠል ያሰጋቸውም ስለነበር) አጄኩ ተወግደው ጄኔራል ገዋን በ1956 ዓ.ም በአሸናፊነት ናይጄሪያን አንድ አድርገው በፕሬዚዴንትነት አስተዳደሩ።



ጄኔራል ገዋን የኢትዮጵያ አየር መንገድ 25ኛ ዓመቱን ባከበረበት ዕለት የክብር እንግዳ በመሆን በሻምላቸው የተዘጋጀውን ኬክ ሲቆርሱ





# የቤተመንግሥት ጥሪ

(በአንድ ወቅት የተፈጸመ የእጩ መኰንኖች አቀጣጠር)

ጊዜው ሐምሌ 1941 ዓ. ም. ሲሆን ወራቱ ክረምት ስለሆነ ያካፋል። በሦስት የጦር ሠራዊት ካሚዮኖች ከሦስት ትምህርት ቤቶች፣ ማለትም ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ከተፈሪ መኮንንና ከጄኔራል ዊንጌት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመጡ ወደ 60 የሚሆኑ ተማሪዎች ቤተመንግሥት እንደደረሱ በሰልፍ ሆነው በእልፍኝ አስከልካዩ አማካኝነት ወደ ጃንሆይ ቢሮ ጽ/ቤት ገብተው እጅ እየነሱ ከጃንሆይ ፊት ቆሙ። በእሳት ማንደጃው የተማገደው እንጨት ክፍሉን አሙቆታል። ከንጉሠ ነገሥቱና ከማንደጃው ግራና ቀኝ መኳንንት ቆመዋል።

ጃንሆይ ንግግራቸውን የጀመሩት «ምንድነው ይህ ሤራ» ብለው በመቀለድ ነበረ። በመቀጠልም «እናንተ አሁን ልጆች ስለሆናችሁ ስለ አየር ኃይል ጥቅም አታውቁም። ምናልባት አሁን አየር ኃይላችን ትንሽ ስለሆነች ይሆናል እዚያ ለመግባትና ለመቀጠር የማትፈልጉት። ለወደፊት ከታሪክ እንደምትረዱት የእንግሊዝ ሮያል ኤይር ፎርስ የማልታን ደሴት በጀግንነት የተከላከሉት በሁለት አይሮፕላኖች ብቻ ነበር» አሉ።

ከዚያም ተማሪዎቹ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች አቀረቡ። ከተማሪዎቹ አንዱ ጌታሁን እጅጉ (አሁን ኰሎኔል) «እኔ መሐንዲስ መሆንና ቤተሰቦቼን መርዳት ነው የምፈልገው» ሲል ሌላው «ገበሬ መሆን ነው የምፈልገው» አለ። ጃንሆይም «መሐንዲስነት የሚፈልገው የአይሮፕላን መሐንዲስ መሆን ይችላል። የቤተሰብ ችግር ካለባችሁ በአሰፋ በኩል ይቅረብልንና ርዳታ ይደረግላችኋል። ማወቅ ያለባችሁ አገራችሁን ካልተከላከላችሁ መሬታችሁ ከተነጠቀ የት ሆናችሁ ነው የምታርሱት?» በማለት መሪ ቃል ተናግረው ተማሪዎቹን አሰናበቱ። ከዚህ በኋላ በእልፍኝ አስከልካዩ «እጅ ንሱ!» ተብለው ከጽሕፈት ቤቱ ወጥተው በመጡበት አኳኋን ወደ የትምህርት ቤታቸው ተመለሱ። ተማሪዎቹ መኪናው ላይ ከመሣፈራቸው በፊት ጄኔራል አሰፋ አየነ (በዚያ ጊዜ ሻለቃ) ሰብስበው ት/ቤቶቹ ለሦስት ወራት ተዘግተው እስከሚከፈቱ ወጣቶቹ አየር ኃይል እንዲቀጠሩ ለማበረታታትና ተጨማሪ ፍላጎት ለማሳደር ሳይሆን አይቀርም በትርፍ ጊዜያቸው በከተማው ውስጥ በዚያን ጊዜ ከታወቀው የወታደር ልብስ ሰፊ ኤድዋርድ ጋራቤዲያን ዘንድ እየሄዱ የገበርዲን ዩኒፎርም እንዲለኩ አዘዙ። አብዛኛው ተማሪ ሄዶ ተለክቷል። ከካኪ ደንብ ልብስ የወጣው ግን



ጀኔራል ጎዋን የኢትዮጵያ አየር መንገድ 25ኛ ዓመቱን ባከበረበት ዕለት የክብር እንግዳ በመሆን በሻምላቸው የተዘጋጀውን ኬክ ሲቆርሱ

ከአራት ዓመታት አገልግሎት በኋላ ነበር። የአየር ኃይል አስተማማኝ
መሠረት የተጣለውና የትምህርት በር የተከፈተው በኢትዮጵያ የአቪዬሽን
አባትና መሥራች የነበሩት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሰጡት ከላይ
በተጠቀሰው መሪ ቃል መሠረት ነበር። የዚህ መጽሐፍ ደራሲ የተቀጠ
ረውም በ3ኛው ኮርስ በጥቅምት 1942 ዓ.ም ነበረ።

## ሣፊሯ ብቻዋን አመለጠችው

እጩ መኮንን ንጉሤ ስሜ የአራተኛ ኮርስ ፓይለት ተማሪ ሆኖ
የመጀመሪያ የበረራ ተማሪ እንደሚያደርገው ሁሉ፣ አስተማሪው ከመም
ጣቱ በፊት በጥዋት ሞተሩን አሙቆና ፈትሾ ማዘጋጀት የዕለቱ ተቀዳሚ
ፕሮግራም ነበር። ሁለት፣ ሁለት ተማሪዎች ሆነው አንደኛው ከውስጥ
ፍሬን ይዞ ሲጠባበቅ ሁለተኛው ከውጭ የሚሠራውን መፈጸም የነበረ
ባቸውን ንጉሤ ተሽቀዳድሞ ለብቻው የሁለት ሰው ሥራ ለመሸፈን፣ ከአይ
ሮፕላኗ ውስጥ ገብቶ ፍሬን ከያዘና ከቆለፈው በኋላ ቤንዚኑን ተቆጣጥሮ
ውጪ በመውጣት ውልብልቢቷን ወደ ግራ ክብ ዞር፤ዞር ካደረገ በኋላ
ወደ ቀኝ አንዴ በኃይል ሲያዞር ሞተሯ ይነሳና ወደፊት መሽከርከር
ትጀምራለች። ክንፏን ዞሮ ወደ ማብረሪያ ኮክፒት ለመግባት ሲሞክር
ይወድቃል። ለመነሣት ሲሞክር የአይሮፕላኗ ጭራ ይመታውና እንደገና
ይወድቃል። አይሮፕላኗ ለብቻዋ ትሽከረከራለች፣ እሱ እየሮጠ ይከተ
ላታል። አንድ መካኒክ ሲያልፍ ለማቆም ክንፏን ለትንሽ ጊዜ ስለያዛት
አቅጣጫዋን ለውጣ ወደ ሜዳው ባትሄድ ኖሮ ፊት ለፊት ወዳለው ነዳጅ
ማደያ ሄዳ ትላተምና ከባድ አደጋ ያስከትል ነበር። ለብቻዋ የተሽከረ
ከረችው ፍሬኑ በተያዘበት ጊዜ መስመሩ ላይ በዘይት ፋንታ አየር ኖሮት
ቆልፎ ለመያዝ ሳይችል ቀርቶ ይሆናል። በመጨረሻ ሰዎች ተሯሩጠው
ግራና ቀኝ ክንፏን ይዘው ከተፈለገበት ቦታ አቆሟት።

## የቢ-17 አይሮፕላን አደጋ

ስለ ድሮው አይሮፕላን አደጋ አለፍ አለፍ እያልን በምናነሳበት ጊዜ
በወቅቱ በአጠቃላይ በአቪዬሽን መስክ የተሠማሩት ወጣቶች የነበራቸው
የኑሮ ደረጃ፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቴክኒክ ነክ የሆኑትን የቴክኖሎጂ
ውጤቶች በእጅ ይዞ ማገላበጥ ቀርቶ ለማየት እንኳን የነበረው ዕድል
የመነመነ የነበረበት ጊዜ መሆኑን አብሮ መመልከት ያስፈልጋል። በልዩ
ልዩ የአቪዬሽን መስኮች ከብዙ ዘመን አገልግሎት በኋላ በዚህ መስመር
አልፈው ለጡረታ የበቁት፤ አሁን በበረራ ላይ የተሰማሩት የኢትዮጵያ
አቪዬሽን ሰዎች፣ ከድንበራችን አልፈን ሄደን በዚህ ሙያ ያስተማ
ርናቸውና ወደ ኢትዮጵያም መጥተው በማንኛውም መስክ ስለ አቭዬሽን





ትምህርት ከኢትዮጵያውያን የቀሰሙት ሁሉ ማስታወስ ያለባቸው አንድ
ትልቅ ቁም ነገር አለ። ይኸውም የኢትዮጵያ አቪዬሽን አሁን ካለበት ደረጃ
ለመድረስ የቻለው በበረራ ሥራቸው ላይ እያሉ በድንገት በአይሮፕላን
አደጋ በሞት የተለዩት ፓይለቶችና አብረው ያለፉት ሙያተኞች በሕይወ
ታቸው የከፈሉት መስዋእትነት ጥሎት ያለፈውን ትምህርት መሰረት
አድርጎ በተገነባው የበረራ ልምድና ሙያ ነው። የተገኘው ጥበብና በሥራ
ላይ የዋሉት የትምህርት ማሻሻያዎች ልምዶች ላገኘነው ውጤትና አሁን
ላለንበት ለማንኛውም አገር ሊሰጥ የሚችል የአቪዬሽን ዕውቀት ባለቤት
መሆን ያስቻለን መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

ሐጎስ የተባሉ ፓይለት በቢ-17 አይሮፕላን በ1942 ዓ.ም በደረሰባቸው
የሞት አደጋ ምክንያት በዚያን ጊዜ በትምህርት ቤት የነበርነው ወጣቶች
ገና አየር ኃይል ሳንቀጠር በዝና በሰማነው ቢ -17 በአእምሯችን ላይ
ተፅእኖ አሳድሮ እንደነበር እናስታውሳለን። በአንድ ወቅት ከተቀጠረው
ቡድን ሁለት አይሮፕላኖች እያንዳንዳቸው ውስጥ ሦስት ዕጩ መኰንኖች
እንደያዙ በሁለት ልዩ ልዩ ቦታዎች ሲበሩ በአንድ ቀን ውስጥ
ባጋጠሟቸው አደጋዎች ምክንያት ከአንዱ ፓይለት በስተቀር አምስቱም
ሕይወታቸው አልፏል። በዚህ ጊዜ አየር ኃይል ውስጥ የሚገኘውን
ሠራዊት ብቻ ሳይሆን መላውን የአካባቢውንና የአዲስ አበባን ሕዝብ
አስደንግጧል። በወቅቱ የተሸበረው ሕዝብ በማንኛውም መስክ ላይ ለተሰ
ማራ የአየር ኃይል ባልደረባ ዘመድ የሆነው ሁሉ ነበር።

ለቅንጦት ዝቅ ብሎ በመብረር የተነሳ ከደረሰው አደጋ የተገኘው ትምህ
ርት፣ የትምህርት አሰጣጥ ፕሮግራሙን በማሻሻልና በዚያን ጊዜ በረራ
ትምህርት ቤት ለሚገኙት ብቻ ሳይሆን ወደፊት ለሚቀጠሩት ፓይለቶች
በትምህርት ላይ እያሉ ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው የሚያ
ስገነዝብ ትልቅ ትምህርት ሰጥቶ አልፏል።

ዕጩ መኰንን ሙሉፀጋ ስብሐት አንድ ዕለት ቢ-17 አይሮፕላን ሲያበር
የሞተሩ ዘይት ማቀዝቀዣ ተሰብሮ ከፊት ለፊቱ ያለውን መስታዎት
ዘይት ይሸፍነዋል። ለማረፍ ወደ ሜዳው ሲቃረብ ፊት ለፊት የሜዳውን
አቅጣጫ አይቶ ማስተካከል እያቃተው ደጋግሞ ዞሮ ለማረፍ ያደረገው
ሙከራ አልተሳካለትም። እንደ አሁኑ በሬድዮ እየተመሩ ለማሳረፍ
የሚያስችሉና ለማረፊያው ሜዳ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ገና ወደ አገር
ውስጥ አልገቡም። ጥራት ያለው መልእክት በድምጽ ለማስተላለፍ
እንኳን አይሮፕላኑ ከፍተኛ የሬድዮ ፍሪኩዌንሲ መገናኛ አልነበረውም።
ስለዚህ ከዱከም በታች ለጥ ካለው ሜዳ ላይ አይሮፕላኑን በሆዱ ለማሳ
ረፍ ወስኖ በአንድ በኩል ወደ መሬት መቃረቡን እየተመለከተ ለማሳረፍ
ሲጠጋ በማይታየው በኩል ከነበረ ዛፍ ጋር የአይሮፕላኑ ክንፍ ተጋጭቶ

በተነሳው እሳት ተቃጥሎ አብራሪው ሕይወቱ አልፏል፡፡ አብሮት የነበረው የሬድዮ ኦፕሬተር ዕጩ መኰንን ጌታቸው ተክለማርያም በግጭቱ ከተገነጠለው አይሮፕላን ጭራ ውስጥ ራቅ ብሎ ተገኝቶ፣ ገበሬዎች ደርሰውለት ከቃጠሎው አድነው ሕክምና ከተደረገለት በኋላ በሌላ ሥራ ሊሰማራ ችሏል፡፡

በአንድ አጋጣሚ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ የአየር ኃይል አዛዥ ከነበሩት ከኰሎኔል ቮን ሮዘን ጋር ስለዚህ አደጋ አንስቶ ሲወያዩ እሳቸው፣ "እኔ በዚያን ዕለት ደብረዘይት ብኖር ሙሉፀጋ አይሞትም ነበር" አሉ፡፡ «እንዴት?» ቢባሉ፣ "እኔ በሌላ አይሮፕላን ወጥቼ ከጎኔ እንዲበር አደርግና እኔን እያየ እንዲወርድና ለማረፍ ተዘጋጅቶ ሜዳው ጫፍ እንዲደርስ አደርገዋለሁ፡፡ ፊት ለፊት ማየት የተሳነው አይሮፕላን በሚያርፍበት ከፍታና ፍጥነት ከሜዳው የመጀመሪያ ጫፍ ከደረሰ በደህናውም ጊዜ ቢሆን በቢ- 17 ሜዳውን ፊት ለፊት ለማየት የሚቻለው ጭራው ከፍ ባለበት ጊዜ ብቻ በመሆኑ አስተካክሎ ቀጥታ ለመያዝ ልምዱ ስላለው በደህና ያሳረፍ ነበር" ብለዋል፡፡ በወቅቱ ሜዳው ላይ የነበሩት አስተማሪዎች እንደሳቸው አላሰቡም እንጂ አባባሉ ትክክል ይመስላል፡፡

በአሥመራ አይሮፕላን ጣቢያ አካባቢ ሌላ ቢ-17 አይሮፕላን ሲወድቅ ለሁለት ተከፍሎ ፓይለቱ ተስፋዬ ሽፋው ተወርውሮ ሲወጣ የአካባቢው ገበሬዎች ከቃጠሎው አድነውታል፡፡ አብሮት ይበር የነበረው ሬዲዮ ኦፕሬተር አብዲ አብዱላሂ፣ ከእሳቱ መውጣት አቅቶት ተቃጥሎ ሞቷል፡፡ ከቃጠሎው የተረፈው አካሉ ሁለት እፍኝ የሚያህል ሆኖ እሱው በሬሳ ሳጥን ተደርጎ ለቀብር በሚሄድበት ጊዜ የእስልምና ሃይማኖት አባቶች በእምነታቸው መሰረት «አስከሬን በሳጥን አይቀበርም» ብለው ስለ ተቃወሙ ስለ ቃጠሎው ሁኔታና ከውስጡም ተርፎ የተገኘው አነስተኛ ስለመሆኑ ብዙ ገለጻ ከተደረገ በኋላ የቀብሩ ሥነ ሥርአት ተፈጽሟል፡፡

## የፓራሹት ዝላይ

ካፕቴን ላቀው ወልደማርያም (በዚያን ጊዜ እጩ መኰንን) በአብራሪነት በአየር ኃይል በሚያገለግሉበት ዘመን (1945 ዓ.ም) (ካፕቴን ላቀው ወደ አየር መንገድ ተዘዋውረው የብዙ ዓመታት አገልግሎት ካበረከቱ በኋላ፣ በጡረታ ሲኖሩ በድንገት በደረሰባቸው ሕመም በ1980 ዓ.ም አርፈዋል፡፡)





ያጋጠማቸውን የመጀመሪያውን የፓራሹት ዝላይ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

«ጅጅጋ ሜዳ ላይ በቢ-17 ዳይቪንግ (በምብ ለመጣል አሽቆልቁሎ መውረድ) ልምምድ ስናደርግ ወደ ኮክፒት ሲገባ ክንፉ ላይ እንዲያንሸራትት የተለጠፈው እግር መርገጫ ጎማ ተቀዶ ይበራል፡፡ ይህ ሲሆን እኔ አላየሁትም፡፡ በበረራው ላይ ምንም ችግር ስላልነበረ ፕሮግራማችንን ጨርሰን፣ ካርፊን በኋላ አብሮኝ ይበር የነበረውን ሬዲዮ ኦፕሬተር ታዴ! (ኰሎኔል ታደሰ ተሊላ በዚያን ጊዜ ም/መቶ አለቃ) የበረርነው ሰዓት ስንት ነው ብዬ ደጋግሜ ብጠይቅ መልስ አጣሁ፡፡ እንዱ መጥቶ ታዴማ ጅጅጋ ከተማ በፓራሹት አርፏል ብሎ እስከነገረኝ ድረስ መውረዱን አላውቅም» ነበር ያሉት፡፡ በጃንጥላ የውረዱት ኰሎኔል ታደሰ ተሊላ በሕይወት ስላሉ ይህንኑ ነው ያረጋገጡት፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በግንቦት 10 ቀን 1946 ዓ.ም (በዚያን ጊዜ እጩ መኰንን የነበሩት) የመቶ አለቃ መኰንን አበበና ኰሎኔል ማሞ ወልደ ማርያም (በዚያን ጊዜ እጩ መኰንን) ለናቪጌሽን በረራ ከአስመራ ተነስተው ወደ ደቡብ ያበራሉ፡፡ በሰዓታቸው ሳይመለሱ በመቅረታቸው ለፍለጋ የሚሄዱት አይሮፕላኖች በመዘጋጀት ላይ እንዳሉ አብራሪው በሕይወት እንደተገኙ የሚገልጽ የስልክ መልእክት ይደርሳል፡፡ «እንዴት አንድ ሰው ብቻ ይገኛል?» ለሚለው ጥያቄ ፓይለቱን ያገኙት ሰዎች ሊያስረዱ አልቻሉም፡፡ ማምሻዉን ደግሞ «ከአየር በጃንጥላ የወረደ አንድ አብራሪ አግኝተናል» የሚል የስልክ መልእክት ከሌላ ቦታ መጣ፡፡ ሁለቱም በሕይወት በመገኘታቸው እዚያ ያለው ሠራዊት ተደስቶ ሁኔታው ግን እንቆቅልሽ ሆኖ አደረ፡፡ በማግስቱ ሁለቱም ከያሉበት ቦታ በመኪና ወደ አስመራ አየር ኃይል ጣቢያ ተመለሱ፡፡ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ በዚያን ጊዜ አስመራ ተመድቦ ይሠራ ስለነበረ ስለ አደጋው የሚያውቀው ይህ ሲሆን ሁኔታው ያጋጠማቸው ኮ/ል ማሞ ወልደ ማርያም በጽሑፍ የቀረቡት ሪፖርት በከፊል የሚከተለው ነው፡፡

*" . . . .ማሞ ስለ አይሮፕላኑ በረራ ቅመራ (የናቪጌሽን ሥራ) በማዘጋጀት ላይ እንዳለ ድምጹ በጣም የራቀ የሬዲዮ ድምጽ እየተደጋገመ ሲተላለፍ ይሰማል፡፡ ምናልባት ከመሬት ካለው ጣቢያ ይሆናል ብሎ ቢጠይቅም «አልተፈለግህም ተጠባበቅ» ተብሎ ይነግረዋል፡፡ ሥራውን ቢቀጥልም መልእክቱ ግን አልተቋረጠም፡፡ ማሞ የመልእክቱ መደጋገም ስላስጨነቀው ምናልባት የአደጋ ምልክት ሊሆን ይችላል ብሎ በማሰብ ሥራውን ያቆምና መልእክቱን በጽሑፍ ይቀበላል፡፡ መልእክቱ «ማሞ፡ አንድ ጭስ ጭስ የሚል ያልተለመደ ነገር ይሸታልና አይተህ ንገረኝ፡፡ ኦኮ» ይላል፡፡ (ኦኮና ማሞ መባባሉ ለበረራ ፕሮግራም ሲባል የወጣው ከመጠሪያ*

ስማችን ውስጥ ካሉት የላቲን ፊደላት ሦስቱን የያዘ ነው):: ማሞ መልእክቱ ከፓይለቱ መሆኑን በመረዳት አካባቢውን ሁሉ ለማየት በተሸከርካሪው ወንበሩ ላይ እንዳለ ወደ ኋላው ዞር ብሎ ሲመለከት ጭጋግ የመሰለ ጭስ ይመለከታል:: ወደፊት ዞር ብሎ የመገናኛ መሣሪያውን ሲፈትሽ ኮንታክት እያደረገ ሬመጥ የሚመስል እሳት ሲረጭ ያያል፣ አካባቢውም በኮንታክቱ ምክንያት ጭስ ይተፋል:: ግን የሚነድ ነገር የለም:: በዚህን ጊዜ ሁኔታዉን ለፓይለቱ ለመኮንን በውስጥ መገናኛ ለመንገር ሲዘጋጅና መሣሪያውን ሲነካ መገናኛው ፀጥ ይላል:: በዚህ ጊዜ ማሞ ሁሉን ነገር ያጠፋፋና ሁኔታውን ከፊት ለፊቱ ላለው ለፓይለቱ ለመኮንን በጽሑፍ ለመስጠት መቀመጫው ላይ ቆሞ ወረወረለት:: የአይሮፕላኑ ንቅናቄ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ የሚነቀንቅ ሁኔታ ውስጥ ገብቷል:: አንዴ ሽቅብ አንዴ ቁልቁል በሌላው ጊዜ ደግሞ ጭልጥ ብሎ ይሰምጣል:: ማሞ ተመልሶ መቀመጫው ላይ ለመቀመጥ ጥረት እያደረገ አፍኖት የነበረው ጭስ ከበፊቱ በማየሉ ሙሉ በሙሉ መስኮቱን ለመክፈትና ለማስወጣት ሲሞክር በወፍራም ሽቦ በመታሰሩ መስኮቱ አልከፈትም ይላል:: በዚህ ጊዜ መቀመጫው ላይ እንደቆመ በእግሩ ሲረግጠው ሽቦው ሲበጠስ በአንደኛው በኩል ይቀረቀራል:: ከዚያም ማሞ ወንበሩ ላይ እንደቆመ የሬዲዮ አንቴናውን ዘንግ በመያዝ የተቀረቀረውን መስኮት ለማስለቀቅ ሲሞክር ተገንጥሎ ይወጣና የፓራሹት መያዣ ቀበቶው ላይ ይሰካል:: ከዚህ በኋላ ማሞ ወደ ውስጥ ተመልሶ ለመግባት ባለመቻሉና መስኮቱም በጀርባው ላይ ስለተቀረቀረበት የግድ መዝለል እንዳለበት አረጋግጦ ሁሉን ካመቻቸ በኋላ አይሮፕላኑ በማዘቅዘቅ ላይ እንዳለ ወደ አይሮፕላኑ የግራ ክንፍ ላይ ይዘላል:: መስኮቱ ጀርባው ላይ ነው:: ልክ እንደዘለለ ጀርባው ላይ ተቀርቅሮ የነበረው መስኮት የአይሮፕላኑ (ስታብላይዘር) ወይም ጭራ ብትንትኑን ያወጣዋል:: ፍንጣሪዉም ማሞን ጭንቅላቱ ላይ በስተቀኝ በኩል ይመታዋል::

ማሞ ከአይሮፕላኑ ከተለየ በኋላ ፓራሹቱን ከፍቶ በዝግታ ወደ መሬት እያመራ ነው:: አይሮፕላኑ እሱ ካለበት ቦታ በርቀት በዐይን ለማየት በሚያስቸግር ሁኔታ ተራሮች መካከል ገብቶ ሲበር ያያል:: ሆኖም በፓራሹት ላይ የተንጠለጠለውን የመስኮቱን ቀሪ ፍሬም ከላዩ ላይ ለማስለቀቅ ሲሞክር አይሮፕላኑ ከዐይኑ ይሰወራል፣ ለማየት አልቻለም:: ማሞ መሬት ለመድረስ ስለቸኮለ ፓራሹቱ የሚወርድ ስላልመሰለው ሥጋት ላይ ቢሆንም ዝቅ ብሎ የፓራሹቱን ፍጥነት ከአካባቢው ጋር ሲመለከት ካሰበው በላይ ፍጥነት እንዳለው በማየቱ በፓራሹቱ ገመዶች ላይ በመንጠላጠል በዝግታ ድንጋያማ መሬት ላይ በደህና ለማረፍ በቃ:: ፓይለቱም አይሮፕላኑ የሚበርበትን ከፍታ በመቀነሱ በአንድ ድንጋያማና እርሻ መሰል ቦታ ላይ በድንገተኛ አሳርፎ፣ አይሮፕላኑ ሦስት ቦታ ላይ ተቆርጦ እሱ በደህና ወጥቷል::





ማሞ ራሱ ላይ በደረሰው ጉዳት የተነሳ ለሰባት ቀናት ሆስፒታል ተኝቶ ከታከመ በኋላ ድኖ ወጣ:: መኮንንም ምርመራ ተደርጎለት ወደ ሥራው ተመልሷል:: ይህ ሁኔታ የሚያስገነዝበው አይሮፕላን አብራሪዎች በተለይ የጦር አይሮፕላን የሚያበሩ ሰዎች በፓራሹት ላይ ያላቸው እምነት እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ነው:: ፓራሹት በምንም ዓይነት ዋጋ የማይገኘውን የሰውን ሕይወት ለማዳን እስከ አሁን ድረስ ተወዳዳሪ አልተገኘለትም:: ማሞ የፓዮኒር ፓራሹት ኩባንያ በሠራው ፓራሹት ዘሎ ስለዳነ የኩባንያዉን ሜዳልያና ፒን እንዲሁም የኩባንያው አባልነት ምስክር ወረቀት ተሰጥቶታል::»

ይህ እንደ ሶፋ ትራስ መቀመጫ ያለ ሆኖ በልዩ ናይለን ቀበቶ በበራሪዎች ሰውነት ላይ የሚታሰረው የሕይወት ማዳኛ ሰፊ ጃንጥላ መልክ መንሳፈፊያ መሣሪያ (ፓራሹት) ጥቅሙ ብዙ ባልተሞከረበት ጊዜ እንደዚህ ያለ አስተማማኝ ውጤት በሥራ ላይ መታየቱ አብራሪ የነበሩትን ሁሉ አስደስቷል:: በተለይ በትምህርት መልክ በየጊዜው ፓራሹቶች እየተፈቱ የሚጠቀልሉት በአብራሪዎቹ ስለሆኑ ያለምንም ችግር በደህና ማሳረፉ በጣም የሚያኮራ ነበር::

ይህንን ታሪክ የአሁኑ የኢትዮጵያ ፕሬዚዴንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ «አየርና ሰው» በሚል ርዕስ በ1951 ዓ.ም. ባወጡት መጽሐፍ ውስጥ «ፓይለቱ የሚበርበትን ከፍታ ለመጠበቅ በሁለት እጁ ይታገል የነበረው የአይሮፕላኑ ከፍታ እንዳይጨምር ነበር:: የማስተማሪያ አይሮፕላን ስለሆነ ከኋላ ያለው የማብረሪያ ዘንግ ዋናዉ ሬዲዮ ኦፕሬተር በሚበርበት ጊዜ ተነቅሎ ከስር የምትቀረው መቆጣጠሪያ ላይ ማሞ ሳያውቅ ቆሞበት ተንጠራርቶ «ጭስ ጭስ ይሸተኛል» የሚል መልእክት ለመስጠት ይሞክራል:: ለመደማመጥ ሳይችሉ ቀርተው ማሞ ወደ መቀመጫው ሲመለስ የተረገጠውን መቆጣጠሪያ ሲለቀዉ በድንገት አዘቅዝቆ (ዳይቭ) መግባቱ የመቀመጫዉን ቀበቶ ያላላው ማሞ ከነመስኮቱ አየር ላይ ለብቻዉ ቀረ:: ከዚያም ጃንጥላውን ከፍቶ ወረደ» በማለት አቅርበውታል::[1] ሙሉ ገለጻው ከመጽሐፉ መጨረሻ ማስታወሻዎች ላይ ይገኛል::

# የእረፍት ጊዜ የአለባበስ ሥነ ሥርዓት

አንድ የአየር ኃይል አባል ከተወሰነ የትምህርት ሥልጠና ወይም የሥራ ወቅት በኋላ፣ ለእረፍት ሲወጣ እጅግ ሰፋ ያለ ሥርአት መጠበቅ ግዴታ ነበረበት። በእጩ መኮንንነት ደረጃ ባለበት ጊዜያት ለእረፍት ወደ ከተማ ወጥቶ በሲቪል ልብስ መታየት ከባድ ቅጣት ያስከትላል። በአንድ ወቅት በጣም ከሚመሳሰሉ መንትያ ወንድማማቾች አንደኛው አየር ኃይል ተቀጥሮ ሳለ ሲቪል ሠራተኛ ወንድሙ በሲቪል ልብስ ከተማ ውስጥ ስለታየ ወንድሙን እጩ መኮንን ወልደ ዮሐንስ መስሏቸው ማስታወሻ የወሰዱት መኮንን ሊቀጡት በተጠራበት ጊዜ ለማስረዳት ምስክሮች መቅረብ ነበረባቸው። የአየር ኃይል አባላት አለባበስ ልዩ ጌጥና ውበት ለማንኛውም ወጣት ልዩ መስህብ ስለነበረው የገበርዲን ዩኒፎርምና የደንብ ልብስ ለአዲስ ወጣቶች ምልመላ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ከሁሉ በፊት በፈቃድ ወደ ውጭ መሄድ የሚቻለው፣ ወቅቱን ጠብቆ እንጂ እንዳመቸ መሄድ አይቻልም። ከዚህ ጋር መደበኛ ወታደራዊ ሥርአት ማሟላትን ማረጋገጥ የቅድመ ሁኔታ ግዴታ ነው። ይህም መላ ወታደራዊ አቋሙን ማለትም ከፀጉር እስከ መላ ወታደራዊ አለባበስ፣ አካሄድና ሌሎች ሥርአት ጠቀስ ሁኔታዎች ፍጹም የተሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት። ዝርዝሮቹ ብዙ ቢሆኑም ግለሰቡ ራሱን አርሞና አስተካክሎ በራሱ ተማምኖ መውጣትን እንደግልም ሆነ እንደ ጠቅላላዉ አየር ኃይል አባል ባሕርይ እንደ ጥሩ መታወቂያው እንደምሳሌነት አደራ ስለሚቆጥረውና፣ በዚህም አድራጎት ስለሚኮራበት ሆነ ብሎ ይፈጽማል። በዚህ አኳኋን በፈቃድ የወጣ የአየር ኃይል አባል አልባሌ ቦታ መታየትን እንደ ከፍተኛ ነውር ስለሚቆጥረው ይህንን የመሰለ ድርጊት ያስወግዳል።

የአየር ኃይል አባል አሰለጣጠን ሥርአት የማስተዋልን፣ እዉቀት የመቅሰምን፣ የሞራል ግንባታን፣ የሥራ ወዳድነትን፣የሀገር ፍቅርን፣ በኅብረት ለላቀ ውጤት መሥራትን፣ የአየር ኃይል ግንባታ መማርን፣ ወታደራዊ ሥነ ሥርአትንና የሀገር ባሕልን ማክበርን ዓላማ ያደረገ ነው። ስለሆነም የመላው አባላት የዕድገት እርምጃ እነዚህን ዓላማዎች የተመረኮዘና ተፈጻሚነታቸውን የተከተለ በመሆኑ አስተዳደጉ ግብረገብ ያለው ነው ማለት ይቻላል። በዚህ መሠረት አባሉ በኅብረተሰቡ ዘንድ በማንኛዉም መልኩ ተከባሪነትና ተወዳጅነት የማግኘት ዕድል እንደገጠመው ይኖር ነበር።





አየር ኃይል ወደ ቢሾፍቱ ከተዘዋወረበት ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው ሠራዊቱን በወታደራዊ ትምህርት ያሰለጥኑ የነበሩት በአዲስ መልክ በእጩ መኮንንነት ጀምረው በስዊድኖች ያሰለጠኑት የክብር ዘበኛ መኮንኖች ነበሩ። ትምህርታቸውን በሚገባ ካጠናቀቁ በኋላ መኮንኖች እንደሆኑ በተራ ወደ ቢሾፍቱ እየመጡ የአንደኛንና የሁለተኛን ኮርስ ያሰለጠኑት መኮንኖች፡ መርእድ ግዛው (ሜ/ጄኔራል)፣ ተፈራ ወልደ ተንሣይ (ሻለቃ)፣ ዮሐንስ ጳውሎስ (ሻለቃ)፣ ዘውዴ ማንደፍሮ (ሻለቃ) ነበሩ።

ሦስተኛን ኮርስ ያሰለጠኑት፡ ታምራት ተሰማ (ብ/ጄኔራል)፣ ፍስሐ ገብረ ሚካኤል (ሻምበል)፣ አጥናፉ መኮንን (ሻምበል)፣ ዱፌራ አብሳ (ሻምበል)፣ ታደሰ ሺበል (መቶ አለቃ) ነበሩ።

ለፓይለትነት ስልጠና ወደ አየር ኃይል የመጡ መኮንኖች፣

ጌታቸው ኃይለሚካኤል (ሻምበል)

ታደሰ ታምሬ (ሻለቃ)

ይገዙ ይመኔ (ኮሎኔል) አርሚ አቪዬሽን አዛዥ ሆነው ከስልሳዎቹ ጋር የተረሸኑ

ተስፋዬ ተሰማ (መቶ አለቃ) በአይሮፕላን አደጋ የሞቱ።

አየለ ከበደ (መቶ አለቃ) በአይሮፕላን አደጋ የሞቱ።

ከጦር ኃይል በወታደራዊ ሕግ ሰፊ ትምህርት ለአየር ኃይል የሰጡት፣ ኮሎኔል ተስፋ ደስታ ነበሩ።

ጠቅላላ ሠራዊቱን ወታደራዊ ትምህርት የሰጡት የጦር ኃይል መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች፡

ፍቅሩ ወልደተንሣይ (ኮሎኔል)፣


ከበደ ፈለቀ (ሻምበል)


ፀጋዬ ይመር (ሻምበል)

የሃምሳ አለቃ አብሴ አያና

የሃምሳ አለቃ ኃይለጊዮርጊስ

የሃምሳ አለቃ ካሣ ዘለለው ነበሩ።







የአየር ኃይል አለባበስ









የአየር ኃይል የደንብ አለባበስ

# አሥመራ ምደባ

የእንግሊዝ ጦር አስመራን ለቆ በወጣ ማግስት አንድ የቢ-17 ስኳድሮን አራት አራት አይሮፕላኖች በሁለት ተከፍለው ሌላው ሠራተኛ በአንድ ሲ-47 የመንገደኛ አይሮፕላን ሆነው አስመራ ገቡ። ቡድኑ እንደደረሰ በመጀመሪያ የተመለከተው አይሮፕላን ማረፊያ አካባቢ የነበረውን የጦር ሠፈር ነበር። የመሥሪያ ቤቶች መጸዳጃ ቤቶች መቆሸሽ፣ የመስተዋቶችና የበሮች መሰባበር፣ በያለበት የሚታየው ሳይጠረግ የቆየ የብዙ ጊዜ የሸረሪት ድር የሸፈነውና የተከመረው ማንኛዉም ዓይነት ስብርባሪ ለዐይን የከፋ ነበር። በጠቅላላው አያያዙና የነበረበት ሁኔታ በጣም የሚያሳፍርና ሠራዊቱ በዚህ ሁኔታ ሰፈሮ ሳይሆን ሆን ተብሎ እንዳይጠቅም የተደረገ እንጂ በዚያን ዓይነት የኑሮ ደረጃ ይኖር ነበረ ብሎ ለመገመት አዳጋች ነበረ። የሆነው ሆኖ ሁኔታው እስከሚስተካከል በከተማው መሀል በሚገኘው ሮያል ሆቴል ጠቅላላ ሠራተኛውን ማኖር አስፈለገ። በዚያን ጊዜ ማንኛዉም ጥቁር በዚህ መንገድ ላይ በሚገኙት

ሆቴሎች፣ ቡና ቤቶችና ዳንስ ቤቶች መግባት የሚከለክለው እጅግ ዘረኛ የእንግሊዞች ሕግ ገና ከተሜውን ስላለቀቀው ብዙ አይታዩም:: የአየር ኃይል ሠራዊት አባል ግን ያሳንዳች ፍርሐት በያለበት ይገባ ነበር:: እንደነአልቤርጎ ቻዎ ያሉት ትልልቅ ሆቴሎችና ከተማው ውስጥ ያሉት ሦስት የማታ ክበቦች በብዛት ይገኙ የነበሩትን ጣሊያኖችና አሜሪካኖች (እዚያው ይገኝ የነበረው መገናኛ ሠራተኞች) ብቻ ያስተናግዱ የነበሩት፣ የዚህን ዓይነት የዘረኝነት እገዳ የማያውቀው የሠራዊቱ አባል በሙሉ ልብ ሲገባ የአገሬው ሕዝብ ለጉድ ነበር የሚያዩት:: በአይሮፕላን ጣቢያዉ ቅጥር ግቢ ውስጥ የነበሩትን ቤቶች ለመኖሪያ እንዲስማሙ አድርጎ ለማደስና ለአስተዳደር የሚሆኑ ቢሮዎች ለማዘጋጀት ብዙ ወጪ አስወጥቷል፣ ሠራተኛውንም ሆቴል ማኖርና መመገብ ከፍ ያለ ወጪ ጠይቋል::

በዚያን ጊዜ ከሁሉም የተውጣጣ ቡድን ደብረዘይት በሚገኘው የአየር ኃይል ዋና ሠፈር በዓመት አንድ ጊዜ ተሰብስቦ የተቀነባበረ የአየር ትርኢት ያሳይ ነበር:: በዚሁ መሠረት የቢ-17 ዊንግ አባላት አብዛኛዎቹ ከአስመራ ወደ ደብረዘይት ሲሄዱ አንደኛዉ አይሮፕላን ጉርኣ አይሮፕላን ማረፊያ ስለተበላሸ ሁለት አይሮፕላኖች አብረዉ እንዲበሩ ለማድረግ የተበላሸውን አይሮፕላን አንድ የስዊድን ተወላጅ እስከ ሚጠግነው ኮ/ል ሥምረት ሙድኅኔና እኔ እንድንጠብቅ ተደረገ::

የጉርኣ አይሮፕላን ሜዳ ከአስመራ 35 ኪ/ሜ ላይ በደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ የሚገኝ ጣልያን ኢትዮጵያን ለመውረር በምትዘጋጅበት ጊዜ ካፕሮኒ የተባሉ የጦር አይሮፕላኖች ለመገጣጠምና ለማደስ የተቋቋመ የአየር ኃይል ሠፈር ነው:: ከዚህ በሲሚንቶ የተሠራ ረጅም ሜዳ አካባቢ ይገኝ የነበረው የጦር ሠፈር ፈራርሶ የቀረው የትልልቅ አይሮ ፕላኖች ማቆሚያ መጋዘኖችና የብዙ ቤቶች የመሰረት ሲሚንቶ ነበር::

አይሮፕላኑ እስከሚሠራ ድረስ አካባቢውን እየተዘዋወርን ስንመለከት እነዚህ የቤት ፍርስራሾችና ለምልክት ብቻ የሚታየው የመሰረት ሲሚ ንቶ አሁን እንደምንረዳው ለሌላ ጉዳይም ውለዋል:: የሁለተኛዉ ዓለም ጦርነት ተፋፍሞ የጀርመናዊው የጄኔራል ሮሜል ታንኮች እያጓሩ ወደ ካይሮ በሚገሰግሱበት ወቅት በአትላንቲክ ውቅያኖስ በኩል ለእንግሊዝ መንግሥት ርዳታ የሚቀርቡትን መርከቦች የጀርመን ባሕር ኃይል እያሳ ደዱ በማስመጣቸው፣ ግብጽ ውስጥ ያለው የእንግሊዝ ጦር ርዳታ እንዲደርሰው ስለተፈለገ ሌላ መስመር መክፈት ግድ ሆነ:: አሜሪካ የገለልተኝነት ፖሊሲ በምታራምድበት ጊዜ የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ዊንስተን ቸርችል ካይሮ ለሚገኘው ጦር አስቸኳይ ርዳታ እንዲደርሰዉ ፕሬዚዴንት ሩዝቬልትን ይጠይቃሉ::








አስመራ ተመድቦ የነበረው ስኳድሮን ከጄኔራል አሰፋ አየነና ከስኳድሮን አዛዥ ካፕቴን ጆንግሬን ጋር

በዚህ መሠረት «ምስጢራዊ ግዳጅ 19» በመባል የታወቀ ከፍተኛ ምስጢራዊ ኃይል ( Project 19 A Mission Most Secret) ይቋቋማል:: ይኸውም በማክዶናልድ የአይሮፕላን ፋብሪካ ስር በከፍተኛ ጥንቃቄ የተመረጡ 3000 ሲቪል የአይሮፕላን ሠራተኞች አሰባስቦ በምስጢር ከአሜሪካ በመርከብ በደቡብ አፍሪካ በኩል በሕንድ ውቅያኖስና ቀይ ባሕር አድርጎ ምጽዋ ወደብ ማድረስ፣ ከዚያም በመንገድ ጉርኣ ማድረ ስና የአይሮፕላን መገጣጠሚያና ማደሻ ማቋቋም ነበር:: እያንዳንዱ ተቀጣሪ ወዶ የገባው ውል በጠላት ቢያዝና ቢታሰር ወይም ቢሞት የአሜሪካ መንግሥት አያውቀኝም የሚል ነው:: ለሥራው ጥሩ የገንዘብ ክፍያ ነበረው:: ከምጽዋ ወደብ በማይ ሀበር ሸለቆውን ተከትሎ በቀጥታ ወደ ደቀ መሐሪ በሚወስደው የአስፋልት መንገድ አሜሪካኖቹ ጉርኣ ደርሰው፣ ከጦርነቱ የተረፉትን ጥቂት ጣሊያኖችንም ቀጥረው፣ የፒሬሊ ጎማ ይሠራ የነበረውን እንደገና አድሰው ትልቅ የጦር አይሮፕላኖች መገጣጠሚያና በውጊያ የተጎዱትን አይሮፕላኖች ማደሻ ጣቢያ አቋቋሙ:: ይህ ጣቢያ ከ3000 በላይ በሚሆን የሰው ኃይል ሁሉን የሚያሟላ የጦር አይሮፕላኖች ማደሻ ሠፈር ሆኖ አገልግሏል::



አስመራ ተመድቦ የነበረው ስኳድሮን ከጄኔራል አሰፋ አየነና ከስኳድሮን አዛዥ ካፕቴን ጆንግሬን ጋር

ታኅሣስ 29 ቀን 1934 ዓ.ም አሜሪካ ወደ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ስትገባ በከፍተኛ ደረጃ ለሰሜን አፍሪካ ጦርነት ያስፈልጉ የነበሩ የጦርና የትራንስፖርት አይሮፕላኖች ከጉርኣ እየተነሱ ተዋግተዋል። በጦር ነቱም የተመቱ ከዚህ ጣቢያ ታድሰዋል። የሜዲቴራኒያንና የሰሜን አፍሪካ ጦርነት በ1936 ዓ.ም. ሲያልቅ፣ የፓስፊክ ውቅያኖስና የጃፓን ጦርነት እየተፋፋመ ሲሄድ «ግዳጅ 19» በአስቸኳይ በመጣበት አኳኋን በከፍተኛ ምስጢራዊ መንገድ በእንግሊዞች ፈራርሶ ወደ ሕንድ ተዛወረ።2

የዚህን ፍርስራሽ እየተመለከተን ሳለ አይሮፕላኑን ይጠግን የነበረው ስዊድናዊ መካኒክ «አሁን ሠርቼዋለሁ» ይልና ሁለቱን አይሮፕላኖች ወደ አስመራ መለስን። አስመራ ካረፍን በኋላ ተበላሽቶ የተሠራው አይሮፕላን ሞተር አልጠፋም አለ። በዚህ ጊዜ መካኒኩ የሠራውን ተንኮል ተረዳን። የአይሮፕላኑ እሣት ማቀጣጠያዎች (ማግኔቶ) ለሴፍቲ ሲባል ሁለት ስለሆኑ አይሮፕላኑ ከመነሳቱ በፊት ፓይለቱ በተራ በተራ አንዱን እያጠፋ ሌላው መሥራቱን በማረጋገጥ ነው ለበረራ የሚነሳው። ይህ የስዊድን መካኒክ ሽቦዎቹን በማጠላለፍ በፍተሻው ወቅት ሁሉም የሚሠራ መስሎ እንዲታይ በማድረጉ ከባድ ወንጀል ነው በማለት ይህና ሌሎች ወደ አስር የሚጠጉ ጉድለቶች ተጨምረው ማመልከቻ በምስጢር ተጽፎ፣ በጊዜው ማንኛውም የአየር ኃይል ጉዳይ ለንጉሠ ነገሥቱ የሚቀርቡትና ውሳኔያቸው የሚተላለፈው በክቡር ፀሐፌ ትእዛዝ ተፈራወርቅ በኩል ስለነበር፣ መጋቢት 26 ቀን 1945 ዓ.ም በፖስታ ተላከላቸው። የማመልከቻው ፍሬ ነገር የአደጋዎች መብዛትና አይሮፕላኑ ጊዜው ያለፈበትና አሮጌ መሆኑን በመጥቀስ በተጨማሪ እንዲገዙ የታቀደው አሮጌ ቢ-17 አይሮፕላኖች እንዲቀሩና በተሻለ አይሮፕላን እንዲለወጥ ነበር።

በዚህ የተነሳ አየር ኃይላችንን ለመጎብኘት የመጡትን የስዊድን ጄኔራል ጨምሮ በኰሎኔል ቮን ሮዘን ሰብሳቢነት ጄኔራል አሰፋ አየነና (በዚያን ጊዜ ኮሎኔል) በጠቅላላ አስመራ የሚገኙት የሠራዊቱ አባላት የተገኙበት የሦስት ቀናት ስብሰባ ተደርጎ አቤቱታ የቀረቡባቸው አይሮፕላኖች እንዳ ይበሩ ተደርጎ፣ ግን ከአቤቱታ አቅራቢዎቹ መሀል ጥቂቶቹ ሁለት ጊዜ ወደ ስዊድን በመመላለስ በተጨማሪ የተገዙትን ቢ-17 አይሮፕላኖች እንዲያመጡ ተደርጓል።

ቅሬታ ያስነሱት አይሮፕላኖች ሀንጋር ውስጥ ታሽገው ብዙ ጊዜ ከቆዩ በኋላ በአይሮፕላን ምሕንድስና አዲስ የሰለጠኑ ቴክኒሺያኖች (ኢ-2) ወደ አስመራ ተዛውረው አንዳንድ አይሮፕላን ተሰጣቸውና የጥገና ሥራው





በአዲስ መልክ ተጀመረ። ደረጃ በደረጃም የአይሮፕላን አደጋ ተቀነሰ፣ ከሞላ ጎደልም ጠፋ። የዚህም ውጤት ዋና ምክንያት የሚከተለው ነው።

1. የአድማው ምክንያት በትክክል ታውቆ ማለትም የቢ-17 አይሮፕላን ጥገና የቴክኒክ አቋም በሕይወት ላይ አደገኛ ሁኔታ መፍጠሩ ስለተረጋገጠ በአስቸኳይ እንዲታረም በግርማዊ ጃንሆይ ጥብቅ ትእዛዝ ተሰጠበት።

2. በአጋጣሚ በአየር ኃይል አይሮፕላን ምሕንድስና ት/ቤት ከአራት ዓመታት በላይ በአይሮፕላን ቴክኒሺያንነት ሰልጥነው በዚህ ወቅት ተመርቀው ወደ ሥራ ሊሰማሩ ተዘጋጅተው የነበሩ ኢ-2 የተባለው ኮርስ ምሩቃን በቢ-17 አይሮፕላን ላይም በቂ ትምህርትና ልምምድ ተሰጥቷቸው ስለነበረ በስዊድናዊው መሐንዲስ መሪነት በአስቸ ኳይ ወደ አስመራ ተልከው በኃላፊነት በየአይሮፕላኑ እንዲመደቡ ተደረገ።

እነዚህ ምሩቃን በትልቅ ሀንጋር (የአይሮፕላን መጠለያ) ውስጥ ታሽገው የነበሩት አይሮፕላኖች ተሰጥተዋቸው በተማሩት የቴክኒክ ትምህርት መሠረት አንድ በአንድ በመፈተሽ፣ እንከኑን በዝርዝር በመመዝገብ፣ የጥገና እቅድ በማውጣትና የጥገናና የመለዋወጫ ዕቃ በማቅረብ ተዘጋጅ ተው ሥራ ጀመሩ። ሰፋ ላለ ጊዜ ጠለቅ ያለ ጥገና ሲያከናውኑ ከቆዩ በኋላ ሥራቸው የተጠናቀቁ አይሮፕላኖች ለፍተሻ ቀረቡ። ፈታኝ ፓይለት ታዝዞ የተዘጋጁት አይሮፕላኖች አንድ በአንድ ወደ አየር እየወጡ በልዩ ልዩ በረራ ስልት በረራቸው እየተረጋገጠ በሰላም አረፉ። በዚህ ጊዜ እርካታው ሁለገብ ሆኖ ተገኘ። በቴክኒክ ችግር ምክንያት አደጋዉ ያስመረረው ፓይለትና የሬዲዮ ኦፕሬተር ክፍል ባደረገው አድማ ቆመው የነበሩት አይሮፕላኖች የመብረራቸው ውጤት ሲያስደስት አደጋው እንደተ ወገደላቸው ተጨባጩ ሁኔታ በዐይናቸው ያዩት ፓይለቶች እጅግ ረኩ። ከዚህ ባላነሰ ደግሞ የቴክኒክ ትምህርታቸውንና ችሎታቸውን በሥራ ላይ ውሎ ያዩት አዲሶቹ የኢ-2 ምሩቃን ቴክኒሺያኖች በእንከን ምክንያት ተገልሎ ሀንጋር ውስጥ ታጉሮ የነበረውን ቢ-17 አይሮፕላን መርምረው ስህተቱን አግኝተው፣ ጠግነውና ደህንነቱን አረጋግጠው ለበረራ በማብቃት እንደገና ለግዳጅ ዝግጁ በማድረጋቸውና አስተዳደሩንና ፓይለቶቹን በማርካ ታቸው በይበልጥ ተደሰቱ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በቢ-17 አይሮፕላን ላይ የነበረው ጥላቻ አብቅቶ በሰማይ ላይ ሲያጓራ እንደ ድሮው «ገብሬ ባለ ሞላሌ መጣ» ይባል ጀመር።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ለስምንት ዓመታት እያዘገመ ይራመድ የነበረው የኮሎኔል ቮን ሮዘን አመራር በስዊድን መንግሥት ጥያቄ ሳይሆን አይቀርም ለመጀመሪያ ጊዜ በ1952 ዓ.ም በጡረታ ላይ የሚገኙ አንድ የስዊድን አየር ኃይል ጄኔራል ላከ። እኚህ በዕድሜ ገፋ ያሉት ጄኔራል ሆርድ ከገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ ከሚገኘው የጽሕፈት ሚኒስቴር አንድ ቢሮ ተሰጥቷቸው በቆዩበት ጊዜ፣ በየጊዜው በጀት በሚፈቀድበት ስብሰባ ከመገኘት አልፈው ለአየር ኃይሉ ጉልህ የሆነ፣ ይህ ነው የሚባል ሥራ ሳይሠሩ ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል።

በየጊዜው ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር ያለውን ግንኙነት ለማከናወንና በጀት ለማስፈቀድ እንዲሁም በየመሥሪያ ቤቶች እየተዘዋወሩ የአየር ኃይሉን ጉዳይ አዲስ አበባ ውስጥ ለማስፈጸም መንገድን ጨምሮ በቂ የመገናኛ ዘዴዎች ባልነበሩበት ጊዜ አቶ ታደሰ ምህረቱ፣ አቶ አስፋው ወልደ ጊዮርጊስና አቶ እውነቱ ሞላ በቀን በቀን የነበራቸው ጉዞ አድካሚ መሆኑ ይታወሳል። አቶ ታደሰ ምህረቱ የፋይናንስ ክፍሉን ከመጀመሪያ ጀምረው ከፍተኛ ደረጃ አድርሰዉታል። እሳቸው የአየር ኃይሉ የፋይናንስ መምሪያ ኃላፊ ሆነው በሚኒስትር ደኤታ ደረጃ ተሹመዋል። መኮንኖችንም በማሳተፍ እንደ ኮ/ል እስጢፋኖስ ቡሽንና በርሄ መስፍን በሂሳብ ክፍል ከፍተኛ ደረጃ ደርሰዋል።

ኮሎኔል ቮን ሮዘን እንደገና አየር ኃይሉን ለሦስት ዓመታት ከመሩ በኋላ የመጡት ጄኔራል ኒልሰን አጭር ተመም ያሉ ቆፍጣና ወታደር ነበሩ። ገና ሥልጣን እንደተረከቡ «እኔ የስዊድን መንግሥት የላከኝ ጄኔራል ነኝ» በማለት አዳዲስ ቆራጥ ውሳኔዎችን በመወሰን ወታደርነታቸውን አሳይተዋል። ለምሳሌም ያህል ቀደም ባሉት የስዊድን አዛዦች ማለትም በካዉንት ቮን ሮዘንና በጄኔራል ሆርድ ጊዜ በሲቪልነት በልዩ ልዩ ሙያዎች ከስዊድን የመጡ ተቀጣሪዎች ሁሉ እንደ ዕዉቀታቸው መጠን ከመቶ አለቃ እስከ ኮሎኔል ማዕረግ ድረስ እየተሾሙ ተራ የሲቪል ሥራቸውን ይሠሩ ነበረ። ጄኔራል ኒልሰን ግን ሥራቸውን ጀምረው ይህን ሁኔታ ካጠኑ በኋላ አንድ ቀን ሁሉንም የስዊድን ተወላጆች ሰብስበው «ከዛሬ ጀምሮ ወታደርና ሲቪል ተለይቶ ሁሉም በየመልኩና በሥራ ሙያው ተግባሩን ያከናውናል፤ ስለዚህም ወታደር ያልሆናችሁና የመኮንን ማዕረግ የለበሳችሁ ሲቪል ስዊድኖች ማዕረጋችሁን አሁኑኑ አውልቁ» ብለው በማዘዛቸው ሁሉም ከትከሻው ማዕረጉን እያወለቀ የተለመደ የሲቪል አቋሙን ሊይዝ በቅቷል። በሄዱበት ስፍራ ሁሉ ኮስተር ቆፍጠን ብለው ወታደራዊ ስርአት ስለሚያስከብሩ፣ «ጄኔራል ኒልሰን መጡ» ሲባል ሁሉም የሥነ ስርአቱ ሁኔታ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ግራ ቀኝ ማማተርን እንደ ልማድ አድርጎት ነበር።





ሌላው የጄኔራል ኒልሰን ትዝታ ያላንዳች ይሉኝታ ለፓይለቶች በተለይም ፒ-7 ለተባሉት የፓይለት ኮርስ አባላት ያላቸው አድልዎ ነው። ፊት ለፊት "My boys" (የኔ ልጆች) በማለት ልዩ እንክብካቤ ስለሚያደርጉላቸው ፓይለቶቹ በዐይን ባይታዩም አንድ ስንዝር ያህል ከመሬት ከፍ የማለት ስሜት እንደነበራቸው በአካባቢው የነበሩ የሌላ ኮርስ ጓደኞቻቸው ይመስክራሉ። ፒ-7 እሳቸው እንደመጡ የተካሄደ የፓይለቶች ኮርስ ነበር።

ጄኔራል ኒልሰን ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አጭር የበጀት ሪፖርት ነሐሴ 4 ቀን 1948 ዓ.ም አቅርበዋል። በጊዜው አየር ኃይል ለመከላከያ ሚኒስቴር ካቀረበው በጀት 5,000,000 ብር ብቻ ስለፈቀደ በአሠራር ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ሁኔታ እንደሚከተለው አቅርበው ነበረ።

| | |
|---|---|
| 1. የተለመደው የሥራ ማስኬጃ | 5,828,000 ብር |
| 2. ሦስት ቫምፓየሮች ለመግዛት | 1,300,000 ብር |
| 3. ድሬዳዋና ቢሾፍቱ ማስተካከያ | 1,200,000 ብር |
| ድምር......... | 8,328,000 ብር |

በሥራ ላይ ያሉት አይሮፕላኖች አሮጌ ከመሆናቸው የተነሳ የመለዋወጫ ዕቃዎች አያገኙም። የቀረበው በጀት የማይፈቀድ ከሆነ፣

1. የበረራ ትምህርት ቤት ይቋረጣል፣
2. የአጥቂ ክፍል ሦስት ከመሆን ወደ ሁለት ይወርዳል፣
3. የመብረሩ ሥራ ስለሚቀነስ አገልግሎት ላይ ያለው የሠራተኛ ቁጥር ይቀነሳል። ድንበር ከማስከበር አልፎ በልዩ ልዩ መልክ ለመንግሥት የሚሰጠውን አገልግሎት ለመቀጠል፣ ባነሰ ወጪ ይሠራ ብሎ በጀቱን መቀነስ እጅግ የሚያሳዝን አሠራር ነው።»

በተጨማሪም፣ «ኢትዮጵያን በሚያህል ሰፊ የሆነ መሬት ባላት፣ ሕዝቦቿ ዘርዘር ብለው በሚኖሩባትና የየብስ ጎዳናዎች በጣም ባነሱበት ሀገር ረጅም የሆነውን ጠረፍ ለማስከበር፣ አየር ኃይሉ የምድር ጦሩን ከቦታ ቦታ ማመላለሻ አይሮፕላን የለውም። አየር ኃይል ከሚያስፈጽማቸው ሥራዎች ጋር በተያያዘ የቴክኒሺያኖች ማሰልጠኛ የሚሆን ለሚመጣው ዓመት ተጨማሪ 500,000 ብር እንደሚያስፈልግ» አመልክተዋል።

በድሬዳዋ የአየር ኃይልን ፍላጎት የሚያሟላ የጄት አይሮፕላን ማረፊያ እንዲዘጋጅ የጣሩትና ያስፈጸሙት እኚህ መኮንን ናቸው። ስዊድኖች የተጠቀሙበትን ቫምፓየር አይሮፕላን ለኢትዮጵያ አየር ኃይል እንዲገዛ የኢትዮጵያ መንግሥትን ለማገባባት ሞክረዋል።

ከጄኔራል ኒልሰን ቀጥለው የመጡትና አየር ኃይሉን ለኢትዮጵያውያን ሙሉ በሙሉ አስረክበው ወደ ሃገራቸው የተመለሱት የመጨረሻዉ ስዊድናዊ ጄኔራል ሊንዳል ናቸው:: በዚህ ጊዜ የነበሩ የውጭ ሀገር ተወላጆች የሚከተሉት ናቸው::

**<u>አስተዳደር</u>**

| | | |
|---|---|---|
| ኬ ሊንዳል | ኤ. ሩቢን | ቮን ታፓቪዛ |
| አይ ዊላንደር | ኤሪክሰን | ኬ ሳገርማርክ |
| ጂ ዘተ ርክቪስት | ኤል ጄሊን | ዩ ኤግሆርን |

| | |
|---|---|
| ቢ. ጆንሶን | ኤም ቢ. ዞርን |
| ጄ ፕራይስ | አይ ታፓቪዛ |

| **<u>ሕንፃ ክፍል</u>** | **<u>በረራ ትምህርት ቤት</u>** |
|---|---|
| ኤም ጎደኬ | ኬ ቴልኒንግ |
| ጂ. ላርሰን | |

| **<u>ትራንስፖርት</u>** | **<u>መኪና ጋራዥ</u>** |
|---|---|
| ሲ. ጄ ስሚዝ | ኤፍ ዴፍነር |
| ኤስ አህማን | |

| **<u>ቴክኒክ ት/ቤት</u>** | **<u>አይሮፕላን ጥገና</u>** |
|---|---|
| ኦ አፍ ስትሮም | ኤ ሀግስትሮም |
| ቤነት | ሲ.ኢ. ለስትሬል |
| ኤም ኤድ | ኤ ችኤክባል |
| ቢ. ኤክበርግ | ጂ. ሄድክቪስት |
| ጂ. ኢንሽ | ኤን ኦ ሂልባሪን |
| ኤን ፋካርበርግ | ቢ. ጆሐንስን |
| ኢ. ሆግበርግ | |
| ጆ ካርልስን | |
| ቢ. ላርሰን | ኤ ጆንግሊን |
| ቢ. ኦቲንካር | ኤስ ናአስ |
| ኢን ስታህር | ሲ. ፒተር |
| ቢ. ሮዘንክቢስት | ሲ. ራህም |
| ኤምቢ. ኦቲንካር | ኤስ ራህም |





| **<u>ሞተር ክፍል</u>** | **<u>ሬድዮ ኤሌክትሪክና መሣሪያ ክፍል</u>** |
|---|---|
| ቢ. ቶርን | ኤስ ቶሬስን |
| ቢ. ብሪደርማን | ኬ ኢግወርን |
| ቢ. ዳንቢሪንክ | ኬጂ. ጆንስን |
| ኬ.ጄ. ግሪፕ | ኤል ጂንግሬን |
| ፍርሆም | ኤን ኢ. ኒልስን |
| ኬ ጄ ጃኮብስን | ቢ. ቬንርክቪስት |
| አር ካርልስን | ኬ.ኢ. ኤበርግ |
| አር ላርስን | |

| **<u>ዕቃ ግዢ ክፍል</u>** | |
|---|---|
| ጂ. ማርቲዝ | ቲ ማየር |
| | ኢ. ማየር |

ለአየር ኃይል የመጡት ስዊድኖች ጠቅላላ 225 ሲሆኑ፣ በሥራ ወንዶች 93፣ ሴቶች 5፣ ቤተሰብ ሴቶች 58 እንዲሁም ሕፃናት 69 ነበሩ::

## <u>ጄኔራል አሰፋ አየነ</u>

በመጀመሪያ የአየር ኃይል አገናኝ መኰንን የነበሩት አምባሳደር ለገሰ ወልደሐና (ሻለቃ) በምሥረታው ብዙ ተሳትፈው የበረራ ትምህርት ጀምረው ሳይጨርሱ በሹመት ወደ ሌላ መሥሪያ ቤት ተዛውረዋል:: አምባሳደሩ በዚያን ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ በቪዲዮ ፊልም የተቀረጸ ሰፊ ገለጻ አድርገዋል::

ሌተና ጄኔራል አሰፋ አየነ በሻለቃነት ማዕረግ አገናኝ መኰንን ሆነው መጋቢት 23 ቀን 1939 ዓ.ም ወደ አየር ኃይል ተዛወሩ:: በዚህ ዘመን ተቀጥረው የበረራ ትምህርታቸውን መከታተል ከጀመሩት ከሁለተኛ ኮርስ ፓይለቶች ጋር እንደ አንዱ ተማሪ ሆነው የበረራ ትምህርታ ቸውን አጠናቀው የአብራሪ ክንፍ ተቀበሉ:: ከዚያም ደረጃ በደረጃ የበረራ ትምህርታቸውን ቀጥለው እስከ ከፍተኛ የጦር አይሮፕላኖች አብርረዋል::

በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ስለ እስራኤላውያን ስቃይ ሚስተር አርመን ቮን ሩን «The Holocaust» በሚል ርዕስ ባቀረቡት መጽሐፍ የአሜሪካ


ጦር ያሳየው ጀግንነትና ጦርነቱን በተሳካ ሁኔታ ለመወጣት የቻለው፣ ፕሬዚዴንት ሩዝቬልት የነበራቸው የጦሩ ጠቅላይ የበላይ አዛዥነት ስልት፣ ፖለቲካው ላይ በማተኮር የጦርነቱን አመራር ሙሉ በሙሉ ለጄኔራሎቻቸው አምነው በመተዋቸው ነው ብለው ያምናሉ። ይኸውም በመጀመሪያ አመራረጥ ላይ ልዩ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። አንድ ጊዜ ከተመረጡ በኋላ መስመር ላይ ያፈገፈጉትን እንኳን ማበረታታት እንጂ እንዲለወጡ አላደረጉም። ለአሸናፊዎቹም ጠቅላላውን የጀግንነት ክብር በግለሰብ ደረጃ ለሚገባቸው እንዲያገኙ ተደርጓል። በመጀመሪያ የነበረው ቡድን ፕሬዚዴንት ሩዝቬልት ከሞቱም በኋላ እስከ ጦርነቱ ማብቂያ እነዚያው ነበሩ ብለዋል።

የኢትዮጵያ አየር ኃይል ከበረራ ትምህርት ቤት ደረጃ ተነስቶ እስከ ከፍተኛ የጦር ኃይል ለመሆን የበቃው ዋነኛው ምክንያት በየጊዜው ተለዋዋጭ የበላይ አዛዥ መኰንኖች ሹም ሽር ያልነካውና በሰከነ የአመራር ዘዴ ከሌተና ጄኔራል አሰፋ አየነ ጋር አብሮ በማደጉ ነው ለማለት ከላይ የተጠቀሰውን የጦር አዛዦች ምሳሌ ለዚህ ተግባር ማቅረቡ ተገቢ ነው። ሌላው አየር ኃይሉን ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው ካደረጉት ምክንያቶች ዋነኛው፣ ከተመሠረተበት ዘመን አንስቶ ከፍተኛ ጉዳዮቹን የሚፈጽመው የበላዮችን አልፎ በቀጥታ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ግንኙነት ስለነበረ ነው። ይህ የአሠራር መሥመር ወደኋላው ዘመን ሌተና ጄኔራል አሰፋ አየነ የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም ሆነው ሲሾሙ የአየር ኃይል ጉዳይ እንደ ሌላው ክፍለ ጦር በሳቸው በኩል አልፎ መታየትና አስፈላጊዎቹ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ መቅረብ የነበረባቸው ጉዳዮች ቀድሞ እንደተለመደው በቀጥታ በአዲሱ የአየር ኃይል አዛዥ መቅረባቸው ሳያሳዝናቸው አልቀረም።

ሌተና ጄኔራል አሰፋ አየነ አገናኝ መኰንን ከነበሩበት ጊዜ አንስቶ የግል ምርምርና ጥናት በማድረግ፣ በመጠየቅና በማንበብ በተገኘ ሃሳብ አየር ኃይሉን በተቻለ መጠን ወደመጠቀ ዘመናዊነት ደረጃ እንዲደርስ ልዩ የግል ጥረት ያደርጉ እንደነበር ይታወቃል። የምዕራባውያንን የአቪዬሽን ቴክኖሎጂ ልምድ በመቅሰም በተለይም በአየር ኃይል በኩል ብቁ የተዋጊነት ስልትና የሥነ ሥርዓት ቀረፃ አስፈላጊነት ጽኑ መሠረት እንዲኖረው እጅግ ብዙ ይጥሩ እንደነበር በቅርብ አብረዋቸው የነበሩ አባላት ያረጋግጣሉ።








ሌተና ጄኔራል አሰፋ አየነ ከመኰንኖቻቸው ጋር

ከውጭ ሀገር ምሁራን ጋር ተነጋግረው ሃሳብ በመቅሰም፣ ከሀገር ውስጥ ምሁራን ጋር በመወያየትና ሀሳብ በማሰባሰብ፤ ከአየር ኃይሉ መሪ አባላት፤ ከተማሪዎችና ከሠራተኞች ጋር በቅርብ ተነጋግሮ ልዩ ልዩ አስተያየት አሰባስቦ፤ ለመማር ለመተራረም፤ ለመሻሻል፤ በጉብኝትና በእረፍት ጊዜ ሁሉ ከኅብረተሰቡ ጋር ተገናኝቶና ተቀራርቦ በመተቻቸት ተምረው የሚያስተምሩት፤ አይተው የሚያሳዩት በጠቅላላውም በምሳሌነት የሚያስተጋቡት ትምህርት አየር ኃይሉን በትክክለኛ መንገድ በመቅረጽና በማንቀሳቀስ ታላቅ ሚና እንዲጫወቱ አድርጓቸዋል። በመሆኑም እኚህ የሀገር ቅርስ የሆኑ ታላቅ ጄኔራል መቼም ቢሆን በታሪክ ሲዘከሩ ይኖራሉ።



ሌተና ጀኔራል አሰፋ አየነ ከመኰንኖቻቸው ጋር

በበላይነት፤ አመራር በመስጠት ሲያስተባብሩ በልዩ የአመራር ዘዴ መሪ ስታፎቻቸውን ስለሚያሰባስቡና በልዩ ጥበብ በሚፈልጉት ስልት ስለሚቀርጿቸው በነዚህ ብልህ ረዳቶቻቸው እየተደገፉ የገነቡት አየር ኃይል በተከታታይ አመራሩን በተረከቡት ብቁ ኃላፊዎችና አባላት አማካይነት ለሀገር ታማኝ፤ ብቁ፤ የማይበገር ኃይል መሆኑን በተደጋጋሚ በማረጋገጡ በአንድ ወቅት ለአህጉሩ አለኝታነቱን አስመስክሯል:: ይህ በጠንካራ መሠረት ላይ የተጣለው ት/ቤት የጊዜውን የቴክኖሎጂ ጥበብ ሥርዓተ ትምህርት በመከተል ብዛትና ጥራት ያላቸውን የቴክኒክ ባለሙያዎች ከማፍራቱም በላይ በዚያን ጊዜ ለአየር ኃይሉ የጀርባ አጥንት የሆነውና በልዩ ልዩ ሙያ የተማረ የሰው ኀይል ማመንጫ ለሆነው ለ101ኛው የአየር ትምህርት ምድብ መቋቋም መሠረት ሊሆን ችሏል:: ከዚያም የልዩ ልዩ ሙያ ት/ቤቶች ማለትም የበረራ፣ የአይሮፕላንና የመኪና ጥገና፣ የኤሌክትሮኒክስ፤ የአየር ምርመራ፤ የሬዲዮ፤ የጦር መሣሪያ፤ የአስተዳደርና የማኔጅሜንት ት/ቤቶች ተቋቁመው ወጣት ኢትዮጵያውያንን ተቀብሎ በማሰልጠን በጥቂት ዓመታት ውስጥ የውጭ አገር አሰልጣኞችን በመተካት በቴክኒክ ሙያ በኩል አየር ኃይሉ ራሱን ችሎ እንዲራመድ ጠንካራ መሠረት ሆነዋል::

## <u>ስዊዝ ካናል</u>

አሜሪካና እንግሊዝ ሐምሌ 19 ቀን 1948 ዓ.ም የአስዋን ግድብን ለመሥራት የተጠየቁትን ብድር ለግብጽ እንደማይሰጡ ያስታውቃሉ:: ከስዊዝ መተላለፊያ ቦይ በሚያገኙት ገቢ የአስዋን ግድብን ለማሠራት እንዲቻላቸው ፕሬዚዴንት ጋማል አብዱል ናሰር ባወጡት አዋጅ መሠረት የስዊዝ ካናልን የግብጽ መንግሥት ወረሰ::

ጥቅምት 17 ቀን 1949 ዓ.ም እስራኤል ግብጽን በአይሮፕላን ደበደበች:: በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያ የእስራኤል ወታደራዊ አታቼ የነበሩት ዝነኛው ኮሎኔል ለኢትዮጵያ አየር ኃይል መኰንኖች ከጦርነቱ በኋላ እንዳስረዱት የሦስቱንም መንግሥታት አየር ኃይሎች መሬት ላይ እንዳሉ በአንድ ቀን ለመደብደብና የአካባቢውን አየር ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር የቻሉት፤

1. ጥሩ መረጃ ከጠላት ሀገር በማግኘታቸው በተለይ ከሲቪሉ አይሮፕላኖች ጋር ተሰባጥረው የቆሙትን የግብጽ ተዋጊ አይሮፕላኖችን ለይተው ለመምታት አስችሏቸዋል::

2. ሠራዊቱ ተገቢውን ሥልጠና አግኝቷል፤





3. ጠቅላላ የጦር ኃይሉ በቆራጥነትና በታማኝነት በመዋጋቱ የሦስቱን አቅጣጫ ጦርነት በአጭር ጊዜ በአሸናፊነት ሊወጣው ችሏል::

ከሁለት ቀናት በኋላ «ስዊዝ ካናልን እንከላከላለን የመርከብ መተላለፊያውንም ነፃ እናደርጋለን» በሚል የገላጋይነት ሚና፤ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ግብጽን ወግተው ጦራቸውን በስዊዝ አካባቢ አሰፈሩ:: ይህ ሁኔታ ያስቆጣቸው የግብጽ ወታደሮች በስዊዝ ቦይ ለመተላለፍ ተከታትለው የገቡትን አርባ መርከቦች በልዩ ጓዶች በፈንጂ በማስመጣቸው የስዊስ ቦይ ተዘጋ:: ከዚያም ጦርነቱ ቆሞ ጉዳዩ ወደ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቀረበና እንግሊዞችና ፈረንሳዮች እንዲወጡ ተደርጎ በተባበሩት መንግሥታት አስተባባሪነት ካናሉ ጸድቶ በየካቲት 1959 ዓ.ም ግብጽ የመርከብ መተላለፊያው ባለቤት መሆኗ ታውቆ የስዊዝ ካናል ለመርከቦች ክፍት ሆነ::

ግብጽ ከፍተኛውን የአስዋን ግድብን ለመሥራት የሚያስችል የኢኮኖሚና የወታደራዊ ርዳታ በብዛት ከሶቪዬት ኅብረት ማግኘት በመቀጠሏ ይህ አዲስ ሁኔታ ኢትዮጵያንና በአካባቢዋ የሚገኙትን አገሮች ስጋት አሳደረባቸው:: በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያ ከአሜሪካ መንግሥት የምታገኘው ወታደራዊ ርዳታ (እ.ኤ.አ ለ1957 ዓ.ም) ፕሮግራም የተያዘለት $554,000 የአሜሪካ ዶላር ሲሆን የአሜሪካ ኮንግሬስ እንዲያጸድቅ የሚጠበቀው የ$5,000,000 ዶላር ርዳታ ነበር:: በአሜሪካ መንግሥት በኩል ይህ ርዳታ በጊዜው ለነበረው የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ኃይል አስፈላጊ የሆኑትን የመከላከያ መሣሪያ ጥያቄዎችን ሊያሟላ ይችላል የሚል ግምት ነበራቸው::[*1]

ይህ ወቅት የግብጽ መንግሥት ለሱማሊያ የመስፋፋት ዓላማ በሃይማኖት ሳቢያ ድጋፍ የምትሰጥበትና በካይሮ ሬዲዮ የአማርኛ ፕሮግራም የምትነዛው ፕሮፓጋንዳ ያየለበት ጊዜ ነበር:: እነዚህን ሁኔታዎች በተመለከተና አገር ውስጥ ሊነሳ የሚችል ሽብር ለመከላከል የጠነከረ አየር ኃይል እንደሚያስፈልግ ንጉሠ ነገሥቱ ስላመኑበት፤ የአሜሪካ መንግሥት ርዳታ እንዲሰጣቸው በማከታተል ጠየቁ:: በተለይ የአሜሪካ ጦር አማጽያንን ተከታትሎ ለማጥፋት ቤይሩት የገባበትን ቀን ምክንያት በማድረግ ንጉሠ ነገሥቱ በቴሌግራም ባስተላለፉት መልእክት ከስድስት ወር በፊት የአካባቢው አሳሳቢነት በኢትዮጵያ የተገለጸ መሆኑን አስታውሰው ለኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ርዳታ ማስፈለጉን ለፕሬዚዴንት አይዘንሐወር ገልጸዋል::

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በስዊዝ ካናል መዘጋት ምክንያት ለአይሮፕላን መለዋወጫ ዕቃዎችና ልዩ ልዩ አላቂ መገልገያዎች ካለማግኘቱም ሌላ ኮንቬር አይሮፕላኖቹ በዋዲ ሐልፋና፣ (በአስዋን ግድብ ምክንያት አባይ ያሰመጠው የሱዳን ከተማ) ቤንጋዚ - ሊቢያ አይሮፕላን ጣቢያዎች ለነዳጅ እያረፉ ከግብጽ አየር ክልል ሳይገቡ ወደ አቴን ለመብረርና ከአውሮፓ ጋር የነበረውን ግንኙነት ለመቀጠል፣ የረጅም መንገድ በረራው ከባድ ወጪ አስከትሏል::

በተጨማሪ በአውሮፓና አሜሪካ የታደሱትን የአይሮፕላን ሞተሮችና መለዋወጫዎች ካናሉ ለረዥም ጊዜ የሚዘጋ ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባትም ሆነ እንዲታደሱም የሚላኩት መሣሪያዎች በጊዜው አለመምጣት በአየር መንገዱ ላይ ከባድ ችግር እንደሚያስከትል በመገመት በደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ የበላይ ቦርድ ፕሬዚዴንትነት የተሰበሰቡት አባሎች፤ የቴክኒክ ትምህርት ቤት ለማስፋፋትና የሞተር ማደሻ አየር መንገዱ ውስጥ እንዲቋቋም የፈቀዱት በዚህ ጊዜ ነበር::

ንጉሠ ነገሥቱ ሴናተር ቴዎዶር ፍራንሲስ ግሪንን ጥቅምት 3 ቀን 1949 ዓ.ም በቤተመንግሥታቸው ተቀብለው በኢትዮጵያና በአሜሪካ መንግሥታት መካከል ስለተፈረመው ውል ተነጋግረዋል:: በዚህ ውይይት በኢትዮጵያ በኩል የነበረው ግዴታ ተፈጽሞ ሳለ በአሜሪካ በኩል ምንም ያህል የሚያረካ ውጤት አለመገኘቱን በመግለጽ ንጉሠ ነገሥቱ በጥብቅ ያስታወቁትን፣ ሴናተር ግሪን ለፕሬዚዴንት አይዘንሐወር በሪፖርት መልክ አቀረቡ:: ፕሬዚዴንቱ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ኅዳር 3 ቀን 1949 ዓ.ም በጻፉት ማስታወሻ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ሴናተር ግሪን ያደረጉትን ውይይት በመጥቀስ አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድ ይጠይቃሉ:: ከደብዳቤውም መጨረሻ በእጅ ጽሁፋቸው «የኢትዮጵያን ወዳጅነት በከፍተኛ ደረጃ እመለከተዋለሁ» ብለው በመጻፍ ፈርመውበታል::[*2]

በተጨማሪም ምክትል ፕሬዚዴንት ኒክሰን ሌሎችንም ታላላቅ የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣኖችን አስከትለው ኢትዮጵያን በጎበኙበት ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ አየር ኃይሉን አሜሪካኖች እንዲያስለጥኑላቸው ደጋግመው ጠይቀዋቸዋል:: የነዚህ ጥያቄዎችና ደብዳቤዎች መለዋወጥ፤ የባለሥልጣኖች በጉዳዩ ማተኮራቸውና በተለይ ክቡር ፀሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ኃብተወልድ ሎንዶን ላይ ከአቻቸው ከጆን ፎስተር ዳላስ ጋር በስዊዝ ካናል መዘጋት ምክንያት በተሰበሰቡበት ጊዜ በተወያዩት መሠረት፤ አንድ አየር ኃይሉን የሚያጠና ቡድን ከአሜሪካ አየር ኃይል ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ ተደረገ::





One of the points that the Emperor seemed to make was that the United States had violated an "agreement." He emphasized this point several times. I should like to know whether we have actually been guilty of violating an agreement, no matter whether such agreement was executed before or after this Administration was inaugurated in January 1953.

I promised Senator Green that the State Department would notify our Ambassador in Ethiopia that the Senator had actually delivered his personal message to me. Will you please instruct your Ambassador to suitably inform the Ethiopian Government?

D.E.

Dwight D. Eisenhower

P.S. The friendship of Ethiopia is considered of great importance. D

### የፕሬዚዴንት አይዘንሐወር ማስታወሻ

ይህ አዲስ ሁኔታ የአሜሪካ መንግሥት ቀደም ሲል «ስለ ኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አይመለከተንም» የሚለውን አቋም እንዲለውጥ አድርጎታል::

አየር ኃይሉን ያጠናው ቡድን ነሐሴ 10 ቀን 1949 ዓ.ም ባቀረበው ሪፖርት፣ አንድ ዊንግ 36 ተዋጊ አይሮፕላኖች፣ አንድ የወታደር ማመላለሻ ትራንስፖርት ስኳድሮን፣ ስምንት አይሮፕላኖች በአራት ዓመታት ውስጥ ለማሟላት ከዚህ ቀደም ለሚሊተሪ ርዳታ ከተወሰነው 22 ሚሊዮን ብር ሌላ ተጨማሪ 12 ሚሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ አመልክቷል::

በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ሦስት ተዋጊ ስኳድሮን፣ ያረጁ የስዊድን ቢ-17፣ የእንግሊዝ ፋየር ፍላይ አይሮፕላኖችና አንድ ያልተሟላ የትራንስፖርት ክፍል ነበረው:: ይህ የመከላከያ ኃይል ደረጃ የተገኘው በስዊድኖች የ11 ዓመት የማስተማርና የአስተዳዳር ውጤት መሆኑ አይዘነጋም::

ይህ ጥናት እስከ 1951 ዓ.ም ለርዳታ የሚሰጠውን የአይሮፕላን ዓይነት በመምረጥና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ዘግይቶ ከላይ እንደ ተጠቀሰው ሊባኖስ ውስጥ የተፈጠረው ሁኔታ፣ ግብጽ የምታራምደው የመስፋፋት ፕላንና በክርስቲያኖችና በእስላሞች መካከል የተጀመረው ጠብ ኢትዮጵያን ስላሰጋት የአየር ኃይል ርዳታው እንዲፋጠን ቶደርጎ የሚከተለው ፕላን ወጣ::

1. አንድ ዊንግ ሦስት ስኳድሮን ያለው ብዙም ዘመናዊ ሳይሆን ለጥቂት ዓመታት መለዋወጫቸውን በመፈብረክ የሚቀጥሉ ተዋጊ አይሮፕላኖች፣

2. አንድ ስኳድሮን የትራንስፖርት አይሮፕላን በሲ-47 ደረጃ፣

3. 25 ምርጥ ኢትዮጵያውያን ፓይለቶች ለትምህርት ወደ አሜሪካ እንዲላኩና በጄት አብራሪነት እንዲሰለጥኑ፣

4. የፓይለቶቹ ስልጠና እንዳለቀ አንድ ስኳድሮን ተዋጊ አይሮከፕላኖች ኢትዮጵያ እንዲደርሱ በማድረግ አስፈላጊውን ውጤት ማግኘት፣
5. የጥገና ትምህርት ማካሄድ፣

6. ሌሎች የኢኮኖሚ እውታሮች እንዳይጐዱና ባለው የገንዘብ እጥረት የመንግሥት በጀት እንዳይናጋ ፕሮግራሙን ማራዘም፣ ስዊድኖች (ከስዊድኖች ወደ አሜሪካኖች ዝውውር የሚደረግበት ጊዜ ተጨምሮ) የ12 ዓመታት አስተዳደር ያስገኘው መሠረት አየር ኃይሉን በሦስት ዓመታት ከተፈለገው ደረጃ ማድረስ ይቻላል:: ይህ ፕላን ለጦር ሠራዊቱ አምስት ዓመታት፣ ለባሕር ኃይሉ 10 ዓመታት ከሚያስፈልገው ጋር ሲነፃጸር በአጭር ጊዜ የሚያኮራ ውጤት ያስገኛል የሚል ጥናት የአሜሪካ አምባሳደር ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴራቸው ልከዋል::*2

የአካባቢውን ውጥረት በተመለከተ የኢትዮጵያ ጥያቄ በአስቸኳይ ተዋጊ አይሮፕላኖችን ማግኘት በጣም አስፈላጊ ስለነበረ ከወጣው ፕሮግራም ቀድሞ እንዲሰጥ በተደጋጋሚ ለቀረበው ጥያቄ መፍትሄ ለማግኘት ተሞከረ::

የካቲት 7 ቀን 1951 ዓ.ም የተሰበሰበው ስቴት ጆይንት ቺፍስ (የአሜሪካን ከፍተኛው የወታደራዊ ጉዳይ ኮሚቴ) ለኢትዮጵያ የሚሰጠውን የአየር ኃይል ርዳታ ለኢትዮጵያ አየር ኃይል ፓይለቶች አጭር ስልጠና ተሰጥቶ፤ የአሜሪካ ስትራይክ ኮማንድ በሚባለው ዓለም አቀፍ ጸጥታ አስጠባቂ አየር ኃይል ውስጥ እንደ አንዱ ክፍል ሆኖ የአካባቢውን





ሰላም እንዲጠብቅ የተጠየቀውን ፕላን የስትራቴጂክ ኮማንድ ክፍል ኃላፊ ወዲያውኑ ውድቅ ያደርጉታል::4 የሰጡትም ምክንያት "ኢትዮጵያ ከውስጥ ጸጥታ ማስጠበቅ አልፋ አየር ኃይል አያስፈልጋትም:: በተጨማሪ የሚሰጣቸውን ጄት አይሮፕላን ጠግነው ለብዙ ዘመን ለማብረር አይችሉም» የሚል ነበረ::" ይህ አፍራሽ የሆነ የመከላከያው ክፍል አባል አመለካከት በወቅቱ ለነበረው የቅርብ ምሥራቅ የፖለቲካ ሁኔታ በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ተቀባይነት አልነበረውም:: ምክንያቱም አሜሪካኖች ሳውዲ አረቢያን፣ ኢራቅን፣ ሊባኖስንና ዮርዳኖስን በጄት አይሮፕላኖች አስታጥቀዋቸው ስለነበረ፤ እንዲያውም ለጄት አይሮፕላን የሚያስፈልገውን እንክብካቤ በፒስቶን ሞተር ከሚሠሩት ቀለል ያለ ስለሆነ ለኢትዮጵያ የሚሰጠው ርዳታ ፕሮግራም መቀጠል አለበት ተብሎ ተወሰነ::3

## የአሜሪካ ርዳታ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በየጊዜው ኢትዮጵያን ይጐበኙ ከነበሩት የአሜሪካ ከፍተኛ የጦር ኃይል አዛዦች ጋር ስለ መከላከያ ርዳታ ጉዳይ እያነሱ ተወያይተዋል:: በዚህም መሠረት በጄኔራል ትሩዶ፣ ጄ. ኩክና አድሚራል ኩዊን በኩል ማስታወሻዎች ተልከው የአሜሪካ መንግሥት አስተያየት ምን እንደሆነ የሚገልጽ አንዳችም መልስ አልተገኘም ነበር1::

በዚህ ጊዜ የአሜሪካ መንግሥት ለኢትዮጵያ የነበረው ፖሊሲ፤ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የአሜሪካ ማስታወቂያና ባሕል ልውውጦች ማጠናከር ነበረ:: አትዮጵያም ባላት የምዕራቡ ርእዮተ-ዓለም እንድትቀጥል የተፈለገው:-
1. ትምህርት ላይ የሚያተኩር ርዳታ በመቀጠል፣
2. የተወሰነ ኢኮኖሚያዊ ርዳታ መስጠቱ ቀጥሎ፣
3. አነስተኛ ወታደራዊ መሣሪያ ርዳታ የምታገኘው ያገር ውስጥ ጸጥታን ለማስከበር የሚያስችል ሆኖ ወደ ከፍተኛ መሣሪያ ክምችት እንዳይዛመት ጥንቃቄ ማድረግና የሀገሪቱን ምጣኔ ሀብት እንዳይጎዳ መጠንቀቅ፣ ለማንኛውም የጦር መሣሪያ ርዳታ በየጊዜው ወደ አሜሪካ እንዳትመለከትና የአካባቢውም ሰላም እንዳይናጋ መታሰብ አለበት የሚል ነበረ::

በዚህ ጊዜ አካባቢ ሚስተር ሚላን ፒስክ የሚባሉ የቼኮዝሎቫኪያ ተወላጅ አዲስ አበባ ከሚገኘው የጥይት ፋብሪካ ሠራተኛ ሆነው ያገለ

ግሉ ነበር። እኚህ ሰው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ልዩ ግንኙነት ነበራቸው። ይኸውም አንድ አነስተኛ የጦር መሣሪያ ፋብሪካ አገር ውስጥ ለማቋቋም የሚቻልበትን ፕላን በየጊዜው እያቀረቡ ይነጋገሩበት ስለነበር ነው። ፋብሪካውን ለማቋቋም የሚያስፈልገው 10,000,000 ብር ($400,000) በመሆኑ ለዚህ ፋብሪካ የሚያስፈልገውን ወጪ ብቻ ሳይሆን ለአንዳንድ መሣሪያዎችና የአመራር ርዳታ ከቼኮዝሎቫኪያ እንደሚገኝ ተስፋ ተጥሎበት ሳለ ባልታወቀ ዘዴ ሚስተር ፒስክ ወደ አሜሪካ ሄደው ጥገኝነት ያገኛሉ።[3]

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጆን ፎስተር ዳለስ ኅዳር 7 ቀን 1949 ዓ.ም "የአየር ኃይሉን ችሎታ የሚያጠና ኮሚሽን እንልካለን። ይህን ስላደረግን ግን የአሜሪካ መንግሥት ለኢትዮጵያ አየር ኃይል ርዳታ ያደርጋል ተብሎ ግዴታ የሚያስገባው አይደለም" ብለው ያስታውቃሉ። የተባለው ኮሚሽን ሳይላክ ስድስት ወር ያህል ቆይቶ በኮሎኔል ዊልያምስ የሚመራ ቡድን በሚያዝያ ወር ይመጣል። የጥናት ኮሚሽኑ ከመምጣቱ ጥቂት ሳምንታት ቀደም ብሎ ምክትል ፕሬዚዴንት ኒክሰንና አምባሳደር ሪቻርድስ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት መጥተው ስለነበረ ስለ እርዳታው ተጠይቀው ሪቻርድስ ሲመልሱ፤ ከሦስት ዓመት በፊት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ሚስተር ባይሮንድ የሰጡትን መልስ ደገሙት፤ «ርዳታው አልተፈቀደም።»

በጊዜው በሳውዲ አረቢያና በየመን መንግሥታት መካከል የተፈጠረው አስጊ ሁኔታ የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታ ምክር ቤት እንዲነጋገርበት ኢትዮጵያ ጠይቃለች። እንደዚሁም በምሥራቅ በኩል የምትገኘውና የኢትዮጵያ ጎረቤት የሆነችው አገር ሶማሊያ ለመከላከያዋ 30 T34/85 ታንኮች፣ 55 አውቶማቲክ ጸረ አይሮፕላኖች፣ 50-100 መድፎች፣ 30 ብረት ለበስ መኪናዎች፣ 100 ብረትለበስ የወታደር ማጓጓዣዎችና 50 ጸረ ታንክ መድፎች ነበሯት።

በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ከዚህ ቀደም ሲል በተገለጸው ሁኔታ ላይ መገኘቱ፤ አስጊ ሁኔታ ተፈጥሯል። የቶጎ ውጫሌ ጦርነት በዚህ ጊዜ አካባቢ ነበረ። ኢትዮጵያ በጠረፎቿ ዙሪያ አስጊ ወደሆኑ ሥፍራዎች ወታደሮቿን ለመላክ የሚያስችላት በቂ የትራንስፖርት

አይሮፕላኖች የሏትም። በሥራ ላይ ያሉት አንድ ሲ-47 እና አንድ ስባት ሰው የሚይዝ ዴሐቪላንድ ዳቭ፣ ለሚያስፈልገው ሥራ በቂ አይደሉም። ቢ-17 እና ፋየር ፍላይ አይሮፕላኖች የመለዋወጫ መሣሪያ





ስለማይገኝላቸው ርዳታ ካልተገኘ በአንድ ዓመት ውስጥ የተዋጊ ክፍል የተባለውን መዘጋቱ ግድ የሆነበት ጊዜ ነበር። የተዋጊው ክፍል ሲዘጋ በ14 ሣፊር አይሮፕላኖች ይካሄድ የነበረው የበረራ ትምህርትም አብሮ መዘጋት ይኖርበታል።


አሥራ ሁለት ዓመታት ተደክሞበት፣ ብዙ ሚሊዮን ብር ፈስሶበት፣ የብዙ ዘመን ትምህርትና የሥራ ልምድ የተገኘበትና ለአየር ኃይሉ የሚያስፈልጉት ድርጅቶችና የአይሮፕላን ጣቢያዎች ተሠርተው ወደፊት የሚያድግበት ጽኑ መሠረት ከተቋቋመ በኋላ፣ ምንም ርዳታ ሳይደረግለት ቢቀር፣ ይህ ሁሉ ድካምና ገንዘብ ከንቱ ሆኖ መቅረቱ ስለሆነ የአሜሪካ አምባሳደር ለነበሩት ሚስተር ብሊስ የአየር ኃይሉን በተመለከተ ዝርዝር ማስታወሻ ይላካል።

ከዚህ በኋላ እ.ኤ.አ. በ1960 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ከአሜሪካ መንግሥት ጋር ሁለት ውሎች ተፈራርሟል። አንደኛው ኢትዮጵያ ለአሜሪካ መንግሥት የጦር ሠፈር የመስጠት ውል ሲሆን፣ ሁለተኛው ለኢትዮጵያ የሚሰጠው ጠቅላላ የወታደራዊ ተራድኦ ስምምነት ነበረ። በእነዚህ ውሎች መሠረት አሥመራ የሚገኘው (የቃኘው) የአሜሪካ የመገናኛ ጣቢያ ሥራውን ይቀጥላል። ማግ ("MAAG") የተባለው የአሜሪካ ወታደራዊ ተራድኦ ቡድን አስተማሪዎችንና የጦር መሣሪያዎችን ለጦር ሠራዊቱ በየጊዜው እያቀረበ የማሻሻሉ ፕሮግራም ቀጠለ።

### አየር ኃይል የተመደቡት የአሜሪካን ተራድኦ ፕሮግራም መኰንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኮሎኔል | ሮበርት ኤል | ራምዚ | ዋና አማካሪ |
| ሌ/ኮሎኔል | ሒንሪይ ጂ | ቪክትር | አፕ.የትም.ክፍል |
| ሜጀር | ጀምስ ኤፍ | ኪኒይ | ትምህርት ክፍል |
| " | አሻዲ ዲ | ማብሪይ | ቴክኒክ አማካሪ |
| " | ጆሴፍ ኤፍ | ፐሪጋ | መገናኛ |
| " | አልቪን ኢ | ዩልቪክ | ጥገና |
| ም/የሃምሳ/አ | ቻርሊ አር | ዴል | የዕቃ ክፍል |
| ቴ/ " " | ሬይሞንድ ኤፍ | ጀምስ | አይሮፕላን ጥገና |
| ቴ/ " " | አንቶኒ ኤ | ፓጋልቢኪ | |
| የሃምሳ/አ | ኢውግን | ግጀር | ሬድዮ ኦፕሬተር |
| " " | ኦመር አይ | ማቲይስ | ፀሐፊ |
| " " | ሮጀር ቢ | ኦልሰን | የአስተዳደር ረዳት |

አሜሪካኖች አየር ኃይሉን ማሠልጠን በጀመሩበት ጊዜ የነበሩት የስዊድን ተወላጆች፣ ከአየር ኃይል አዛዥ ጄኔራሉና ከጥቂት መኰንኖች በቀር ሁሉም ሲቪሎች ስለነበሩ አዲስ ለሚመጡት አይሮፕላኖች የሥልጠና ትምህርት፣ ስዊድኖቹ ከበታቾቻቸው ጋር በአንድነት ይጀምራሉ የሚል አቋም ወስደው ነበር:: በተጨማሪ ማንኛውም ዓይነት የውጭ አገር ሥልጠና የሚሰጠው ለኢትዮጵያውያን ብቻ ይሆናል የሚል ነበረ::



የአሜሪካና የኢትዮጵያ አየር ኃይል መኮንኖች

ስዊድኖቹ ይዘዋቸው የነበሩት ቁልፍ የሆኑት የአመራር ክፍሎች በኢትዮጵያውያን ለመተካት ሁለት ዓመታት ያስፈልገዋል የሚል ግምት ነበረ:: ነገር ግን ቀጥሎ እንደምንመለከተው ኢትዮጵያውያኖቹ በሥልጠናው ላይ የተሻለ ውጤት እያመጡ ከአሜሪካኖቹም ጋር የተሻለ መግባባት ተፈጥሮ ስዊድኖቹ አንድ ባንድ እየሄዱ ከታሰበው ሁለት ዓመታት ባነሰ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ሥራውን በቀጥታ ተረከቡት::





# ወደ ጄት ሽግግር የአይሮፕላን ጥገናና የቴክኒክ ክፍሉ ተከታታይ ዕድገት

መሠረታዊ የሆኑ የቴክኒክ ትምህርቶች በቴክኒክ ት/ቤቶች ለመጀመሪያው አንድ ዓመት ተኩል በአጠቃላይ ሲሰጥ ይቆይና ወደ መጨረሻው ባሉት ጊዜያት በተወሰኑ አይሮፕላኖች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት ትምህርቱ ይፈጸማል:: ሠልጣኞችም እንደየችሎታቸውና ዝንባሌያቸው በአይሮፕላን፣ በሞተር፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በኤሌክትሪክና በመሣሪያዎች ጥገና እንዲሁም በሌሎች ሙያዎች ትምህርታቸውን ተከታትለው ሲያበቁ በየሥራ መስካቸው ይመደባሉ::
ተመራቂዎቹ በየሥራ መስኩ ከተመደቡ በኋላ ሥራቸውን ያከናውናሉ የሚል ግምት በቀድሞ አሠልጣኞች ዘንድ ይኑር እንጂ ብዙዎቹ ተመራቂዎች ሥራውን ለመከታተልና ለመሥራት ረጅም ጊዜ እንደሚፈጅ በበላዮቹ ዘንድ ይታወቅ ነበረ:: በተለይ በአንዳንድ የሥራ መስኮች፤ ለምሳሌ እንደ ሞተርና የሞተር ረዳት አካላት እደሳና ጥገና ላይ የተመደቡ ተመራቂዎች ዋናውን ጠንቅቆ ለማወቅ ከአምስት እስከ አሥር ዓመታት ያሳልፉ እንደነበር ይታወሳል:: ይህም የጊዜ መጓተት ምክንያት የሆነው የቴክኒክ መጻሕፍት ባለመኖራቸው እንጂ የተመዳቢዎች የማንበብና የመረዳት ችሎታ ማነስ አልነበረም:: እንዲያውም ተመዳቢዎቹ ባዩትና በሰሙት ብቻ መልካም የሥራ ውጤት ያሳዩት ጥቂት አልነበሩም:: በእነዚህ ጥቂት ሰዎች ዕውቀትና ጉልበት ጠቅላላ እድሳት የተደረገላቸው የሲ-47፣ የቢ-17፣ የሣፊር ሞተሮች በጣም ብዙዎች ናቸው:: የኢትዮጵያ አየር መንገድም የሲ-47 ሞተሮች (R-1830) የተባለውን ወደ አየር ኃይል እየላከ ያሳድስ እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው::

እ.ኤ.አ. ከ1955 እስከ 1957 ባሉት ጊዜያት የአቪዬሽን ቴክኖሎጂ በከፍተኛ ደረጃ እየመጠቀ ባለበት ወቅት ብዙ ሀገሮች የዚህ ቴክኖሎጂ ተካፋይ እንደሆኑ ሁሉ በአሜሪካ ተራድኦ ፕሮግራም አማካይነት አዲስ የጄት ቴክኖሎጂ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ተደረገ:: በፕሮግራሙ መሠረት በ1958/59 ዓ.ም ቲ-33 የተባሉ ጄት የመማሪያ አይሮፕላኖችን ከበረራ አስተማሪዎችና ከጥገና ሠራተኞች ጋር የያዘ አንድ ልዩ የአሜሪካኖች ቡድን ደብረ ዘይት፣ ሐረር ሜዳ ይዞ መጣ::
ይህ ቡድን በደረሰ በሁለተኛው ሳምንት ሌላ የትምህርት ቡድን የቴክኒክ መጻሕፍት፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች (Training Aids) ሞክ አ-ፕ (Mock Up) ይዞ መጣ:: የዚህ ቡድን ዋና ተግባር ስለ ቲ-33 ዋና



የአሜሪካና—የኢትዮጵያ አየር ኃይል መኮንኖች

ዋና ሲስቴም (System) የማስተዋወቅ ትምህርት በመስጠት ተጠቃሚ ሀገሮችን በአቪዬሽን ቴክኖሎጂ የዕውቀት አድማስ ማስፋት ነው። አየር ኃይልም ይህን ቴክኖሎጂ በጉጉት ይጠብቀው ስለነበር በየሥራ መስኩ የተሠማሩትን ባለሙያዎችና የቀድሞ አሠልጣኞች (ስዊድኖች) በአንድነት እንዲሳተፉ አደረገ። ቡድኑም የትምህርት መርጃዎችን እየተጠቀመ በሚገባ አስተምሮና ፈትኖ የያንዳንዱን ተሳታፊ ውጤት በይፋ ባስታወቀበት ወቅት፣ በኢትዮጵያውያን ተሳታፊዎች ዘንድ ታላቅ የሆነ የመንፈስ እርካታ ታየ። በአንፃሩ የቀድሞ አሠልጣኞች በአንድ የሥራ መስክ ብቻ ሳይሆን በአምስት የሥራ መስኮች በጣም ዝቅተኛ ውጤት በማምጣታቸው ለ50 ዓመታት የመቆየት ዓላማም ሆነ ተምሮ የማስተማር ተስፋ በዚሁ ያበቃለት መሆኑን ተገንዝበው ቀስ በቀስ ከኢትዮጵያ እየወጡ ወደ ሀገራቸው ሄዱ።

የማስተዋወቅ ትምህርት እንዳበቃ "የሥራ ላይ ትምህርት" በአሜሪካኖች ተቆጣጣሪነት ወዲያውኑ ተጀመረ። የዚህ ትምህርት ዋና ተግባር የጥገና አገልግሎት ተሳታፊዎች በትምህርት ቤት ያገኙትን ዕውቀት በአጭር ጊዜ ውስጥ በሥራ ላይ እንዲተረጉሙት ማስቻል ነው።

ሁለትና ሦስት የጥገና ተሳታፊዎችን በአንድ የቡድን መሪ ስር በመመደብ፣ ለአይሮፕላኑ በተዘጋጀ የጥገና መጻሕፍት እየተመሩ፣ የታዘዙትን ሥራ በመሪው ተቆጣጣሪነት መሥራታቸው የዕለት ተዕለት ተግባራቸውን እንዲወጡ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል። ይህ "የጥገናን መጻሕፍት" ተከትሎ የመሥራት ዘዴ ቀድሞ የሌለ፣ ከአሜሪካኖች መሣሪያ ጋር የመጣ አዲስ ክስተት ነበር። የጥገና ሥርአትን መልክ ለመስጠትና የጠለቀ ዕውቀት ለቴክኒሺያኖቻችን ለማስጨበጥ ታስቦ በጥንቃቄ የተዘጋጀ ፕላን ስለነበረ ጥቅሙ በማንኛውም ደረጃ የተመደበ የጥገና አባል ቋሚ መመሪያ ሆኖ ለብዙ ዓመታት አገልግሏል። የመጻሕፍቱ ዋና ይዘት በየዕለቱ ፍተሻዎችን ከማከናወን ባሻገር፣ የተበላሹ ዕቃዎችን በመፈታታት፣ በመፈተሽና በመገጣጠም ላይ ያተኮረ ነው። የጥገናው ሂደት በዚህ መልክ በመሠራቱ ረዳት ቴክኒሺያኖች ከቡድን መሪው ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ አብረው፣ በኋላ ግን ለብቻቸው በመለማመድ የሥራ ችሎታቸውን ማዳበር ብቻ ሳይሆን የሥራ ጥራቱንም በማሳደግ ለተከታታይ ዕድገቶች ራሳቸውን በማዘጋጀት፣ ለፈተናዎች እየቀረቡ አስደሳች ውጤት አስመዝግበዋል። በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሠልጣኞች በዚህ "የሥራ ላይ ሥልጠና" ካለፉ በኋላ ለአየር ኃይል የቴክኒክ ግንባታ ምሰሶ ሆነው የተለያዩ የጄት አይሮፕላኖችን ተቀብለው በቀላሉ ለመጠገን ችለዋል። ይህን የዳበረና






የሠለጠነ የጥገና ኃይል አልፎ አልፎ ከአየር ኃይል አቅም ከፍ በሚልበት ወቅት ለውጭ ድርጅቶች ያካፈለበት ጊዜ ጥቂት አልነበረም።

ከነዚህ ቴክኒሺያኖች መካከል በትምህርታቸውና በሥራ ችሎታቸው ብልጫ ያሳዩ ተሳታፊዎችን ለከፍተኛ የቴክኒሺያንነት ትምህርት ወደ አሜሪካ በመላክ ተምረው ሲመለሱ በጥገና አመራርና አስተዳደር ውስጥ የሚገኙትን ቁልፍ ቦታዎች ሊይዙ በቅተዋል። ከጊዜ በኋላ ይህንን ትምህርት በራሳችን ትምህርት ቤቶች በመስጠት ለብዙ ቴክኒሺያኖች የዕድገት በር ከፍቷል።


ለጥገና ቴክኒሺያኖች የትምህርት ዕድል እንደተሰጠው ሁሉ፣ ለጥገና መኰንኖችም በሦስት የተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል። አየር ኃይል አካዳሚ በመግባት የሁለት ዓመታት የኰሌጅ ትምህርት በማሳተፍ ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማሸጋገር በኢንጂነሪንግ ትምህርት እንዲቀጥሉ ማድረግ ሲሆን ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ ተሳታፊዎች የማታ ትምህርት በመከታተል ራሳቸውን ለዲግሪ ፕሮግራም ማዘጋጀት ነው። ለዚህ ፕሮግራም ተሳታፊዎች፣ አየር ኃይል በየዕለቱ ከደብረዘይት አዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ደብረዘይት ማጓጓዣ ትራንስፖርት በማቅረብ እንዲሁም የትምህርት ክፍያ በመለገስ ብዛት ያላቸው አባላትን አስተምሯል። ሦስተኛውና የመጨረሻው ፕሮግራም ተሳታፊዎች ለአንድ ዓመት ያህል አሜሪካ በሚገኙ የአየር ኃይል የጥገና ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚሰጡትን የቴክኒክና የአመራር ኮርሶች እንዲሳተፉ በማድረግ አየር ኃይል የቴክኒክ አገልግሎቱን ሲገነባ ቆይቷል።



ይህን ጽሑፍ ያቀረቡት ኮሎኔል ተሾመ አቶ



ይህን ጽሑፍ ያቀረቡት ኰሎኔል ተሾመ አቶ



የአየር ኃይል ቺፍ ዴ ኤታ ማዦር ብ/ጄኔራል አበራ ወልደ ማርያም ከሠራዊቱ
መኮንኖች ጋር ከቤተመንግሥት መግቢያ ላይ



የአይሮፕላን ምህንድስና አንደኛ ኮርስ
ከግራ ወደ ቀኝ፡ በቀለ ግዛው (ኮ/ል)፣ ታደሰ ላቀው (ኮ/ል)፣ ጌታሁን እጅጉ (ኮ/ል)፣
አፈወርቅ አጥላባቸው (ብ/ጄ)፣ አሰፋ ክፈተው (ኮ/ል)፣ ሠይፉ ኃይለ ሥላሴ (ሻለቃ)፣
ስቬንሰን፣ ሙሉ ወንድሙ (ኮ/ል)፣ ጉደታ ገብረወልድ (ም/መ/አ)፣ ተስፋዬ መንገሥቱ
ኮ/ል። የተቀመጡት ብንያም ባሕልቢ (ኮ/ል)፣ በቀለ ያኒ (ኮ/ል)

የቀድሞ አሠሪዎች ከሥራ መልቀቅ፣ የቴክኒክ አገልግሎቱንና የሥራ አመራሩን ያዳከመዋል ተብሎ የተፈራውን ያህል ተጽዕኖ አላሳደረም:: እንዲያውም ከአራት የሚበልጡ መሐንዲሶች እ.ኤ.አ. በ1960 ዓ.ም ጥገናውንም ሆነ የሥራ አመራሩን በማደራጀት በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል ታላቅ አስተዋጽዖ አድርገዋል:: ከዚህም አንዱና ዋነኛው ቀላልና መለስተኛ ጥገና ዎችን በአንድነት በማሰባሰብ የዕለት ከዕለት የጥገና ሥራዎች በቀላሉ የሚስተናገዱበት መዋቅር በመዘርጋት የሥራ ክፍፍልን ከኃላፊነት ጋር ያዛመደ አቋም ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ እንዲሠራበት ተተኪ የሆኑት ኃላፊዎች ረድተዋል:: በአንፃሩ ይህ አዲስ መዋቅር በቀላልና በመለስተኛ ጥገና ብቻ ሳይወሰን፣ የከባድ ጥገና ሥራዎችን እንደ አይሮፕላንና የሞተር ዕደሳ ጭምር ያጠቃልላል:: በተጨማሪም ይህ አዲስ መዋቅር በቀላልና በከባድ ጥገና መካከል ያሉን የሥራ ግንኙነትና የሥራ ድርሻ አብራርቶ ያስቀመጠ ሲሆን፣ የጥገና ክፍሎችም ያላቸውን የርስ በርስ ትስስር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠበቀው እንደሄደ በሂደት ታይቷል:: ይህ የርስ በርስ ትስስር ሊጠነክር የቻለው ክፍሎች ለቆሙለት የህብረት ዓላማ አንድ በመሆናቸው ነው:: ይኸውም አስተማማኝ የሆነ የበረራ አገልግሎት እንዲገኝ አይሮፕላኖቹን በብዛት በመስመር ላይ እንዲቀርቡ በማዘጋጀት ነው:: ለዚህ ዓላማ ተሰልፈው ሌት ተቀን ሠርተው ለብዙ ጦር ውጊያዎች ለውጤት ያበቁንን የጥገና አባላት ታሪክ ሲያስታውሳቸው ይኖራል::

## የበረራ ክፍሎች ተከታታይ ዕድገት

ከ12 ዓመታት የስዊድኖች አስተዳደር በኋላ በ1951 ዓ. ም. አየር ኃይሉ አሥመራ ላይ አንድ የቢ-17ና አንድ የፌሪ ፋየር ፍላይ ተዋጊና ቦምብ ጣይ እስኳድሮኖች ሲኖሩት ደብረዘይት ደግሞ በ14 ሣፊሮች የተጠናከረ የበረራ ትምህርት ቤት እንዲሁም ከሁለት የማይበልጡ ሲ-47 እና ሁለት ዳብ አይሮፕላኖች ያሉት የትራንስፖርት ክፍል ነበረው:: ተዋጊና ቦምብ ጣይ አይሮፕላኖቹ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ የነበሩ በመሆናቸው መለዋወጫም እንደልብ የማይገኝላቸው ሲሆኑ ኢትዮጵያውያኑ አብራሪዎችና ቴክኒሺያኖች ወደተሻለ ደረጃ ማለትም ወደ ጄት አይሮፕላኖች ለመሸጋገር ዝግጁ ሆነው በመጠባበቅ ላይ ነበሩ::


የአሜሪካኖች ርዳታ ተግባራዊ መሆን ሲጀምርና ሦስት አዳዲስ ቲ-33 ጄት ማስተማሪያ አይሮፕላኖች ደብረዘይት እንደደረሱ አሥመራ የነበረው የፌሪ ፋየር ፍላይ ስኳድሮን እንዲቆም ተደረገና ፓይለቶቹ ባስቸኳይ የቲ-33 የምድር ትምህርት በአሜሪካውያን አስተማሪዎች






እንዲማሩ ተደረገ:: በማከታተልም የመጀመሪያዎቹ ስድስት ፓይለቶች ተመርጠው የካቲት 21 ቀን 1951 ዓ.ም ለጄት አይሮፕላን አስተማሪነት ሥልጠና ወደ አሜሪካ ተላኩ:: ወዲያውኑ በመጀመሪያ ደረጃ የበረራ ትምህርት ቤት ከነበሩት ወጣት እጩ መኰንኖች ውስጥ አብዛኛዎቹ በሁለት ቡድን ተከፋፍለው በማከታተል በብዛት ረዘም ላለ የበረራ ትምህርት ወደ አሜሪካ እንዲሄዱ ተደረገ:: ከጥገናውና ከሌሎችም የተለያዩ ሙያዎች ምርጥ አባላትን ወደ አሜሪካ የመላኩ ፕሮግራም በማከታተል ቀጠለ::

በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ከተለያዩ የሙያ ዘርፎች በዛ ያሉ የአየር ኃይል አባሎች በመላው አሜሪካ ተሠራጭተው ስለነበረ ትምህርቱንና ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለማስተባበር በቀደምትነት አብረው ተልከው የነበሩት አስተባባሪ መኰንኖች ለፕሮግራሙ መሳካት የተጫወቱት ከፍተኛ ሚና ሳይጠቀስ አይታለፍም:: በተለይም አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ትምህርታቸውን የሚከታተሉት በደቡባዊ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ተሠራጭተው በመሆኑ በጊዜው የነበረው የነጮችና የጥቁሮች የዘር ልዩነት ፖሊሲ ለኢትዮጵያውያኑ አዲስ ነገር ሆኖባቸው መጠነኛ ችግር ፈጥሮባቸው ነበር::



ጃንሆይ የመጀመሪያዎቹን ቲ-33 አይሮፕላኖች ሲጎበኙ



ጃንሆይ የመጀመሪያዎቹን ቲ-33 አይሮፕላኖች ሲጎበኙ

**በመጀመሪያ** ወደ አሜሪካ የተላኩት ስድስት የጀት በረራ አስተማሪ ፓይለቶች ልክ በዓመታቸው ማለትም የካቲት 1952 ዓ. ም. ትምህር ታቸውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቀው እንደተመለሱ በሀገር ውስጥ የሚደ ረገው የጀት በረራ ትምህርት በሥርዓት መካሄድ ጀመረ። ሁኔታው በዚህ ላይ እንዳለ ከአሜሪካ መንግሥት የተሠጡት የመጀመሪያዎቹ ኤፍ-86 ተዋጊ ጀቶች መምጫቸው ስለተጣደፈ እነዚህ ከአሜሪካ የተመ ለሱት ስድስት ፓይለቶች በኤፍ-86 አይሮፕላን ላይም እንዲሠለጥኑ ተወስኖ ዝግጅት ተጀመረ።
አውሮፕላኖቹ ከአስፈላጊው የጥገና ድርጅት ጋር በሐምሌ 1952 ዓ.ም. ደረሱና የበረራው ሥልጠና በሁለት የአሜሪካ የበረራ መምህራን ተካሂዶ በአራት ወራት ውስጥ ኢትዮጵያውያኑ ፓይለቶች በአይሮ ፕላኑ ላይ የዘመቻ ዝግጁነታቸውን አጠናቀቁ። ወዲያውኑ የ1953ቱ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ተካሂዶ ይኸው አዲስ የተዋቀረው የኤፍ- 86 ተዋጊ ስኳድሮን ከሌላው ነባር የቢ-17 ስኳድሮን ጋር በመሆን የመንግሥት ግልበጣውን በማክሸፍ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫወተ። ብ/ጄኔራል አሰፋ አየነም የአየር ኃይል አዛዥነቱን ቦታ ከስዊድኖች ተረከቡ።

ከዚህ በኋላ ቀደም ብለው ለመሠረታዊ የበረራ ትምህርት በብዛት ወደ አሜሪካ የተላኩት ወጣት ፓይለቶች የሁለት ዓመት የበረራ ትምህር ታቸውን አጠናቀው በመመለስ ላይ ስለነበሩ የበረራ ክፍሎችን የማሟ ላቱና የማጠናከሩ ተግባር በመካሄድ ላይ እንዳለ የኮንጎ ችግር እየተባ ባሰ ሄደ። በመሆኑም በመጀመሪያ የአየር ኃይሉ የትራንስፖርት ስኳድሮን የተሳተፈበት የእግረኛ ወታደሮችን ወደ ኮንጎ ማጓጓዙ ከተጠ ናቀቀ በኋላ አዲሲ ከተዋቀረው የኤፍ-86 ተዋጊ ስኳድሮንም አራት አውሮፕላኖች ያለው ቡድን ከአስፈላጊው የሰው ኃይልና ሎጅስቲክስ ጋር በመስከረም 1954 ዓ. ም. ወደ ኮንጎ ዘምቶ በተባበሩት መንግ ሥታት ጥላ ሥር ከአንድ ዓመት በላይ አገልግሎት አበረከተ። (የተዋጊ ጀቶቹ የኮንጎ ዘመቻ ለአየር ኃይሉ የመጀመሪያው ከመሆኑም በላይ አስቸጋሪ ሁኔታዎችም የነበሩበት በመሆኑ ራሱን በቻለ ርዕሰ በዝርዝር ተገልጿል።)

የትራንስፖርት ስኳድሮኑም ከኮንጎ ዘመቻ ጋር በተያያዘ ምክንያት ከዳኮታዎቹ በተጨማሪ በባለ አራት ሞተር ሲ-54 አውሮፕላኖችም ጭምር ተጠናክሮ ስለነበረ ኮንጎ ላለው የኢትዮጵያ እግረኛ ጦርና እዚያው ለዘመተው የአየር ኃይል ተዋጊ ቡድን የሚያደርገውን የበረራ ድጋፍ በመደበኛ ሣምንታዊ በረራ ጭምር በማካሄድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። በመከከሉም በጉረቤት ሶማሊያ የውኃ ማጠለቅለቅ ችግር





በመፈጠሩ አንድ የትራንስፖርት ስኳድሮን ቡድን ተልኮ ከአንድ ወር በላይ በመቆየት ከፍተኛ የነፍስ አድን ሥራ አከናውኖ ተመልሷል።

የአየር ኃይሉ ሁለንታዊ ዕድገትና ወደ ጄት በረራ ሽግግር በዚህ ሁኔታ እየተካሄደ በመጋቢት 1954 ዓ. ም. የታንዛኒያው የመጀመሪያ ፕሬዚ ዳንት ጁሊየስ ኔሬሬ አየር ኃይሉን ጐብኝተው የተደረገውን ፈጣን ዕድገት ተመልክተው ከተመለሱ በኋላ ሀገራቸው ውስጥ ለተፈጠረው አለመረጋጋት የኢትዮጵያ አየር ኃይልን ድጋፍ ጠይቀው ስለነበር የተላከው የቲ-28ዲ አጥቂ ቡድን ሀገሪቱን በማረጋጋት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጐ ተመልሷል።

በጥገናውም ረገድ ከዕለት ወደ ዕለት ራስን የመቻሉ ጥረት ቀጥሎ የጄትንም ሆነ ጄት ያልሆኑ ሞተሮችን ሙሉ ለሙሉ የመጠገንና የማደስ ደረጃ ላይ ከመድረሱም ሌላ በልዩ ልዩ የኤሌክትሮኒክስና የናቪጌሽን መሣሪያዎች፣ እንዲሁም በጦር መሣሪያዎች አያያዝና ጥገና አስተማማኝ ዕድገት ተገኘ። የበረራ ትምህርት ቤቱም ከአሜሪካ በተመ ለሱ ፓይለቶች ከመጠናከሩም ሌላ በሣፊር አይሮፕላን ብቻ ይሰጥ የነበረውን የአንድ ዓመት ተኩል የመጀመሪያ ደረጃ የበረራ ትምህርት በሁለት በመክፈል፣ የመጀመሪያውን በሣፊርና ሁለተኛውን ክፍለጊዜ ግን ተለቅ ባለውና ለሚከተሉት አይሮፕላኖች በተሻለ ሊያዘጋጅ በሚያስ ችለው በቲ-28ኤ አይሮፕላን መስጠት ተጀመረ። በዚህኑ ጊዜ አየር ኃይሉ ከራሱ አልፎ ከሌሎች አፍሪካ ሀገሮች ተማሪዎችን በመቀበል በበረራ ትምህርት ቤቱ አሠልጥኗል። ከነዚህም ውስጥ አንዳንዶቹ የአየር ኃይላቸው አዛዦች ለመሆን በቅተዋል።

የሶማሊያ የመስፋፋት ዓላማ በ1956 ዓ. ም. ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ወቅት በመሆኑ የቶጎ ውጫሌ ጦርነት ተቀስቅሶ አየር ኃይሉ በነበሩት የኤፍ-86 እና ሌሎች ስኳድሮኖች አማካይነት በጠላት ጦር ላይ የማይረሳ ቅጣት አድርሶ የሀገሩን ወሰን አስከብሯል። ከዚያም በማስ ከተል ከአሜሪካ በተላከ ልዩ የሥልጠና ቡድን አማካይነት የተዋጊና የትራንስፖርት ስኳድሮኖች የተሳተፉበት "SANDY ROAD" ተብሎ በተሰየመና ከትራንስፖርት አይሮፕላኖች በሚጣሉ ብርሃን ሰጪ መሣሪ ያዎች አማካይነት የሚፈጸም የተቀነ ባበረ የሌሊት የማጥቃት ልምምድ ተደርጎ አየር ኃይሉ በሌሊትም ጭምር የውጊያ ብቃት እንዲኖረው ተደረገ። ይህ ልምምድ የአየር ኃይሉን የውጊያ ዝግጁነት በከፍተኛ ደረጃ ያሳደገው በመሆኑ ራሱን በቻለ ርእስ ተገልጿል።

አየር ኃይሉ በ1958 ዓ. ም. ከድምፅ ፍጥነት በላይ የመብረር ችሎታ ያላቸውን ኤፍ-5 ተዋጊ ጀት አይሮፕላኖች ከአሜሪካ መንግሥት

በማግኘት ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ለመሸጋገር ቻለ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላም ማለት በ1960 ዓ. ም. የንጉሠ ነገሥቱ የዘውድ በዓል ላይ የመጀመሪያው የኬንያ ፕሬዚዳንት ጆሞ ኬንያታ በእንግድነት ተጋብዘው በተገኙበት የአየር ኃይሉን ሁለንተናዊ ዕድገት ያሳየውና በውጪ ሀገር ዜና አውታሮችም ጭምር የተወደሰው ታላቅ የበረራና የምድር ትርኢት ተካሄደ:: (ይህ ትርኢቱ በስፋቱ፣ በጥራቱና በፖለቲካውም አንፃር ልዩ ሚና ስለነበረው ራሱን በቻለ ርዕስ ተዘርዝሮ ተገልጿል::)



ፕሬዚዳንት ኔሬሬ በጉብኝታቸው ጊዜ ጀት አይሮፕላን ኮክፒት ውስጥ





የአየር ኃይሉ ዕድገት በየፈርጁ ቀጥሎ በ1960 ዓ. ም. መጨረሻ ላይ ከእንግሊዝ አራት ካንቤራ ከባድ ቦምብ ጣይ ጄቶች ተገዝተው የሀገሪቱን የመከላከያ አቅም ወደ ስትራቴጂካዊ መልሶ የማጥቃት ደረጃ ለማድረስ ተቻለ:: የትራንስፖርት ስኳድሮኑም በተለይ ለጭነትና ለአየር ወለዶች አመቺ የሆኑትን በዛ ያሉ ሲ-119 ትላልቅ አይሮፕላኖችን ከአሜሪካ መንግሥት በማግኘት የበለጠ ተጠናከረ:: የሄሊኮፕተር ክፍሉም ከፈረንሣይ በተገዙ አልዌት ሄሊኮፕተሮች በበለጠ ከማጠናከሩም በተጨማሪ ለቤተመንግሥት ግልጋሎት ጭምር የተሰጡና የተገዙ የሶቭዬት ሥሪት ግዙፍ ሚ-8 ሄሊኮፕተሮችንም ሥራ ላይ አዋለ:: (የንጉሠ ነገሥቱ የ1963 ዓ.ም የሚ-8 ሄሊኮፕተር አደጋ በአየር ኃይሉ የአቪዬሽን ታሪክ አንድ ክስተት እንደመሆኑ በዚሁ አጋጣሚ ራሱን በቻለ ርዕስ በአጭሩ ተገልጿል::)

በ1965 ዓ.ም በተከሰተው ረሃብ መነሾ የተጀመረው ህዝባዊ እንቅስቃሴ ለመንግሥት ለውጥ ምክንያት ሆኖ ወታደራዊ አስተዳደር በ1967 ዓ.ም ከተመሠረተም በኋላ በጥሩ መሠረት ላይ የተገነባውና በአስተማማኝ የዕድገት ደረጃ ላይ የነበረው አየር ኃይል በተደጋጋሚ የሀገር አለኝታነቱን አስመስክሯል::

## የአየር ኃይል ተዋጊ ቡድን በኮንጎ ዘመቻ

የአየር ኃይላችን የትራንስፖርት ስኳድሮን የተሳተፋበት የኢትዮጵያን እግረኛ ጦር ክፍል ወደ ኮንጎ የማጓጓዙ ግዙፍ ሥራ ከተጠናቀቀ ወራቶች ተቆጥረዋል:: ቢሆንም የኮንጎ ሁኔታ እየተባባሰ መጥቶ የወቅቱ የተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሐፊ በጉብኝት ላይ እያሉ በአካባቢው በአውሮፕላን አደጋ የሞቱበትና ቅጥረኛ ፓይለቶች ከተገንጣይ-ካታንጋ እየተነሱ የኮንጎን መንግሥትና የተባበሩት መንግሥታትን ሠፈሮች ያለምንም የአየር ተቀናቃኝ እየደበደቡና እያፈረሱ የሚመለሱበት ወቅት ነበር::

የኮንጎ ሁኔታ ባጠቃላይ እየተበላሸና ከቁጥጥር ውጭ እየሆነ በመምጣቱ ከብዙ ሀገሮች ተውጣጥቶ በሀገሪቱ ከሠፈረው እግረኛ ጦር በተጨማሪ ከኢትዮጵያ፣ ከስዊድንና ከህንድ የተውጣጡ የአየር ኃይል ተዋጊ ቡድኖች ባስቸኳይ ወደ አካባቢው ለመላክ ስምምነት ይደረጋል:: (እንደሚባለው ንጉሠ ነገሥቱ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ቡድን ቀድሞ ኮንጎ እንዲገባ ከፍተኛ ጉጉት ነበራቸው::) ሁኔታው በእንዲህ እንዳለ አንድ እሑድ (8/1/54) ከቀኑ ሰባት ሰዓት አካባቢ ሁለት ተረኛ ተዋጊ



ፕሬዚዴንት ኔሬሬ በጉብኝታቸው ጊዜ ጄት አይሮፕላን ኮክፒት ውስጥ

ጄት ፓይለቶች በአስችኳይ የአየር ኃይሉ ምክትል አዛዥ ወደነበሩት ስዊድናዊ ኰሉኔል ቤት ይጠሩና ከደቂቃዎች በፊት ከንጉሠ ነገሥቱ በስልክ በተሰጣቸው ትእዛዝ መሠረት በማግስቱ ጠዋት ለጊዜው ሁለት ተዋጊ ጄቶች ወደ ኰንጐ ለማብረር ዝግጅት እንዲያደርጉና እንዲጠባበቁ ይነገራቸዋል:: ጉዳዩ ዱብ ዕዳ የሆነባቸው ሁለቱ ፓይለቶች በአስቸኳይ ወደ ካምፕ በመመለስ ለበረራው የሚያስፈልጉትን አንዳንድ መረጃዎች በማሰባሰብ ላይ እያሉ ሌሎች የስኳድሮኑ ፓይለቶች በየአድራሻቸው እየተፈለጉ ባጭር ጊዜ ውስጥ መሰባሰብ ጀመሩ:: በመሀከሉ ለሣምንት መጨረሻ ዕረፍት ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ሄደው የነበሩት ኢትዮጵያዊ የአየር ኃይል አዛዥ ጉዳዩ በስልክ ተነግሯቸው ኖሮ ከዚያው ካሉበት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በስልክ በመነጋገር የጉዳዩን ክብደት ከተረዱ በኋላ ባስቸኳይ ወደ ደብረዘይት ተመልሰው ዝግጅቱን መምራት ጀመሩ::

አየር ኃይሉ የተዋጊ ክፍሉን ከዚህ ቀደም ከሀገር ውጪ ለግዳጅ የላከ በት ጊዜ ባለመኖሩና ገና ወደ ጄት አውሮፕላኖች በመሸጋገር ላይ በመሆኑ አንድን የጄት ተዋጊ ቡድን ካስፈላጊው የሰው ኃይልና ሎጂስ ቲክስ ጋር አቀናጅቶ እንደኰንጐ ያለ እሩቅ ቦታ መላክ ቀላል ሥራ አልነበረም:: በተለይም ጊዜው ከኢትዮጵያ ጀምሮ ወደ ደቡብ ባሉ ሀገሮች ሁሉ ከባድ የክረምት ወቅት ከመሆኑም ሌላ የኰንጐ የፖለቲካ ሁኔታ እየተበላሸ በመምጣቱ በሀገሩ ውስጥ ያሉት የአውሮፕላን ማረፊያዎችና የመገናኛና የናቪጌሽን መሣሪያዎች አስተማማኝ ያለመ ሆን ዝግጅቱን የበለጠ አክብዶት ነበር:: በመሆኑም የሚላከው ተዋጊ ቡድን በሁሉም መስክ ራሱን መቻል ስለነበረበት የበረራው ዝግጅት፣ ሎጂስቲክሱና የሰው ኃይል የማደራጀት ሥራ ሌት ተቀን ተካሂዶ ልክ በሣምንቱ እሑድ ጠዋት (15/1/54) አራት ተዋጊ ጄቶች በኢንቴቤና በእስታንሊቪል (ያሁኑ ኪሳንጋኒ) በኩል ወደ ሊዎፓልድቪል (ያሁኑ ኪንሻሳ) ለመሄድ ከደብረዘይት ተነሱ::

ተዋጊ ጄቶቹ በጉዟቸው ላይ በየታቀደላቸው የማረፊያ ቦታዎች ለመድረስ ረጅም ሰዓት መብረር ስለነበረባቸው እያንዳንዳቸው ተጨ ማሪ አራት አራት የነዳጅ መያዣዎች (DROP TANKS) በውጭ በየክንፎቻቸው ሥር የጫኑ ሲሆን ጊዜው ከባድ የክረምት ወቅት ስለነበረ ሳይለያዩ ለረጅም ጊዜ ጥቅጥቅ ባለ ደመና ውስጥ መብረር ነበረባቸው:: እስከ ኢንቴቤ ያለው በረራ በዚህ ሁኔታ ተደረገና በማግሥቱ ወደ ስታንሊቪል የተደረገው በረራ ፈታኝና በጣም አስቸጋሪ ነበር:: በዚያን ጊዜ የነበረው የስታንሊቪል አውሮፕላን ማረፊያ አጭርና ለጄት ማሣረፊያ ካለመብቃቱም ሌላ የማረፊያ መቃረቢያው በረጃጅም ዛፎች የተከበበ በመሆኑ ጄቶቹ በጣም አስቸጋሪና መስዋዕትነትን በጠየቀ






ሁኔታ ነበር ለማረፍ የቻሉት:: ቀደም ብሎ ኰንጐ የዘመተው የኢትዮጵያ እግረኛ ጦር የሠፈረው በዚሁ በስታንሊቪል ከተማ ስለነበርና እንዳጋጣሚ ሆኖ ተዋጊ ጄቶቹ የደረሱበት ዕለት የመስቀል በዓል ዋዜማ (የደመራ ዕለት) ስለነበረ ጦሩና የከተማው ህዝብ በነቂስ ወጥቶ በታላቅ ደስታ ተቀብሏቸዋል:: በዚያን ወቅት የኢትዮጵያ ተዋጊ ጄቶች ከሁሉም ቀድመው ኰንጐ ምድር መግባታቸው በተለይም ኰንጐ ለዘመተው የኢትዮጵያ ሠራዊት ከፍተኛ ኩራትና አለኝታ ሆኖታል::

ጄቶቹ የመጨረሻ መድረሻቸው ሊዎፓልደቪል እንደመሆኑ እዚያ እንዲያደርሳቸው የጫኑት ነዳጅ ብዙ ስለነበረና ለወትሮው ከአካባቢው በሚኖረው ከፍተኛ ሙቀት የስታንሊቪል ሜዳ ለመነሣት ስለማይበቃ ቸው በማግሥቱ ጠዋት የአየሩ ሁኔታ ደመናማና ጭጋጋማ በመሆኑ መጠነኛ የካፊያ ስሜት በነበረበትና ቀዝቀዝ ባለበት ሁኔታ በመስከረም 17 ቀን 1954 ዓ. ም. ሊዎፓልደቪል ደርሰው በተባበሩት መንግሥታት ባለሥልጣናትና በአካባቢው ህዝብ ከፍተኛ አቀባበል ተደርጎላቸዋል:: በማግሥቱም ለህዝቡና ለባለሥልጣናቱ የአየር ትርኢት አሳይተዋል::

ከዚህ ዘመቻ ጥቂት ቀደም ብለው የአየር ኃይሉን አመራር ከስዊድኖች ተረክበው የነበሩት ኢትዮጵያዊ አዛዥ ጄኔራል አሰፋ አየነ ከአሜሪካ መንግሥት በተገኘ ሄርኩሊስ አውሮፕላን አስፈላጊውን የሰው ኃይልና ሎጂስቲክስ በመያዝ ጄቶቹ በየደረሱበት ቀድሞ በመድረስና ቀድሞ በመነሣት እየተከተሉ አመራር ይሠጡ ስለነበረና የኢትዮጵያ ሕዝብም ሁኔታውን በልዩ ልዩ የመገናኛ አውታሮች በዜና ይከታተል ስለነበረ አዛዡ በሕዝብ ዘንድ መታወቅንና ዝናን አትርፈዋል:: ከኛ የበለጠ አቅሙም ሆነ ድርጅቱ የነበራቸው የስዊድንና የህንድ ተዋጊ አይሮፕላኖች የኢትዮጵያ ቡድን ኰንጐ ከደረሰ ከሁለትና ሦስት ሣምን ታት በኋላ መድረሳቸው ሲታይ የአየር ኃይላችንን ቆራጥ እርምጃና ብርታት ያሳየ ዘመቻ ነበር:: "TOM-TOM" የተባለውና በየሣምንቱ የሚታተመው በኰንጐ የተባበሩት መንግሥታት ጋዜጣ በወቅቱ ስለሁኔታው ሲጽፍ የኢትዮጵያ ተዋጊ ቡድን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተዘጋጅቶ ቀድሞ ኰንጐ መግባቱን አድንቆ፤ የተገንጣዩ ካታንጋ ቅጥረኛ ፓይለቶችም የኢትዮጵያ ተዋጊ ጄቶች ኰንጐ የገቡ ስለሆነ በጣም ከፍተኛ ክፍያ ካልተሠጣቸው በቀር የሚያደርጉትን በረራ ሁሉ ያቆሙ መሆኑን ገልጾ ነበር::

የተዋጊ ቡድኑ ጥቂት ወራት ሊዮፓልዲቪል ከቆየ በኋላ ወደ ተገንጣዩ የካታንጋ ግዛት ቀረብ ወደሚለው የካሚና አየር ጣቢያ ተዛውሮ ለአንድ ዓመት ያህል በተባበሩት መንግሥታት ጥላ ሥር ግዳጁን ከተወጣ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል:: አየር ኃይላችንም በዚህ ዘመቻ አንድ

ፓይለት ከነአውሮፕላኑ በግዳጅ ላይ አጥቷል። በ1959 ዓ.ም ሌላ የተዋጊ ቡድን ወደ ኰንጐ በድጋሚ ዘምቶ ከሦስት ወራት ቆይታ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል:



ኰሎኔል ወብሸት ተፈራ
«የበረራ ክፍል ተከታታይ ዕድገቶች» እና «የኰንጎን ዘመቻ» በተሰኙት ሁለት ርእሶች የተረቡትን ጽሑፎች ያቀረቡት ሌ/ኰሎኔል ወብሸት ተፈራ (በዚያን ጊዜ ሙሉ የመቶ አለቃ) ተዋጊ ጀቶቹን በማብረር በመጀመሪያ ኰንጎ ከዘመቱት አራት ፓይለቶች አንዱ ነበሩ።

## የሳንዲ ሮድ በረራ ሥልጠናና ልምምድ

የአሜሪካ መንግሥት በኮምኒዝም ላይ የነበረው ዋነኛው ፖሊስ "አፍኖ መያዝ" የሚለው መርህ እንደነበር የሚታወቅ ነው። እ.ኤ.አ. በ1960ዎቹ ደግሞ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች ከአውሮፓውያን ቅኝ አገዛዝ ለመላቀቅ እንቅስቃሴ የጀመሩበት ጊዜ ነበር። በመሆኑም በየቦታው የነፃነት ንቅናቄዎች በመጀመራቸው የሽምቅ ውጊያ እየጨመረ ሄደ። የአፍሪካ አገሮችም ነፃነታቸውን በሚያገኙበት ጊዜ ወደ ኮምኒዝም ካምፕ እንዳይገቡና አሜሪካ ሲመኘው የነበረው የአፍኖ መያዝ ዓላማው እንዳይሰናከል ከፍተኛ ፍላጎት ነበረው።

በኢትዮጵያ አካባቢም ነፃነታቸውን የተጎናጸፉና ለመጎናጸፍም የተዘጋጁ ኬንያና ሶማሊያ ነበሩ። አሜሪካ የነፃነት ትግሉ በዓለም ዙሪያ እየተ ስፋፋ መሄዱን የምትደግፈው ቢሆንም፤ የነፃነቱ ንቅናቄ የኮምዩኒዝምን





ርእዮተ ዓለም ለማስፋፋት የሚጥሩትን ወገኖች ለማስቆም የሚችል የወታደራዊ ኃይል ማቋቋሙን ስላመነችበት «ልዩ የአየር ኃይል ማዕከል» በሚል ስም አንድ ኃይል አቋቁማ የራሷን ጦር ለማዘጋጀት ተያይዛው ነበር።

ይህ ወቅት የኢትዮጵያ አየር ኃይል የአሜሪካ አይሮፕላኖችን (ተዋጊ፣ አጥቂና ማሠልጠኛ) ታጥቆ በጥሩ ግስጋሴ ላይ የነበረበት ነው። በመሆኑም «ፀረ ሽምቅ ውጊያ እናስተምራለን» በማለት ብዙ ሙያተ ኞች የያዘ የአሜሪካ ወታደራዊ ቡድን «ሳንዲ ሮድ ኦፕሬሽን» ተብሎ የተሰየመውን የውጊያ ሥልጠና ለመስጠት በ1965 (እ.ኤ.አ.) ወደ ኢትዮጵያ ገባ። ቡድኑ እንደመጣ ለልምምድ የተመረጠው አካባቢ ድሬዳዋን ማዕከል ያደረገ እንዲሆን ተወሰነ። ይህም የሆነበት ምክንያት ሶማሊያ ነፃነቷን ካገኘች በኋላ ኢትዮጵያን በመውጋቷና፣ ከተሸነፈች በኋላ ደግሞ በኦጋዴን ውስጥ ሰርጎ ገቦችን በማስረግ የተለያዩ ንቅናቄዎችን ስታደርግ ስለነበረ ከትምህርቱ በተጓዳኝ እጇን እንድት ሰበስብ ለማድረግ ነበር።

የአሜሪካኖቹ ቡድን በራሪዎችን፣ የአየር ወለድ ሙያተኞችንና የመገናኛ ዘዴ አዋቂዎችን እንዲሁም ከፍተኛ የሥነ ልቡና ምሁር የሆኑ አንድ ሳይንቲስት የያዘ ነበር። እኚህ ምሁር የመጡት የአሜሪካ ወታደሮች ከውጭ አገር ሰዎች ጋር በሚሠሩበት ጊዜ እንዴት ይግባባሉ? ማኅበ ራዊ ግንኙነታቸውስ ምን ይመስላል? የሚለውን አጥንተው መፍት ሔዎችን በማቅረብ ለወደፊት የግንኙነት ሥርዓት እንዲመሠረት ዘዴ ለመፈለግ ነው። ሳይንቲስቱ ኢትዮጵያውያን አብራሪዎች በሙሉ ክፍል ውስጥ ሆነው ትምህርት በሚከታተሉበት ጊዜ ከአስተማሪዎቹ ጋር በሚኖረው ጥያቄና መልስ ወቅት የአብራሪዎች የመቀበልና የመገንዘብ ሁኔታ ከፍተኛ መሆኑን ከገመገሙ በኋላ ከጥያቄዎቻቸው አንዱ "ቀደም ሲል አሥራ ሁለተኛ ክፍል ብቻ የጨረስን ነን» ብላችሁኝ ነበር «አሁን ላየው ግን ይህ ሊሆን የሚችል አይመስለኝም፤ ምንም የኮሌጅ ትምህርት እንዳልወሰዳችሁ እርግጠኛ ናችሁ?» የሚል ነበር። እያይዘውም «ግንዛቤአችሁ በጣም ሰፊና ሁሉን አቀፍ ነው። በእኔ አገር የዩኒቨርሲቲ ዲግሪ ያለው ከዚያች ከተማራት ሙያ ውጭ ምንም ነገር አያውቅም፤ እናንተ ግን በማንኛውም ርእስ መግባባት የምትችሉ ናችሁ» በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

የዶ/ር ሄንስ ዕውቀት በሥነ ልቡና የትምህርት ሙያ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ስለ ሕዋ ምርምርም ከፍተኛ ዕውቀት ነበራቸው። በትርፍ ጊዜያቸውም ስለ ሳይበርነቲክስ (Cybernetics) ብዙ ገለጻዎች አድርገ ዋል። ከኢትዮጵያውያን አብራሪዎች ጋር የነበራቸው ግንኙነት ከፍተኛ



ኮሎኔል መንግሥቱ ነዋይ

በመሆኑ አብረው ለመብረርና የድፍረታቸውንም ደረጃ ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት አደረባቸው:: የሚያሳዝነው ግን አንድ ቀን ከእጩ መኮንን ምናሴ ዘውዴ ጋር በቲ-28ዲ አይሮፕላን የቦምብ አጣጣል ልምምድ አብረው ሲበሩ ከዳይቭ (ከፍተኛ ማሽቆልቆል) ሲወጡ ክንፉ በመገንጠሉ አይሮፕላኑ ተከስክሶ ሁለቱም ሞቱ:: በዚያ አደጋ አብራሪውን የአየር ኃይል አባልና እሳቸውን የመሰለ ሰው በማጣቱ እጅግ ቢያሳዝንም የመጡበትን ዓላማ በመገንዘብ የተጀመረው ልምምድ በከፍተኛ ጥንቃቄ፣ ፍላጎትና ወኔ እንዲፈፀም ያልተቆጠበ ጥረት ተደርጓል::

ወታደራዊ ቡድኑ በመጀመሪያ የክፍል ትምህርት በመስጠት ጀመረ:: ከሁኔታው የተገነዘብነው ነገር ቢኖር በቋንቋው ምክንያት የትምህርት ደረጃቸውም ዝቅተኛ ይሆናል የሚል ስጋት እንደነበረባቸው ያስታውቅ ነበር:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን አብራሪዎች ባሳዩት ተሣትፎና የመገንዘብ ችሎታ በመደነቅ ትምህርቱን በከፍተኛ ፍጥነት አከናወኑ:: የቀጠለው የበረራ ልምምዱ ነበር:: በዚህም ቢሆን የእነሱ አስተሳሰብ ሁላችንንም በማስተማሪያ አይሮፕላን ካሳዩን በኋላ ወደ ዋናው ልምምድ እንድንገባ ተደረገ::

ስለዚህም ከድሬዳዋ ከ50-60 ኪሎ ሜትር ርቀት በስተሰሜን ምዕራብ የተኩስ ኢላማ ወረዳ ተዘጋጀ:: ይህ ቦታ ልክ የጠላት ወታደራዊ ጣቢያ ሊኖረው የሚችለውን ክምችት ሁሉ የያዘ መስሎ የተዘጋጀ ነበር:: በዚህ ላይ ነበር የቦምብ፣ ሮኬትና መትረየስ ተኩስ ልምምዱ የተደረገውና በአብራሪዎቹም ኢላማ የመምታት ችሎታም አሜሪካኖቹ ተደንቀው "እናንተ ሰዎች ሁሉንም የምትችሉ ናችሁ" ያሉት:: በቀን ብርሃን የበረራ ልምምድ ከተፈጸመ በኋላ ቀጣዩ ልምምድ የማታ በረራና በማታ የማጥቃት ልምምድ እንዲካሄድ ተወሰነ:: ለዚህም ቲ-28ዲ እና ሲ-47 (ዳኮታ) በተባሉት ጄት ባልሆኑ አይሮፕላኖች በድሬዳዋና አዋሬ ላይ ልምምዱ እንዲደረግ ተወሰነ:: የድሬዳዋ አይሮፕላን ማረፊያ በሲሚንቶ ኮንክሪት የተሠራ የጄት አይሮፕላኖቹም ሊጠቀሙበት የሚያስችል ነበር:: የአዋሬው ሜዳ ደግሞ የተደለደለ አሸዋ ሆኖ ምንም ዝግጅት ያልተደረገበት ሲሆን በዚህ ሜዳ ላይ ሊሠሩ የሚችሉት ቲ-28ና ሲ-47 ነበሩ:: ከፍተኛ ብርሃን የሚሰጥ "ፍሌር" የተባለ መሣሪያ በሲ-47 በመጣል እየበራ በፓራሹት እንዲወርድ በማድረግ የኢላማ ወረዳውን እንደቀን በብርሃን እንዲሸፍነው በማድረግ ለመቀጠል ተወሰነ::

ቲ-28ዲ የተባሉት አጥቂ አይሮፕላኖች ፍጥነታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ በረራውን ለማከናወን እዳጋች አልነበረም:: እሁን አጠያያቂና አሳሳቢ የሆነው በከፍተኛ ፍጥነት በሚምዘገዘጉት ተዋጊ ጄቶች መፈጸሙ ሆነ::





አሜሪካውያን አስተማሪዎችም በእርግጠኛነትና በጽኑ እምነት ቀጥሉ ለማለት አልደፈሩም ነበር:: በመጨረሻ ግን በረራው እንዲቀጥል ተወሰነ:: አፈጻጸሙም እንደሚከተለው ነበር:-


- ሲ-47 አይሮፕላን ተቀጣጣይ "ፍሌሮችን" ይዞ ወደ ኢላማ ቀበሌ ይቃረባል::
- ከሱ ከፍ ብሎና ወደ ጎንም ራቅ ብለው ደግሞ ተዋጊ ጄቶች ይቃረባሉ::
- ሲ-47 በጨለማ ውስጥ ኢላማው ላይ እንደደረሰ ፍሌሩን ይጥልና "ፍሌርስ አዌይ" በማለት በሬዲዮ ያስተላልፋል::
- ተዋጊ ጄቶቹ ቦታቸውን አመቻችተው ይቆዩና ጥቅጥቅ ካለው ጨለማ ውስጥ በመውጣት እያሽቆለቆሉ ወርደው ፍሌርሱ ተቀጣጥሎ ከስሩ ያለውን መሬት እያበራ ከሚያሳየው ዒላማ ላይ ቦምብ ወይም ሮኬታቸውን ጥለው ይወጣሉ::

በዚህ ዓይነት ልምምድ ቀጥሎ በጣም ከፍተኛ ውጤትም ተገኝቶበት ተገባዷል:: በመጨረሻ አብራሪዎቹ የተለያዩ የአየር ላይ ልምምዶች ካደረጉ በኋላ ከምድር ኃይል ተዋጊ ጋር በቅንጅት መዋጋት ስለሚቻልበት ዘዴ ጠለቅ ያለ የክፍል ትምህርት ተሰጠ:: በዚህም መሠረት ተዋጊ ወይንም አጥቂ አይሮፕላኖች ከእግረኛው ጦር ጋር ሆኖ በመሬት ላይ የሚገኝ ተቆጣጣሪ ወይም መሪ በሚያመለክታቸው መሠረት ኢላማቸውን በመደምሰስ ለወገን ጦር አመቺ ሁኔታ የሚተባበሩበት መንገድ ተፈጠረ:: ይህ ትምህርት ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠው ለአብ ራሪዎች ነበር:: ሆኖም አብሮ የሚዋጋውና ተጠቃሚው የእግረኛው ሠራዊት እንደመሆኑ ትምህርቱን ከወሰዱት ውስጥ የተወሰኑ አብራ ሪዎች ተመርጠው የጦር ክፍሎች በሚገኙበት ቦታ ሁሉ እየተዘዋወሩ አስተማሩ:: ይህም አሠራር እስከአሁን ድረስ አየር ኃይሉ ለወገን ጦር የተኩስ ድጋፍ በመስጠትና ከፍተኛ ውጤት የሚያገኝበትና አለኝታ ኑቱንም ያረጋገጠበት ዘዴ ነው::

የበረራ ልምምዱና የክፍል ትምህርቱ ከአራት ወራት በላይ ፈጅቶ እንደተጠናቀቀ በድሬዳዋ አየር ጣቢያ ላይ እግረኛው ጦርና የአየር ኃይል አይሮፕላኖች ከፍተኛ የውጊያ ስልት በተቀናጀ ሁኔታ ያሳዩት ትርኢት ተከናወነ:: በዚህ ወቅት በአይሮፕላኖቹ የተደረጉ የቦምብና ሮኬት ድብደባና የመትረየስ ተኩስ የኢላማ ወረዳውን ጭስ በጭስ አደረገው:: ከንጉሠ ነገሥቱ ጀምሮ ወገን በሙሉ ኰራ፤ አስተማማኝ ኃይልም እንዳለው አመነ:: በዚህ ትርኢት ላይ ግን አንድ አስቂኝ ሁኔታ

ደርሷል። (ከቁም ነገር ጋር ቀልድም አለኮ።) አራት ኤፍ-86 ተዋጊ ጄቶች ይቃረቡና የኢላማ ወረዳውን በቦምብና በሮኬት መደብደብ ይጀምራሉ። የመጀመሪያዎቹ ሦስት አይሮፕላኖች ድብደባ ያረፈው በኢላማው ላይ ስለነበር ተመልካቹ በደስታ ያጨበጭባል፤ አራተኛው አይሮፕላን ከኢላማው ውጭ አሳልፎ ይመታል። በዚህም ፓይለቱ በጣም ያዝናል። ሁሉም አብራሪዎች ቅር ይላቸዋል። መሬት ለተመልካች የተነገረው ገለፃ ግን ሌላ ነበር። አስተዋዋቂው በድምጽ ማጉያው ሲናገር:- *«ክቡራን እንግዶች የመጨረሻው አይሮፕላን ቦምብ ከኢላማው ውጭ ያረፈው ስቶ እንዳይመስላችሁ፣ ቀደም ብሎ የመቱትን ቦታ ለቆ የሚሸሽ ጠላት አይቶ አሳዶ መምታቱ ነው አለ»*። ይህንን ሲሰሙ የአብራሪዎቹ ቅሬታ ወደ ፈገግታ ተለወጠ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ በልምምዱ ለተሳተፉ አባላትና ጥሪ ለተደረገላቸው የመንግሥት ባለሥልጣኖችና እንግዶች ታላቅ ግብዣ በራስ ሆቴል ተደርጎ ተሳታፊዎቹም ምስክር ወረቀታቸውን አግኝተው ተፈጸመ። የአሜሪካውያን አስተማሪዎች ተወካይ ንግግር ሲያደርጉ ግን ሁሉንም ያስደነቀና ያስደነገጠ ዜና ቀረበ። ይኸውም በማታ የአየር ድብደባ አሜሪካኖችም በጄት ተዋጊ አይሮፕላኖች ሞክረውት እንደማያውቁና የኢትዮጵያ አብራሪዎች የመጀመሪያ መሆናቸውን አረጋገጠ። ሌላ ኩራት።



ብ/ጄኔራል ተሜን መስፍን

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ብ/ጄኔራል ተሜን መስፍን (በዚያን ጊዜ የመቶ አለቃ) በዚህ ልምምድ ላይ በኤፍ-86 ተዋጊ ጄት ፓይለትነት ሙሉ በሙሉ የተሳተፉ ናቸው።





# ወደ ሱፐር ሶኒክ ሽግግርና የዕድገት መለኪያዎች

«ዮቋንዲ ሮድ» ዘመቻ ያላንዳች እንቅፋት በከፍተኛ ውጤት መከናወኑ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ወደሚቀጥለው ደረጃ ለመሸጋገር ብቁና ዝግጁ መሆኑን ያለምንም ጥርጣሬ አረጋግጦ፣ ቢስኪሌት ሳይፈናጠጥና መኪና ሳይነዳ፣ ጄት አይሮፕላን ማገለባበጥን፣ ጦር ሜዳ ውሎ ጠላትን ድል ለመንሳት የበቃው ወጣት፣ የጄት ሞተር ፈትቶ መገጣጠም፣ የሬዲዮ፣ የኤሌክትሮኒክስና የጦር መሣሪያ ሁሉ ከነትጥቁ ከቁጥጥሩ ስር ያደረገው ቴክኒሺያን ባጭር ጊዜ የደረሰበትን ደረጃ የውጭ አገር ዜጎችንና አስተማሪዎችን ሁሉ አስገረመ። አስደነቀ።

በዚሁ መነሾ የአሜሪካ የወታደራዊ ተራድኦ ድርጅት (MAAG) ልዩ ጥናት ካስደረገ በኋላ የኢትዮጵያ አየር ኃይል በጊዜው ዘመናዊ የሆነውን ኤፍ-5 የተባለ (ከድምጽ ፍጥነት በላይ የሚበር) ሱፐር ሶኒክ የጦር አይሮፕላን እንዲታጠቅ ወሰነ። ይህንን ዕቅድ በሥራ ላይ ለማዋል ሁለት ነባር አብራሪዎችና በቁጥር 50 የሚሆኑ ከልዩ ልዩ የጥገናና የኤሌክትሮኒክስ ሙያዎች የተውጣጡ ቴክኒሺያኖች ለሥልጠና ወደ አሜሪካ ተላኩ። ይህ ቡድን በሚያዝያ መጀመሪያ 1958 ዓ.ም እንደተመለሰ የመጀመሪያዎቹ ኤፍ-5 አይሮፕላኖች ደብረዘይት ገቡ። እነዚሁ አራት አይሮፕላኖች በሁለት ኢትዮጵያውያን ፓይለቶች በሁለት አይሮፕላኑን ባመጡት አሜሪካኖች አብራሪነት የሚያዝያ 27 በዓል ላይ የበረራ ትርኢት አሳዩ። በማከታተልም ሠልጥነው በተመለሱት ሁለት አስተማሪዎችና አንድ አሜሪካዊ አማካሪ አማካይነት የበረራው ሥልጠና ተከናውኖ ባልታሰበ አጭር ጊዜ ውስጥ አንድ የታክቲካል ተዋጊ ስኳድሮን ተቋቋመ። አብራሪዎቹም ሆነ ቴክኒሺያኖቹ አብዛኛዎቹ ቀደም ብሎ ከተቋቋመው የኤፍ-86 ስኳድሮን ውስጥ ብዙ ልምምድ ካላቸው የተውጣጡ ስለነበረ ሽግግሩ ከታሰበው የበለጠ ቀላል ሆኖ ተገኘ።

የኢትዮጵያ አየር ኃይል ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በችሎታና በዕድገት የመጨረሻ ከፍተኛ ደረጃ ደረሰ ተብሎ ወደሚነገርለት ደረጃ የደረሰው ብዙ ውጣ ውረድ አልፎ፣ የብዙ ሰው ሕይወት ተሰውቶ፣ እያሌ መሣሪያዎች (አይሮፕላኖች) ተከስክሰውና ብዙ የሙዓለ ንዋይ ወጪ ተደርጎ እንደሆን የማይታበል ሀቅ ነው። ስለሆነም አቪዬሽን ቀርቶ ትምህርት እንኳን ገና ባልተስፋፋበት ዘመን ከባላገር ጭምር የተውጣጡት የኢትዮጵያ ወጣቶች አየር ኃይሉን ከበው ከፍተኛ ደረጃ ማድረሳቸው በኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በውጭ አገር ሰዎች ጭምር አድናቆት አግኝቷል።



ብ/ጄኔራል ተሜነ መስፍን

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ብ/ጄኔራል ተሜነ መስፍን (በዚያን ጊዜ የሙቶ አለቃ) በዚህ ልምምድ ላይ በኤፍ-86 ተዋጊ ጄት ፓይለትነት ሙሉ በሙሉ የተሳተፉ ናቸው::

የኢትዮጵያ አየር ኃይል በየጊዜው ያደርገው ለነበረው የዕድገት ፋና መለኪያ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው ከሚወሰዱት አንዱ የአየር ትርኢት ነው። በተለያዩ ምክንያቶችና አጋጣሚዎች ንጉሠ ነገሥቱ አንዳንዴም የተጋበዙ የሀገር መሪዎች በተገኙበት በኋላም ለመንግሥት ባለሥልጣናትና ለሕዝብ ክፍት የሆነ የአየር ትርኢት ይደረግ ነበር። የአየር ትርኢቱ ዋና አላማ የኢትዮጵያ ወጣቶች አይሮፕላን በማብረር፣ በማገለባበጥና በልዩ ልዩ መሣሪያዎች የማጥቂያ ዘዴ ዒላማ እንዴት እንደ ሚመቱና በጠቅላላ አየር ኃይሉ የደረሰበትን ደረጃ ለማሳየት ነበር። ከአየር ትርኢቱ በኋላ ተመልካቾች በልዩ ልዩ የቴክኒክ አገልግሎት አንፃር ማለትም በጥገናና ዕደሳ ሥራ፣ በአይሮፕላን ሀንጋር ውስጥ በመሠራት ላይ ያሉ አውሮፕላኖች፣ በትምህርት መስጫ ክፍሎችና በመሳሰሉት የተደረሰባቸውን ደረጃዎች ለማመልከት በሠራዊቱ አስረጂነት እንዲጎበኙ ይደረግ ነበር።

የአየር ትርኢቶችን አቀነባብሮ ለሕዝብ ለማሳየት የሚደረገው ወጪ ተገቢነቱ የሚለካው የአየር ኃይሉን ችሎታ በማሳወቁ፣ አዳዲስ ወጣቶችን እንዲስብ በማድረጉና የሌሎች አገር መንግሥታትም ወጣቶቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ አየር ኃይል ልከው እንዲሰለጥኑለት በመገፋፋቱ ነው። በተለይም በአየር ትርኢቱ ላይ በተዋጊ አይሮ ፕላኖች በግልም ሆነ በጥንድ የሚከናወኑ የመገለባበጥ በረራዎች የተለየ ሥፍራ አላቸው።

ሌሎች ታላላቅ መንግሥታት የዚህ ዓይነቱን ትርኢት በተግባር ላይ ለማዋል ቋሚ የሆነ የኤሮባቲክስ ቡድን አቋቁመው በየቀኑና ዓመቱን በሙሉ አብረው ልምምድ ያደርጋሉ። የኢትዮጵያ አየር ኃይል ግን ይህንን በቋሚ መልክ ለማድረግ የኢኮኖሚውም ሆነ የመሣሪያውና የሰው ኃይል አቅሙ ስለሌለው በየጊዜው ይደረግ ለነበረው ትርኢት ጊዜው ከመድረሱ ጥቂት ሣምንታት ሲቀረው አንድ ወይም ሁለት ቡድኖች አቋቁመው ልምምድ በማስደረግ ነው።

በ1940ዎቹ የቀድሞዎቹ ቢ-17 እና ፌሪ ፍየር ፍላይ አውሮፕላኖች በጊዜው የሚቻላቸውን አድርገው የመሸጋገሪያ ድልድይ ሆነው አልፈዋል። ከ1950ዎቹ ጀምሮ ግን በኤፍ-86 ከዚያም በኤፍ-5 ጄት አይሮፕላኖች በየጊዜው የሚቋቋሙት ቡድኖች የሚያሳዩት ትርኢት ምንኛ አድናቆት ያገኝ እንደነበረ አይዘነጋም። ይህ የኢትዮጵያ አየር ኃይል በየጊዜው እንዳስፈላጊነቱ የሚያቋቁማቸው የኤሮባቲክስ ቡድኖች በአየር ላይ ያደርጉት የነበረው የመገለባበጥ ትርኢት በማንኛውም ዓለም ለዚህ ብቻ ከሠለጠኑት ያላነሰ ነበር።





ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ሁሉ ወደ ጄት ዘመን መሸጋገርም ሆነ ከዚያም አልፎ ሱፐር ሶኒክ ዘመን የተደረሰው ያለምንም ዕንቅፋት አልነበረም። የብዙ ሰው ህይወት ተሰውቷል አያሌ አይሮፕላኖች ተከስክሰው ተሰባብረዋል። ስለሆነም አየር ኃይሉ እንደገና እየዳበረ በሄደ ቁጥር ያንኑ ያህል የህይወትም ሆነ የመሣሪያ ጉዳት እየቀነሰ ሄዷል። ከነቢ-17 ዘመን ወደ ጄት ሽግግር ዘመን የጠፋው ሕይወትና መሣሪያ ሲነጻጸር በጄት ዘመን የነበረው በጣም አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ይህም ሊሆን የቻለው:-

ሀ/ መሣሪያዎቹ ዘመናዊ በመሆናቸው፣

ለ/ የበራሪዎቹም ሆነ የቴክኒሺያኖቹ የትምህርት ደረጃ ከፍ እያለ ስለሄደ፣

ሐ/ የአይሮፕላን ጥገና ችሎታ በፕሮግራም ከዕለት ወደ ዕለት እየተሻሻለና እያደገ በመሄዱ፣

መ/ ከሁሉም በላይ የፕሮፌሽን አስተሳሰብ (Professionalism) በሁሉም ደረጃ እየዳበረ በመሄዱ ነው።



ሱፐር ሶኒክ አይሮፕላንና አዛዡ




ሱፐር ሶኒክ አይሮፕላንና አዛዥ



ብ/ጄኔራል ዮሐንስ ወልደማርያም

ከዚህ በላይ የሚገኘውን ጽሑፍ ያቀረቡት ብ/ጄኔራል ዮሐንስ ወ/ማሪያም የመጀመሪያው የሱፐር ሶኒክ ኤፍ-5 ስኳድሮን አዛዥ ሲሆኑ ከዚያም በኋላ የአየር ኃይል አዛዥ ነበሩ።

## ታላቁ የአየር ትርኢት


የኬንያ የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት ዕውቁ ጆሞ ኬንያታ ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ የታሰበው ከንጉሠ ነገሥቱ የንግሥ በዓል ጥቅምት 23 ቀን 1960 ዓ.ም ጋር እንዲገጣጠም ተደርጎ ስለነበር በዚሁ በዓል ላይ አየር ኃይሉ ከፍተኛ የበረራና የምድር ትርኢት እንዲያዘጋጅ ትዕዛዝ ደርሶት ዝግጅቱ ለበዓሉ ሦስት ሣምንት ሲቀረው ተጀመረ። ለአጠቃላይ የበረራና የምድር ትርኢቱ የበላይ ሃላፊ አንድ ብ/ጄኔራል ይመደቡና በረራውን በተመለከተ ግን ትርኢቱን እንዲያዘጋጁና እንዲያቀናጁ ሁለት ነባር ፓይለቶች ተመርጠው ሙሉ ሃላፊነት ተሰጣቸው። ይህ የአየር ኃይሉን አባላት በሙሉ ያሳተፈውና ሌት ተቀን የተደከመበት የበረራና የምድር ትርኢት በሀገር ውስጥ ተመልካች ብቻ ሳይሆን በውጪ ሀገር የዜና አውታሮችም ጭምር አስደናቂነቱ ተነግሮለትና የአየር ኃይሉንም ብቃት ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ አስመስክሮ በተሳካ ሁኔታ ተከናውኗል።





የበረራው ትርኢት ያለማቋረጥ ለሁለት ሰዓት ከሰላሳ ሦስት ደቂቃ ተካሄዶ አሥር የተለያዩ የአውሮፕላን ዓይነቶች የሚገኙበት በጠቅላላው ስድሳ አይሮፕላኖችንና ሰባ ያህል ፓይለቶችን ያሳተፈ ሲሆን ሃያ ሦስት የተለያዩ የአየር ትርኢቶችን ያቀፈ ነበር። በጣም ከፍተኛ ቁጥር ለነበረው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ተመልካች የተዘጋጀው ሥፍራ ቀኛዝማች ኃይሌ ኩረብታ ከሚባለው ላይ ሲሆን የኩረብታው አቀማመጥ በአንድ በኩል አውሮፕላኖቹ ከሥር ሲነሱና ሲያርፉ በቅርብ የሚያሳይና ዙሪያውን ግን ለጥ ያለ ሜዳ ሆኖ የነበረውን የቦምብና የሌላውን መሣሪያ ናዳ አለሥጋት በቅርብ ቁልቁል ለመመልከት የሚያስችል ነበር።

እንግዶቹና ተመልካቹ ሕዝብ ቦታቸውን ከያዙ በኋላ የበረራ ትርኢቱ ተጀምሮ ስድሣዎቹም አውሮፕላኖች በሃያ አምስት ደቂቃዎች ውስጥ ተነሥተው ወደ ተመደበላቸው አካባቢና ከፍታ እንዳመሩ፣ አሥር ሣፊር የማስተማሪያ አይሮፕላኖች የንግሥ በዓሉን ለማመልከት የዘውድ ቅርጽ ሠርተው ብቅ አሉ። በመከተልም አሥራ ስድስት ቲ-28 ማሠልጠኛ አውሮፕላኖች የእንግሊዝኛውን (JH) ቅርጽ ጐን ለጐን ሠርተው አለፉ። (J) የቆመው (JOMO) ለሚለው የኬንያታ መጠሪያ ሲሆን (H) ለኃይለ ሥላሴ ነው። ከዚያም የተቀሩት አውሮፕላኖች በዓይነት በዓይነታቸው በመከታተል በሠልፍ ካለፉ በኋላ ለሚከተሉት



ቲ - 28 አይሮፕላን



ብ/ጄኔራል ዮሐንስ ወልደማርያም

ከዚህ በላይ የሚገኘውን ጽሑፍ ያቀረቡት ብ/ጄኔራል ዮሐንስ ወ/ማሪያም የመጀመሪያው የሱፐር ሶኒክ ኤፍ-5 ስኳድሮን አዛዥ ሲሆኑ ከዚያም በኋላ የአየር ኃይል አዛዥ ነበሩ።

## ታላቁ የአየር ትርኢት


የኬንያ የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት ዕውቁ ጆሞ ኬንያታ ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ የታሰበው ከንጉሠ ነገሥቱ የንግሥ በዓል ጥቅምት 23 ቀን 1960 ዓ.ም ጋር እንዲገጣጠም ተደርጎ ስለነበር በዚሁ በዓል ላይ አየር ኃይሉ ከፍተኛ የበረራና የምድር ትርኢት እንዲያዘጋጅ ትዕዛዝ ደርሶት ዝግጅቱ ለበዓሉ ሦስት ሣምንት ሲቀረው ተጀመረ። ለአጠቃላይ የበረራና የምድር ትርኢቱ የበላይ ሃላፊ አንድ ብ/ጄኔራል ይመደቡና በረራውን በተመለከተ ግን ትርኢቱን እንዲያዘጋጁና እንዲያቀናጁ ሁለት ነባር ፓይለቶች ተመርጠው ሙሉ ሃላፊነት ተሰጣቸው። ይህ የአየር ኃይሉን አባላት በሙሉ ያሳተፈውና ሌት ተቀን የተደከመበት የበረራና የምድር ትርኢት በሀገር ውስጥ ተመልካች ብቻ ሳይሆን በውጪ ሀገር የዜና አውታሮችም ጭምር አስደናቂነቱ ተነግሮለትና የአየር ኃይሉንም ብቃት ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ አስመስክሮ በተሳካ ሁኔታ ተከናውኗል።





የበረራው ትርኢት ያለማቋረጥ ለሁለት ሰዓት ከሰላሳ ሦስት ደቂቃ ተካሄዶ አሥር የተለያዩ የአውሮፕላን ዓይነቶች የሚገኙበት በጠቅላላው ስድሳ አይሮፕላኖችንና ሰባ ያህል ፓይለቶችን ያሳተፈ ሲሆን ሃያ ሦስት የተለያዩ የአየር ትርኢቶችን ያቀፈ ነበር። በጣም ከፍተኛ ቁጥር ለነበረው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ተመልካች የተዘጋጀው ሥፍራ ቀኛዝማች ኃይሌ ኩሪብታ ከሚባለው ላይ ሲሆን የኩሪብታው አቀማመጥ በአንድ በኩል አውሮፕላኖቹ ከሥር ሲነሱና ሲያርፉ በቅርብ የሚያሳይና ዙሪያውን ግን ለጥ ያለ ሜዳ ሆኖ የነበረውን የቦምብና የሌላውን መሣሪያ ናዳ አለሥጋት በቅርብ ቁልቁል ለመመልከት የሚያስችል ነበር።

እንግዶቹና ተመልካቹ ሕዝብ ቦታቸውን ከያዙ በኋላ የበረራ ትርኢቱ ተጀምሮ ስድሣዎቹም አውሮፕላኖች በሃያ አምስት ደቂቃዎች ውስጥ ተነሥተው ወደ ተመደበላቸው አካባቢና ከፍታ እንዳመሩ፣ አሥር ሣፊር የማስተማሪያ አይሮፕላኖች የንግሥ በዓሉን ለማመልከት የዘውድ ቅርጽ ሠርተው ብቅ አሉ። በመከተልም አሥራ ስድስት ቲ-28 ማሠልጠኛ አውሮፕላኖች የእንግሊዝኛውን (JH) ቅርጽ ጐን ለጐን ሠርተው አለፉ። (J) የቆመው (JOMO) ለሚለው የኬንያታ መጠሪያ ሲሆን (H) ለኃይለ ሥላሴ ነው። ከዚያም የተቀሩት አውሮፕላኖች በዓይነት በዓይነታቸው በመከታተል በሠልፍ ካለፉ በኋላ ለሚከተሉት



ቲ - 28 አይሮፕላን

ሃምሣ ደቂቃዎች ሳያቋርጥ የተለያዩ ተዋጊ አውሮፕላኖች በግልና በጥንድ የመገለባበጥና ልዩ ልዩ ትርኢቶች አሳዩ:: ከዚህም ውስጥ አራት ኤፍ-86ና አራት ኤፍ-5 ጄቶች የተሳተፉበት ሁለት የተለያዩ የአውሮፕላን ቡድኖች ነበሩበት:: የትራንስፖርት አይሮፕላኖችም አንድ ሞተራቸውን በማጥፋት ጭምር ልዩ ልዩ ትርኢቶች አደረጉ:: ሄሊኮፕተሮችም በተመልካቹ ፊት ለፊት ቀረብ ብለው እንዳሻቸው በመሽከርከር ከአየር ዳንስ ያላነሰ ትርኢት አካሄዱ::

ተጨማሪ አንድ ሰዓት ያህል የፈጀው ሁለተኛው ክፍለ ጊዜ የጦር መሣሪያዎች ድብደባና የጦርነት ጊዜ እንቅስቃሴ ትርኢት እንደመሆኑ ኢላማዎች በተለያዩ ጄትና ጄት ባልሆኑ ተዋጊና ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች በመትረየስ፣ በሮኬት፣ በቦምብና፣ በናፓልም ተደበደቡ፤ አካባቢው በፍንዳታው ጭስ ታፈነ፣ በእሳት ነደደ:: ቀደም ብለው የትራንስፖርት አውሮፕላኖች በድብደባው ቀጠና አካባቢ በአጭር ርቀት በማረፍና ከሰማይ በጃንጥላ በማውረድ አጥቂ እግረኛ ጦርና አየር ወለዶችን አራግፈዋል:: ሄሊኮፕተሮች አስፈላጊውን ስንቅና ትጥቅ እያራገፉ ካካባቢው ተሠውረዋል:: ሰማይ ላይ ከፍ ብሎ የጄት አውሮፕላኖች አየር ላየር ውጊያ ተጧጡፏል:: በጠቅላላው አካባቢው ቅልጥ ያለ የጦር ቀጠና መስሎ ሲያበቃ በመጨረሻ ሄሊኮፕተሮች ቁስለኞችን አንስተው ሲሄዱ ትርኢቱ ይፈጸማል::

ይህ በሁለት ክፍል የተከፈለው ታላቅ የበረራ ትርኢት የውጭውን ተመልካች ብቻ ሳይሆን የአየር ኃይሉንም ሠራዊት ያረካ ከፍተኛ ዝግጅት የተደረገበትና ያለአንዳች አደጋ የተጠናቀቀ ነበር:: ትርኢቱን የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ «አስደናቂ የአየር ትርኢት» ብሎ ማታውኑ ሲገልጸው በትርኢቱ መጨረሻ ፕሬዚዳንት ጆሞ ኬንያታ በንግግ ራቸው ላይ «......ኢትዮጵያን በጦርነት የሚፈልግ በእሳት የሚጫወት ነው.....» ብለውት ነበር:: በመሆኑም ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ ከሶማሊያ ጋር በተደረገ ጦርነት አየር ኃይላችን አሥር ዓመታት ሙሉ በተለየ ሁኔታ ተደራጅቶ የነበረውን የሶማሊያን አየር ኃይል እንዳልነበረ አድርጎታል::

(የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ሌ/ኮሎኔል ውብሸት ተፈራ (የዚያን ጊዜ ሻለቃ) የበረራ ትርኢቱን ካዘጋጁትና ካቀናጁት ሁለት ነባር ፓይለቶች አንዱ ነበሩ::)





# የንጉሠ ነገሥቱ የሄሊኮፕተር አደጋ

ንጉሠ ነገሥቱ ሰኞ መጋቢት 6 ቀን 1963 ዓ.ም ለጉብኝት ከአዋሳ ቤተመንግሥታቸው ወደ ብላቴን እርሻ በአየር ኃይል ሄሊኮፕተር እንደሚሄዱ ከአንድ ሣምንት ቀደም ብሎ ለአየር ኃይሉ ትእዛዝ ደርሶ ታል:: በዚሁ መሠረት ንጉሠ ነገሥቱና አጃቢዎቻቸው ቁጥሩ 777 በሆነ በሶቪዬት ሥሪት ሚ-8 ትልቅ የአየር ኃይል ሄሊኮፕተርና በሌላ አነስተኛ የአርሚ አቪዬሽን ሄሊኮፕተር ተሳፍረው በተባለው ቀን በአራት ሰዓት አካባቢ ከአዋሳ ወደ ብላቴን በረሩ:: የብላቴን ጉብኝት ካለቀና ምሣ ከተበላ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱና አሥራ አምስት ተከታ ዮቻቸው በዚሁ ሚ-8 ሄሊኮፕተር ተሣፈሩና ከብላቴን ለመነሣት በሚያደርገው ዝግጅት የያኔው የአየር ኃይል አዛዥ የሚቀጥለውን የጉዞ አቅጣጫ ለፓይለቶቹ ለማመላከት ሲባል ከዋናው ፓይለት ኋላ በሚገኘ ው የቴክኒሺያኑ መቀመጫ ላይ ይቀመጣሉ::

ሄሊኮፕቲሩ ለወትሮው እንደሚደረገው ሁሉ ከመሬት ብድግ ብሎ ትንሽ ቆም ካለ በኋላ ፍጥነት ለማግኘት ሲባል ከሦስት ሜትር ያህል ከፍታ ፊት ለፊት መብረር ጀምሮ የታረሰው መሬት አካባቢ ሲደርስ ራሱ ባስነሳው ከባድ አቧራ ሙሉ ለሙሉ ይሸፈናል:: በዚህን ጊዜ የአየር ኃይሉ አዛዥ ፓል! ፓል! (የቆመ እንጨት!) በማለት በመደጋገም ጮክ ብለው ይናገራሉ:: ፓይለቱ ከኮክፒቱ ውጪ ምንም ነገር ስለማይታየው ሄሊኮፕተሩን በትክክል ማብረር ባልቻለበት ሁኔታ ሄሊኮፕተሩ ወደ ግራ እየዞረና እየወረደ ሄዶ በግራ እግሩ መሬት ይነካል:: በሁኔታው የተደናገጠው ፓይለት ሄሊኮፕተሩን ወደ ቀኝ ለመመለስ ባደረገው ጥረት ሄሊኮፕተሩ ከአፍንጫው ከፍ ብሎ ወደ ቀኝ ጐኑ ይገለበጣል:: ወዲያው ጭራው ላይ ያሉት አነስተኛ ውልብልቢቶች (TAIL ROTORS) ከመሬት ጋር ይጋጩና መሰባበር ይጀምራሉ:: ሄሊኮፕተሩ ሙሉ ለሙሉ ወደ ቀኝ ጐኑ ሲወድቅ ዋነኞቹ ውልብልቢቶች (MAIN ROTORS) መሬቱን እየረሱ መሰባበር ይጀምራሉ:: በዚህን ጊዜ ከፍተኛ ድምፅ እየተሰማ ሄሊኮፕተሩ መሬቱን እያረሰና እየተሰባበረ መዞሩን ቀጠለ:: ፓይለቶች በታሰሩበት ቀበቶ ተይዘው በጎናቸው ተንጠለጠሉ:: በወንበሩ ቀበቶ ሳይታሰሩ የነበሩት የአየር ኃይል አዛዥና ቴክኒሽያኑ በጣም ተንገላቱ:: በነበረው ሁኔታ ማናቸውም ሁኔታውን ለመቆጣጠርና ሞተሮቹን እንኳን ቶሎ ለማጥፋት ሳይቻላቸው ቀረ:: በመጨረሻም ሄሊኮፕተሩ መሬቱን እያረሰና እየተሰባበረ አንድ ሙሉ ዙሪያ ከዞረ በኋላ ቆመ:: ፓይለቶቹና ቴክኒሽያኑ የሞተሮቹንና ሌሎቹንም መቆጣጠሪያዎች ካጠፉ በኋላ በጐን በኩል በተሠበረ መስኮት


ሾልከው በመውጣት ከኋላ ዞረው የተሣፋሪዎችን በር ከፈቱት። ንጉሠ ነገሥቱና አጃቢዎቻቸው በየወንበሩ ላይ በሚገኘው ቀበቶ ታሥረው በየጎናቸው ከተንጠለጠሉበት እየተፈቱ በነበረው ሕዝብና ወታደር ዕርዳታ በደህና ለመውጣት ቻሉ።

በኋላ እንደተደረሰበት የውልብልቢቶቹ ስብርባሪዎች ከአደጋው ቦታ እስከ ሁለት መቶ ስድሣ ሜትር ድረስ በረው በመሄድ ሦስት ሰዎችን መትተው ገድለዋል። ከአደ ጋው በኋላ አብራሪዎቹ ለጊዜው በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ውለው ነበር። ነገር ግን ወዲያውኑ ከንጉሠ ነገሥቱ በተላለፈ ትእዛዝ ተለቀዋል። የዚህ አደጋ መከሰት በአንዳንድ አካባቢ ጥርጣሬና ሀሜት አስነስቶ የነበረ ቢሆንም አደጋው ከአቅም በላይ በሆነ አጋጣሚ እንጂ በሄሊኮፕተሩም ላይ ምንም ዓይነት ቴክኒካዊ ጉድለት እንዳልነበረ በተደረገው የተሟላ የአደጋ ምርመራ ተረጋግጧል።

የአደጋ ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የመከላከያ ሚኒስትሩና የአየር ኃይሉ አዛዥ በተገኙበት ለንጉሠ ነገሥቱ በጽሕፈት ቤታቸው ሙሉ ገለጻ ተደርጐላቸዋል። ከገለጻው በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ አንዳንድ ቴክኒካዊ ጥያቄዎችን ጠይቀው ሲያበቁ «ልጆቹ (ማለት ፓይለቶቹና ቴክኒሺያኑ) ያለምንም ሥጋት ሥራቸውን እንዲሠሩ ንገሯቸው......" ብለው ጉዳዩ በዚሁ ተዘጋ።

(ከዚህ በላይ የቀረበውን ጽሑፍ ያዘጋጁት ሌ/ኮሎኔል ውብሸት ተፈራ በጊዜው የበረራ ሴፍቲ ዳይሬክተር የነበሩና አደጋውን በሊቀመንበርነት መርምረው ውጤቱን ለንጉሠ ነገሥቱ ገለፃ ያደረጉ ናቸው።)





መስከረም 1 ቀን 1949 ዓ. ም. አሥመራ ተመድበው የነበሩ መኮንኖች



መስከረም 1 ቀን 1949 ዓ. ም. አሥመራ ተመድበው የነበሩ መኮንኖች

# የመገናኛ አገልግሎት

በዘመናችን «የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ አገልግሎት ለአንድ የጦር ክፍል አዛዥ እንደ አምስቱ የሰው የስሜት ሕዋሳት አገልጋይ ናቸው፤ የተሟላ የኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ አገልግሎት የሌለው የጦር ክፍል አዛዥ ለማዘዝ የሚችለው ጦሩን ሳይሆን እፊቱ የሚገኘውን ጠረጴዛውን ብቻ ነው» ይባላል፤ ትክክልም መሆኑ በዘመናችን ተረጋግጧል። የኢትዮጵያ አየር ኃይል ሲቋቋም ከበረራ ትምህርት ቤት ጋር የሬዲዮ ኦፕሬተር ትምህርት ቤት አብሮ ከጎኑ በመክፈት፣ የሬዲዮ ኦፕሬተሮችን ለበረራና ለምድር ሬዲዮ ጣቢያ አገልግሎት አሰልጥኗል። በጊዜው ይከተለው የነበረው ሥርዓተ ትምህርት የኢንተርናሽናል ሲቪል አቪዬሽን ድርጅትና የኢንተርናሽናል ሬዲዮ ደንብና ሥርዓት ሞርስ ኮድ፣ ሂሳብ፣ እንግሊዝኛ፣ የበረራ ጉዞ ትምህርት እና የሬዲዮ ንድፈ ሐሳብ አሠራር ሲሆን በሬዲዮ ግንኙነት ደንብ ትኩረት የሚሰጠው በ(ICAO እና IRR) ላይ ነበር። ይህም ማለት የራሱ የሆነ የሚከተለው ወታደራዊ አሠራርና ልምድ አልነበረውም። በዚህም መሠረት የነበረው የመገናኛ ግንኙነት ከአየር ኃይሉ ጣቢያዎች፣ አይሮፕላኖችና አልፎ አልፎ ከሲቪል አቪዬሽን ጋር የአየር ሁኔታዎችን ለመለዋወጥና የአውሮፕላን እንቅስቃሴዎችን ለመቀበልና ለማስተላለፍ ብቻ ነበር።

የጦር ሚኒስቴር ይባል የነበረው መሥሪያ ቤት ስያሜው ተቀይሮ የመከላከያ ሚኒስቴር ከተባለ በኋላ በስሩ የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም ጠቅላይ መምሪያ ተመሠረተ። በጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም ስር ሦስቱ የጦር ኃይሎች ማለትም የምድር ጦር፣ የአየር ኃይልና የባሕር ኃይል ተደራጁ።

በዚህም ጊዜ አዲስ የተቋቋመውን የኤታ ማዦር ሹም ጠቅላይ መምሪያ መዋቀሩን ለመዘርጋት፣ ለማደራጀትና በሚቋቋምበትም ጊዜ ለመርዳት፤ ከስዊድን መንግሥት በ1950 ዓ. ም. ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የተላኩትና በየዘርፉ በአማካሪነት የተመደቡት ከፍተኛ መኰንኖች የብዙ ጊዜ ልምድ ያካበቱ ነበሩ። እነዚህም መኰንኖች ያለገደብ አስፈላጊውን የቴክኒክና የሙያ ምክር፣ ሥልጠና እንዲሁም አሠራርና ደንብ በማውጣት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

በተዘረጋው መዋቅርና የዕዝ ሰንሰለት መሠረት በኤታ ማዦሩ ሹም ስር ሦስቱም ኃይሎች በሰላም ጊዜ ሆነ በጦርነት፤ በመገናኛ አገልግሎት ዘዴ የመገናኛ ግንኙነት እንዲኖራቸውና ማንኛውም ዓይነት መልእክት





መለዋወጥ እንዲቻል መመሪያ ደንብ እንዲቀረጽ ተደረገ። በዚያን ጊዜ ክቡር ራስ አበበ አረጋይ የመከላከያ ሚኒስትር ሲሆኑ ሌ/ጄ ነጋ ኃይለ ሥላሴ ምክትል ሚኒስትር ሆኑ። የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም ክቡር ሌ/ጄ ሙሉጌታ ቡሊ፣ ክቡር ሌ/ጄ ከበደ ገብሬ የምድር ጦር አዛዥ፣ ብ/ጄ ሊንዳል የአየር ኃይል አዛዥ፣ ሪር አድሚራል እስክንድር ደስታ የባሕር ኃይል አዛዥ ነበሩ።

በተነደፈው ፕላንና የዕዝ ሰንሰለት መሠረት የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም ሦስቱን የጦር ኃይሎች ለማዘዝና ለማስተባበር በማንኛውም ጊዜ አስተማማኝ ጥበቃ፣ ፍጥነትና ተለዋዋጭነት ያለው የመገናኛ አገልግሎት አስፈላጊነቱ ስለታመነበት፣ ከሦስቱም ኃይሎች የተውጣጡ የመገናኛ መኰንኖች ተመርጠው በኤታ ማዦር ሹም ጠቅላይ መምሪያ ሥር ሥልጠና ተሰጠ። ይኸውም ሥልጠና የተመራው ከስዊድን አማካሪዎች ውስጥ ለመገናኛ መምሪያ በተመደበው መኰንን ነበር። የተሰጠው ትምህርትና ሥልጠና ወታደራዊ የመገናኛ አገልግሎት ደንብና አሠራር ሲሆን፤ የምስጢር መልእክቶች አጻጻፍና አላላክ ዘዴን አሠራርና (በሰላምና በጦርነት ጊዜ) የሕብረት ግንኙነት መመሪያ ነበር። በወቅቱ የባሕር ኃይል በዚህ ሙያ የተላኩ መኰንኖች አልነበሩትም። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሦስቱም ኃይሎች መሠረታዊ የሕብረት መገናኛ ዶክትሪን (መመሪያ ደንብ) ተዘጋጅቶ በኤታ ማዦር ሹሙ ጽ/ቤት ትእዛዝ ተላለፈ።

ይህ የመገናኛ አሠራር መመሪያና ደንብ አሠራሩን በዝርዝር የሚያመለክት ነበረ። በኤታ ማዦር ጠቅላይ መምሪያና በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ የሬዲዮ ግንኙነት ተቋቁሞ አስቸኳይ መልዕክት ማስተላለፍና እንደ አስፈላጊነቱም የሬዲዮ ቃል ግንኙነት መለዋወጥ ተጀመረ። በጊዜውም በአዲስ አበባና በደብረዘይት መካከል በነበረው የስልክ መስመር ለመገናኘት በጣም አስቸጋሪና ጊዜ ይወስድ ስለነበረ አስቸኳይ ጉዳዮችን በሬዲዮ ግንኙነት በተሻለ ፍጥነት ማስተላለፍ ተችሏል።

የክሪፕቶግራፊክ (የምስጢር መልእክት አጻጻፍ ዘዴ) እና መሠረታዊ የመገናኛ አገልግሎት መመሪያና ደንብ ትምህርት በተሰጠበት ጊዜ ከክብር ዘበኛና ከግርማዊ ን.ነ. ልዩ ኤታ ማዦር መኰንኖች፤ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ የኮድ ክፍል ኃላፊና ከጸጥታ ጥበቃ መኰንኖች ተልከው በተለይ የምስጢር ጽሕፈት ሥራን እስከ ምሥጢር ደረጃ ያለውን ተላትፈዋል። ወታደራዊ መኰንኖች ግን እስከ ጥብቅ ምሥጢር ደረጃ ያለውን በመማርና ልምምድ በማድረግ ሦስቱም የጦር ክፍሎች ለሰላምና ለጦርነት ጊዜያት መልእክቶች የሚለዋወጡበትን

ዘዴ እንዲያዘጋጁ ሠልጥነዋል። የትምህርቱ ኮርስ ሲጠናቀቅ ክቡር ሌ/ጀ አማን አንዶም ጄኔራሉ የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር የ3ኛ መምሪያ መኰንን ተገኝተው የምስክር ወረቀት ሰጥተዋል። ጄኔራሉ ለተመራቂዎቹ መኰንኖች ንግግር ሲያደርጉ እንዲህ ማለታቸው ይታወሳል። «በመጀመሪያ የመገናኛ አገልግሎት ለአንድ የጦር ክፍል የደም ስር ነው። ይሄም ሆኖ አስተማማኝነቱና ጥበቃው ካልተሟላ ጠሩ ውጤት ሊኖረው አይችልም። የኢትዮጵያ መንግሥት በተለይ የምሥጢር ቋንቋ አገልግሎት አሠራርን ትምህርት/ሥልጠና እንዲሰጡልን ወዳጅ የተባሉትን አገሮች ማለት፤ የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይና የስዊድንን መንግሥታት እርዳታ ጠይቀን ነበር። ሁሉም ጥያቄውን ገሸሽ አድርገውት በመጨረሻ የስዊድንን መንግሥት ፈቃደኝነት አግኝተን ይኼው ዛሬ እናንተ የመጀመሪያዎቹ ሠልጣኞች ሆናችኋል። የስዊድን መንግሥት ስላደረገልን ትብብር በጣም እናመሰግናለን፤ እናንተም የገበያችሁትን ትምህርት መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች ወደፊት የሚጠቀሙበትን የአሠራር ዘዴ ደንብና መመሪያ በሕብረት እንድታዘጋጁ ይጠበቅባችኋል፤ የትምህርታችሁንም ሙያ ላልተፈቀደለት ማስተላለፍም ሆነ ማሳወቅ እንደሌለባችሁ አደራ በማለት አስጠንቅቃችኋለሁ።»

በተሰጠው መመሪያ መሠረት በጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ጠቅላይ መምሪያ ውስጥ ከምድር ጦርና ከአየር ኃይል መኰንኖች ተመድበው የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች የሚሠሩበትን የመገናኛ አገልግሎትና የምሥጢር ቋንቋ ጽሕፈት ሥራ አሠራር መመሪያና ደንብ እንዲወጣ ተደርጎ በሥራ ላይ ውሏል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአዲስ አበባ ጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ጠቅላይ መምሪያ፣ በምድር ጦርና በአየር ኃይል የግንኙነት ልምምድ ቀጥሎ እየተጠናከረ በመሄዱ በሙያው የተሠማሩት መኰንኖች ትውውቅ የተሻለ እየሆነ በመምጣቱ፤ በ1953 በታህሳስ ወር የተሞከረው መፈንቅለ መንግሥት በተካሄደበት ወቅት ሂደቱን ለመግታት አንድ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይኼውም በኤታ ማዦር ጠቅላይ መምሪያና በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ መካከል የነበረው የሬዲዮ ግንኙነት በምሥጢር በመካሄዱና የሚተላለፈውንም የሬዲዮ መልእክት የክብር ዘበኛ ጦር ጣልቃ ገብቶ ቢያዳ ምጥም ለመፍታት ባለመቻሉ እንደሆነ ይገመታል።

ስለዚህ በማንኛውም ጊዜ አስተማማኝ ጥበቃ ያለው የመገናኛ አገልግሎት፤ ቁልፍ የሆኑ ሰዎች ግንኙነት አስፈላጊነት፤ ይህን ለማሳካት ባለሙያዎቹም ይጠይቁት የነበረው ድጋፍ፤ በዚያን ወቅት "መገናኛ" ጉልህ ሚና እንዳለው በተግባር ጥሩ አስረጂ ሆኖ አልፏል። አየር ኃይል ከምድር ጦር ጋር ለሚያደርገው የሕብረት ውጊያና የአየር ድጋፍም





ለመስጠት አስተማማኝ ጥበቃና ፍጥነት ያለው የመገናኛ አገልግሎት እጅግ ወሳኝ መሆኑን አዛዦች በተግባር እንዲረዱትና የበለጠ እንዲገነዘቡት አደረጋቸው።

ከጥቂት ጊዜ በኋላም የጎረቤት አገር የሆነችው ሶማሊያ ነፃነቷን ተቀዳጅታ የሶማሌ ሪፐብሊክ መንግሥት መሠረተች። ወዲያውም በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ የፕሮፓጋንዳ ጦርነት በመጀመርና «ታላቋ ሶማሊያ» በሚል ቅዠት ኢትዮጵያውን የኦጋዴን ሶማሌዎችን ወደ ግዛቷ ለመቀላቀል እንቅስቃሴዋን ቀጠለች። አዝማሚያውም «ታላቋን ሶማሊያ» የሚለውን ህልም ለማሟላት በያለበት የጦር መሣሪያ ለማግኘት መሯሯጥ፣ ኢትዮጵያን ወደ መከላከል ጦርነት የሚያመራት መሆኑን መንግሥት በመረዳቱ በአንጻሩ ለዘመቻው የሚያስፈልገውን ለማዘጋጀት እርምጃ ተወሰደ።

በዚያን ጊዜ የአሜሪካ ወታደራዊ እርዳታ ፕሮግራም ከተጀመረ ከአም ስት ዓመት በላይ በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ይደርሳል የሚለውን ሥጋት በበቂ የመረጃ ድጋፍ በማስረዳት በየደረጃው የሚፈለገውን መሣሪያ፣ የተለያዩ የመለዋወጫ ዕቃዎችና ለጦርነት መጠባበቂያ የሚሆን ልዩ ልዩ የአይሮፕላን በምብና ጥይት በአስቸኳይ እንዲቀርብልን ጠየቀ። ሆኖም የተፈለገውን በሙሉ ለማግኘት እንደማ ይቻልና በአሜሪካኖቹም ስልት ለጦርነት መጠባበቂያና የ30 ቀን ፍጆታ ብለው የመደቡልን በመሣሪያም ሆነ በመለዋወጫ ዕቃ ከአንድ ሳምንት የጦርነት ጊዜ በላይ እንደማያስኬደን ተረዳን። ሁኔታው እጅግ አሳሳቢና የአገር ህልውናን ፈተና ላይ የሚጥል በመሆኑ ጉዳዩ ለመንግሥት ቀርቦ ሌላ ርምጃ በመውሰድ መሰናዶው ቀጠለ። በሌላ በኩል ግን ከሶቪዬት ሕብረት መንግሥት ለሶማሌ ርዳታ በገፍ ይደርስ ነበር።

የሶማሌ ሪፐብሊክ መንግሥት የፕሮፓጋንዳው ጦርነት በጣም እያየለ መጥቶ በ1956 ዓ. ም. ላይ የታወቀውን የቶጎ ውጫሌ ጦርነት ከፈተብን። በዚህ ጦርነት አየር ኃይል ቀዳሚ ዘመቻ መምሪያውን ድሬዳዋ አየር ኃይል ጣቢያ አቋቁሞ ከአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያና ከ3ኛ ክፍለ ጦር ጋር የሬዲዮ ግንኙነት አቋቁሞ ስለነበር፤ ክፍለጦሩ የሚጠይቀውን የአየር ድጋፍ ወዲያውኑ ያገኝ ነበረ። የኢትዮጵያ አየር መንገድም በዚህ ጊዜ ቁጥራቸው በዛ ያሉ የዲሲ-3 አይሮፕላኖች በማሠማራት ወታደር ወደሚያስፈልግበት አካባቢ አጓጉዟል።

አየር ኃይልም በራሱ የአየር ቅኝት ከሚያገኘው በተጨማሪ ከ3ኛ ክፍለጦር ስለጠላት እንቅስቃሴ መረጃ በቶሎ ይደርሰው ስለነበረ ለእግረኛው ጦር የአየር ድጋፍ ከመስጠት በተጨማሪ እንደአስፈላጊነቱ

በጠላት የጦር ሠፈርና በጠላት ተንቀሳቃሽ ሜካናይዝድ ጦር ላይ ከፍተኛ የማጥቃት ዘመቻ ፈጽሟል:: የሶማሌ ሪፐብሊክ መንግሥት አየር ኃይል ቢያቋቁምም የኢትዮጵያን አየር ኃይል ለመከላከል ወይም በእግረኛው ጦር ላይ ጥቃት ለማድረስ ምንም አልሞከረም:: ስለዚህም የኢትዮጵያ እግረኛ ጦር በአጭር ጊዜ የጠላትን ጦር በየወሰኑ ላይ ባደረሰበት ከፍተኛ ውድመትና ጉዳት ወዲያውኑ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት «ኢትዮጵያ ልትወረኝ ነው» በማለት ጩኸት ማሰማት ጀመረ:: ሆኖም በኢትዮጵያ በኩል የሚሰነዘረው ማጥቃት እየቀጠለ ሄዶ፤ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ረዳታችን የነበረው የአሜሪካ መንግሥት በቅድሚያ ለዘመቻ መጠባበቂያ እንደተመነልን ሳይሆን በራሳችን ግምት የመሣሪያም ሆነ የአይሮፕላን መለዋወጫ እጥረት ሳይገጥመን የጠላት ጦር ተግበስብሶ እንደመጣ እግሬ አውጭኝ በማለት መፈርጠጥ ጀመረ:: የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተኩስ አቁም ትእዛዝ ወዲያው ይቀበላል ብለው ገምተው ስለነበረና እንደአስተሳሰባቸውም ባለመሆኑ መገረም ብቻ ሳይሆን በጣም ተናድደው ነበረ::

በኢትዮጵያ በኩል እግረኛውም አየር ኃይሉም የጠላትን ጦር እያሳደደ አይቀጡ ቅጣት ከሰጠው በኋላ ከብዙ አቅጣጫ "ተኩስ አቁሙ" የሚለው ውትወታ በመብዛቱ በድል አድራጊነት የጠላትን ቅስም ከሰበርን በኋላ የተኩስ አቁሙን ትእዛዝ መንግሥት ተቀበለና ጦርነቱም በድል አድራጊነት ቆመ::

በዚህ ጦርነት የአገራችንን የአየርና የምድር ወሰን ከማስከበር ባሻገር አየር ኃይላችን ያገኘው ልምድ ወደፊት በሚጠብቀን ጦርነት ፍጹም የአየር የበላይነትና የውጊያ ብልጫ ለማግኘት እንዲሁም አየር ኃይላችንንም ሆነ የምድር ጦራችንን በተሻለ ሁኔታ ማዘጋጀት እንዳለብን በግልጽ ተማርን:: ይኸውም:-

1. በማንኛውም ጊዜ አስተማማኝ ጥበቃና ፍጥነት ያለው የመገናኛ አገልግሎት እንደሚያስፈልገን፤ <u>መገናኛ</u> ማለት በጦርነት ወቅት የኃይል ልጓም መሆኑን አስመሰከረ::

2. የተሟላ የአየር መከላከያ ዘዴ (Air Defense System)::

3. በራሳችን አቅም የራሳችን የሆነ የውጊያ መሣሪያ (አይሮፕላን) ማለትም ምን ጊዜም ማዕቀብ ወይም ተጽእኖ ሁኔታ የማይኖርበት ኃይል እንደሚያስፈልግ፤ ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች በመንግሥትም ደረጃ ስለታመነባቸው:-





1. በጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም ጠቅላይ መምሪያ፣ ዘመቻ መምሪያ ክፍል፣ አየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ፣ ሐረር ሜዳ ዘመቻ መምሪያና በ3ኛ ክፍለ ጦር ዘመቻ መምሪያ መካከል የቀጥታ የቴሌፎን መስመር (Hot Line) እንዲሁም በአየር ኃይል መ/ቤት፣ ሐረር ሜዳ ዘመቻ መምሪያ፣ ድሬዳዋ አየር ምድብ ዘመቻ መምሪያና 3ኛ ክፍለ ጦር ጠቅላይ መምሪያ ሐረር ዘመቻ መምሪያ መካከል ቀጥታ የቴሌፎን መስመር ተቋቋመ:: ይህ መስመር አስቸኳይ ዘመቻ ነክ ጉዳዮችን ለመለዋወጫ ሲሆን ለአስተዳደር፣ ለሎጂስቲክስና ለሌላ መሰል ጉዳዮች የሬዲዮ መገናኛ ከነተጠባባቂው የግንኙት መስመር ተቋቁሞ ሥራ ላይ እንዲውል ተደረገ::

2. እንግሊዝ አገር የተሠሩ የጠላትን ጦር በጥልቀት ገብቶ ለማጥቃት የሚችሉና ለሜካናይዝድ ጦር መቅሰፍት የሆኑ ካንቤራ (Canbera) የተባሉ ሁለት ጄት ቦምብ ጣይ አይሮፕላኖች እንዲገዙ በመንግሥት ተወሰነ:: በዚያን ጊዜ ወዳጃችን ሆኖ ርዳታ ይሰጠን የነበረው የአሜሪካ መንግሥት ግገርውን ለማሰረዝ ያላደረገው ከፍተኛ ሴራ አልነበረም:: ሆኖም በሁሉም ደረጃ አልተሳካለትም:: «ኢትዮጵያ ለልማት ልታውል የሚገባውን ሀብት እኛም በመከላከያውም በልማቱም እየረዳናችሁ እንዴት አሮጌ አይሮፕላን ትገዛላችሁ?» በማለትና ከባለሥልጣኖቻችን እስከ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተቃውሞ ቢያሰሙም በፍጹም ሊሳካላቸው አልቻለም:: የኢትዮጵያ ነፃነትና ሀልውና ከወታደራዊ ርዳታ ፕሮግራም በሚገኝ የጦር መሣሪያ መጠበቅ አለመቻሉን የቶጐ ውጫሌ ጦርነት የማይረሳ ትምህርት ሰጥቶን ማለፉና የተወሰደ ውም እርምጃ ወዲያው በመሆኑ የወዳጆቻችን አስተያየት የአዞ እንባ ሆኖ ቀረ::

3 የአየር መከላከያ ዘዴ:- የኢትዮጵያ ን.ነ. መንግሥት አየር ኃይል የመጀመሪያ ግዳጅ የኢትዮጵያ አየር ወሰን በማንኛውም ጊዜያት እንዳይጣስና እንዲከበር በተለይም ድንገተኛ የአየር ጥቃት በየትኛውም አቅጣጫ እንዳይደርስብን የመጠበቅ ኃላፊነት ነው:: ስለሆነም ይሄንንም በብቃት ለመወጣት የአየር መከላከያ ዘዴ ማቋቋም አስፈላጊነት በቅድሚያ በአየር ኃይል የታመነበት በመሆኑና ድርጅቱንም ለማቋቋም ከፍተኛ ወጪ ስለሚጠይቅ ለምሥራቅና ደቡባዊ ምሥራቅ አገራችን ቅድሚያ በመስጠት በአሜሪካ ወታደራዊ ርዳታ ፕሮግራም ውስጥ እንዲካተት ተጠየቀ:: ምንም እንኳን አስፈላጊነቱ የማያጠራጥርና የአየር ኃይልም የመኖርና አለመኖር ሁኔታ

ጥያቄ ውስጥ የሚከት መሆኑን አሜሪካኖች ጭምር የሚያምኑበት መሆኑ ቢታወቅም ጉዳዩን ተቀብለውና አምነው ርዳታ ፕሮግራም ውስጥ ለማስገባት ረጅም ጊዜያት ከመውሰዳቸውም በላይ እንዲሁ በእሺታ መልክ ብቻ ከዓመት ወደ ዓመት ጥያቄው እየተንከባለለ ዕቅድ ሳይኖረው ወደ አሥር ዓመታት ገደማ ወሰደ። በዚህም ጊዜያት የፊሲካል ዓመቱን (የበጀት ዘመን) ሳይከተል በመሐል ዓመት ውስጥ ኤ. ኤን. ቲ. ፒ. ኤስ. -፩ዲ (AN/TPS-ID) የተባለ ሬዳር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ዘመን የተሠራ ከአሜሪካኖች እንዲሰጥ ለአየር ኃይል ሃሳብ ቀረበ። ይህ ሬዳር የአየር ኃይልን መሠረታዊ ፍላጎት የማያሟላና ጊዜውም ያለፈበት በመሆኑ መቀበሉ ጥቅም እንደሌለው ስለታመነበት «አንቀበልም» የሚል መልስ ተሰጠ። ሆኖም ፍላጎታችንን በተሻለ የሚያሟላ እንደሚያስፈልገን በመግለጽ ጥያቄአችንን ከማስተላለፍ አልቦዘንም።

በዚህ መሐል ለአየር ኃይል ዘመቻ መምሪያ አማካሪ የሚሆኑ ከፍተኛ መኰንን ከእስራኤል አየር ኃይል ተልከው ዘመቻ መምሪያ ተመድበው ነበር። የአየር ኃይልን ችግር አወቀውት ስለነበርና ከወዳጆቻችንም ጋር የመረጃ ልውውጥ ስለሚያደርጉ በመከላከያ ሚኒስቴር በኩል በእስራኤል ኤምባሲ አማካይነት የእስራኤል መንግሥት በርዳታ ሬዳር እንደሚሰጡን ታወቀ። ከዚያም የሚሰጡን የሬዳር ዓይነት የሚገልጽ ቴክኒክ መግለጫ ጽሑፍ ደርሶን ስንመለከተው የአሜሪካ ወታደራዊ ፕሮግራም እንስጣችሁ ካለው የባሰ ሆኖ አገኘነው። አየር ኃይልም «ይህ መሣሪያ የኛን ጥያቄ አያሟላም» ብሎ መልስ ሲሰጥ «ለሥልጠና ይረዳችኋል» ቢሉንም ምንም ጥቅም እንደ ሌለው ገልጸን አስረዳን። የዚህን ሬዳር ስጦታ ላለመቀበል በመከላከያ ሚኒስቴርም በኩል ተገልጾላቸው በዚያው ቀረ።

ከዚህ ጊዜ በኋላ በአሜሪካ ወታደራዊ ፕሮግራም አማካይነት ከአሜሪካ የሬዳር ጣቢያዎች ቅየሳ የሚያደርግ ቡድን ተላከ። ይህ ቡድን የመጣው የቅየሳ ጥናት ለአየር መከላከያ ቋሚ የሬዳር ጣቢያ ጥሩና ከፍተኛ የሬዳር ሽፋን ለማግኘት የሚያስችሉ ነጥቦች ለማግኘትና ለመቀየስ ነበር። በመንግሥትም፣ በአየር ኃይልም በኩል ለአየር መከላከያ ቅድሚያ እንዲሰጠው የተፈለገው የምሥራቁ ክፍል (ዞን) ስለነበርና ለዚህም ይመቻሉ ተብለው የታሰቡት ቦታዎች በአየርም በመሬትም ቅየሳው ተደረገ። ይኸውም በአየር በሄሊኮፕተርና በዳኮታ በመብረርና የአካባቢውን የመሬት ካርታ በመመልከት ሦስት ቦታዎች ተመርጠው ቋሚ የሚሆን ምልክት ተደርጎና የአየር ፎቶግራፍ ተነስቶ ቡድኑ ማንኛ





ውንም ተፈላጊ መረጃ (Data) አሟልቶ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። በዚያን ወቅት ይዞ ያልሄደው የአየር ፎቶግራፍ ብቻ ሲሆን ይኸው ተነስቶ ተላከለት።

ከዚህ ጊዜ በኋላ በአየር ኃይል በኩል የተቀየሰውንና የፕሮግራሙን ቅደም ተከተል ዝርዝር በሚጠባበቅበት ወቅት በመከላከያ ሚኒስቴር በኩል ከዚህ ቀደም ፍላጎታችንን አያሟላም ብለን ተሟግተን አስቀረነው የተባለውን ሬዳር «ተቀበሉ» የሚል አስደንጋጭ ዜና በትእዛዝ መልክ ደረሰን። ሆኖም «መቀበል የለብንም» ብንልም የአሜሪካ ወታደራዊ ተራድኦ ፕሮግራም ሬዳሩን ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ውስጣዊ አካሉን በማሻሻል የኢት. ን. ነ. መንግሥት አየር ኃይል ግዳጁን ለመወጣት የኤሌክትሮኒክስ መገናኛውን ሁሉ አሟልተው እንደሚፈልገው አድርገው አሟልተው እንደሚያስረክቡን ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አሳምነው ማስወሰናቸው ተገለጸ። በአየር ኃይል በኩል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ማሻሻል እንደ ማይቻልና እንደማያምኑበትም ለማስረዳት ቢሞክሩ ጉዳዩ ያለቀለት በመሆኑ በትእዛዝ መልክ እንድንቀበል ተደረገ።

ከዚያም አሁንም በአሜሪካ ወታደራዊ ተራድኦ ፕሮግራም መሠረት የሚያስፈልገው የሰው ኃይልና ድጋፍ፣ እንዲሁም የመቋቋሚያ ቦታ ተወስኖ የዝግጅት ፕሮግራም ተቀየሰ። የመጀመሪያው ሬዳር በምድር ጦር መሐንዲስ ተቀይሶ ሥራው በሚያስደንቅ ሁኔታ በሦስት ወራት ውስጥ ተጠናቀቀ። ለዚህ የመንገድ ቅየሳ ፕሮጀክት ኃላፊ ሆነው የቀየሱና የመንገድ ሥራውንም እቦታው ላይ ተገኝተው ይመሩ የነበሩት ሻለቃ ጥበበ መንክር እጅግ አስደናቂ የሆነ ሥራ በአጭር ጊዜ ውስጥ በማይታመን ሁኔታ መፈጸማቸው ለጉዳዩ የነበራቸው አገራዊ አስተሳሰብ ምን ጊዜም የማይረሳ ነው። አስፈላጊው የሰው ኃይልም ተመድቦ ነባር መኰንኖችና ቴክኒሺያኖች የመኖሪያ ቤት ማዘጋጀት ስላልተቻለ ለሥልጠናው ጊዜያት በድንኳን እንዲኖሩ ተወስኖ ሌላው ማንኛውም አስፈላጊ ዕቃ ቦታው ላይ እንዲገኝ ተደረገ።

ለረጅም ዘመን ደክመን በመጨረሻም «የኢትዮጵያ አየር ኃይልን ፍላጎት ስለማያሟላ አይሠራም» ብለን ሽንጣችንን ገትረን የተሟገትንበት ሬዳር መጣ። ወዲያው ወደሚቋቋምበት ሥፍራ በአየርና በመኪና ጉዞ ተጀምሮ ያላንዳች እክል ተጠናቀቀ። በአንድ ሻምበል የሚመራ አባላት ያሉት የአሜሪካ አሠልጣኝ ቡድን በአየር ኃይል አይሮፕላን ተጓጉዞ በአካባቢው በሚገኝ ሆቴል ውስጥ እንዲቀመጡ ተደርጎ የመቋቋሙና የሥልጠናው ፕሮግራም ዝግጅት በአጭር ጊዜ ተጠናቀቀ። በመሠረቱ ኤ ኤን ቲ ፒ ኤስ-1ዲ (AN/TPS-ID) በአጭር ጊዜ ውስጥ ተንቀሳቅሶ

ከሚፈለግበት ቦታ ሲደርስ ሥራው ወዲያው እንዲጀመር ሆኖ የተሠራ በመሆኑ ሥልጠናው ወዲያው በፕሮግራም እንዲቀጥል ተደረገ:: የኢትዮጵያ አየር ኃይል ዘወትር በየቀኑ በተወሰነ ሰዓት አንድ አይሮፕላን ቲ-33 ለሥልጠናው እንዲረዳ እንዲያበር ተደረገ:: ሆኖም በየዕለቱ ከሬዳር ጣቢያው የሚደርሰው ሪፖርት ሬዳሩ አለመሥራቱን ብቻ ሆነ:: በአየር ኃይል በኩል ያለመሰልቸት ሥልጠናውም፣ በረራውም፣ ሙከራውም እስኪቻል ድረስ ቀጠለ:: በቅድሚያ እንደተጠበቀው ውጤት ከንቱ ሆነ:: የቲ-33 አይሮፕላን በሬዳሩ ስኮፕ የምትታየው ሬዳሩ አናት ላይ በምትደርስበት ጊዜያት ብቻ ነው:: የአሜሪካ ወታደራዊ ተራድኦ ፕሮግራም አማካሪዎች ለበላይ ባለሥልጣኖቻችን የኢትዮጵያ አየር ኃይልን ጥያቄ ያሟላል ብለው ያስወሰኗቸው ሬዳር በተባለው ርቀት የኢትዮጵያ አየር ኃይልን ቲ-33 አይሮፕላን መፈለግና ማግኘት ቀርቶ ግንኙነትም እያደረገ ሬዳሩ የሚያየው አናቱ ላይ (ሬዳር ጣቢያ ላይ) ከደረሰ በኋላ ነበር:: ይህም ማለት፣ የጠላትን አይሮፕላን ቢሆን ኖሮ፣ የወገን ጦር እንዳይጠቃ ማንቃትና ማስጠንቀቅ ቀርቶ እራሱም እንዳይመታ የመከላከል ዕድል አይኖረውም:: የጠላትም አይሮፕላን የሚፈልገውን ዒላማ ያላንዳች ሥጋት ደምስሶ ወደቦታው ተመልሶ መሄድ ይችላል::
የሬዳር ጥቅሙ:-

1. የኢትዮጵያ ን. ነ. መ. አየር ኃይል ከአንድ የአየር መከላከያ ድርጅት የሚጠብቀው የድጋፍ አገልግሎት፣ በቅድሚያ በማንኛውም ጊዜያት በተወሰነ ክልል ውስጥ የኢትዮጵያን የአየር ወሰን ያለፈቃድ ጥሶ የሚበርን አይሮፕላን በረጅም ርቀት መፈለግና ማግኘት፣ የጠላት መሆኑን ለይቶ ካወቀ በኋላ የጠላት መሆኑ ሲረጋገጥ ድንገተኛ ጥቃት ከማድረሱ በፊት ለአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ትእዛዝ መስጫ ክፍል ማሳወቅ፣ የወገንን ጦር ማንቃትና ማስጠንቀቅ ሲሆን፣

2. የጠላትን አይሮፕላን ለማግኘትና ለማውደም የሚነሱትን የወገን ተዋጊ አይሮፕላኖች መምራት፣ ማሳየትና የጠላትን አይሮፕላን ደምስ ሰው ወይም አባረው ወደ ሠፈር በቀላሉ እንዲመለሱ መርዳት ነው::

3. ይህን የተዘረዘረውን ግዳጅ ለማሟላት የጠላትን አይሮፕላን ከረጅም ርቀት መፈለግና ማግኘት፣ አቅጣጫውን፣ ርቀቱን፣ ከፍታውንና ፍጥነቱን በትክክል ማወቅ ያስፈልጋል::

በአሜሪካ ወታደራዊ ፕሮግራም መሠረት ለአየር ኃይል የቀረበው ሬዳር ግን ከብዙ ሙከራ በኋላ ፈጽሞ አለመሥራቱ ሲረጋገጥ፣ በኢትዮጵያ





አየር ኃይል በኩል ይህን የማይሠራ ሬዳር ለመቀበልና ለማሠራት የተደረገው ወጪና በሙከራ የባከነው የበረራ ሰዓት እንዲሁም ለሥልጠና፣ ለደሞዝና ለድጋፍ የወጣውን ጠቅላላ ወጪና በተለይም ለዝግጅት የባከነውን ጊዜና ሁኔታ በዝርዝር ለክቡር የጦር ኃይሎች ዋና ጠቅላይ ኤታ ማዦር ሹም ለሌ/ጄ አሰፋ አየነ ሪፖርት ቀረበ::

ክቡር ኤታ ማዦር ሹሙም በቦታው ላይ ተገኝተው ሁኔታውን ለመረዳት እንደሚፈልጉ ለአየር ኃይልና ለአሜሪካ ወታደራዊ ርዳታ ፕሮግራም አማካሪዎች ቡድን በጽሑፍ አስታወቁ:: በአየር ኃይል በኩል የፕሮጀክቱ ኃላፊ መኰንን በተወሰነው ቀን ቦታው ላይ እንዲገኙ ተደረገ:: ክቡር የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹምና የማግ አየር ኃይል ክፍል ኃላፊ የሁለቱ ባለሥልጣኖች የመገናኛ ኤሌክትሮኒክስ መምሪያ መኰንኖቻቸውን ይዘው በቦታው ላይ ሲደርሱ የአየር ኃይል የአየር መከላከያ ፕሮጀክት ኃላፊ መኰንን ተገኝተው ሬዳሩን ለመቀበል የተደረገውን ዝግጅት፣ ለሥራው የተመደቡትን መኰንኖችና ቴክኒሺያኖች መኖሪያ ሠፈር አንድ ባንድ ካስጎበኙ በኋላ ሬዳሩ ወደ ሚገኝበት ሥፍራ ይዘዋቸው ሄዱ:: ከዚያም ሲደርሱ የአሜሪካ የሬዳሩ አሠልጣኞች ቡድን ተጠሪ ዕቃዎችን በማመልከት ገለጻ አድርገው አሠራሩን ሊያሳዩአቸው ወደ ኦፕሬሽኑ ክፍል አስገቧቸው::

ለዚህ ሙከራ የበረራ ፕሮግራም ታቅዶ ስለነበር አይሮፕላኖች ሰዓታቸውን ጠብቀው በረሩ:: ሆኖም ሬዳሩ ሳያገኛቸውና ሳያያቸው በሬዳሩ ጣቢያ አናት ላይ እየዞሩ ተመለሱ:: ክቡር የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹምም ሬዳሩ ያለመሥራቱን ተገንዝበው ጉብኝቱ ተፈጽሞ ወደ አዲስ አበባ ከተመለሱ በኋላ በጣም በማዘንና በመቆጨት በአሜሪካ ወታደራዊ ተራድኦ ፕሮግራም የቀረበው ሬዳር ፈጽሞ የማይሠራ መሆኑን ለክቡር ያገር መከላከያ ሚኒስትር ሲያመለክቱ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ለዝግጅትና ለማሠራት የባከነው ገንዘብ ብቻ የነበረብንን ሥጋት ለመቋቋም ያለውን የመሰናዶ አጭር ጊዜ ጭምር በመሻማቱና በማባከኑ መንግሥት ሁኔታውን በቸልታ እንዳያልፈው አበክረው አሳሰቡ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ የየካቲት 1966 ዓ. ም. ንቅናቄ ተጀመረና ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጡት የነበሩት ባለሥልጣኖች ወደ ማረፊያ ቤት ተወሰዱ:: ወዲያው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት እንደ ተቋቋመ በሶማሌ ሪፐብሊክ መንግሥት በኩል የሚደረገው ወታደራዊ ዝግጅት በመረጃ በመጠናቀሩ በኢትዮጵያ ላይ የሚያስከትለው ሥጋት ከምንጊዜውም በላይ የበለጠ መሆኑ በተጨባጭ ስለተረጋገጠ፣ ሦስቱም ኃይሎች የጊዜውን ሥጋት ለመቋቋም የሚያስፈልጋቸውን ለመንግሥት እንዲያቀርቡ ተደረገ::

በኢትዮጵያ አየር ኃይል በኩል ቅድሚያ ከተሰጠው ዝርዝር ውስጥ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛን ማሻሻልና የአየር መከላከያ ድርጅትን ማቋቋም ነበረ:: በመንግሥት በኩል የጉዳዩ አስፈላጊነት ስለታመነበት «ፕሮጀክት 68» የተባለ በ1968 የሚጠናቀቅ የግዢ ፕሮግራም ዕቅድ ጸደቀ:: በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ አየር ኃይል የመጀመሪያውን የአየር መከላከያ ድርጅት ለድንገተኛ የአየር ጥቃት የተጋለጠውን ቀጠና የሚሸፍንና የሚያስፈልገውንም ዘመናዊና አስተማማኝ ጥበቃና ፍጥነት ያለው መገናኛ ለማቋቋም በቃ::

ከዚያም በ1969 ዓ. ም. የሶማሌ ሪፐብሊክ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመውረር በሞከረችበት ጊዜ ተዋጊ አይሮፕላኖቿ ድንገተኛ የአየር ጥቃት ለመሰንዘር አልቻሉም:: የኢትዮጵያ አየር ኃይል ተዋጊ አይሮፕላኖች በአየር መከላከያ ድርጅት ድጋፍ የጠላትን አይሮፕላን የኢትዮጵያን አየር ወሰን እንዳለፉ ጥቃት ከማድረሳቸው በፊት እንዲወድሙ በማድረግና ለእግረኛውም ጦር ሽፋኑና ድጋፍ በመስጠት የላቀ ውጤት በማስመዝገብ ድል ተቀዳጅተናል:: ከእንግሊዝ አገርም የተገዛው ካንቤራ የጠላትን ሜካናይዝድ ጦር በቦምብና በሮኬት ድባቅ በመምታት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል::
ከዚህ ሁሉ ሁኔታዎች አየር ኃይላችንም ሆነ መንግሥት በሚገባ የተገነዘበውና ቅድሚያ የሰጠው ጉዳይ በራስ መተማመንን ነው:: በወዳጅ አገር ርዳታማ በኩል በኢትዮጵያ የደረሰውን በታሪክም እንባበናል:: በዕድሜአችንም በገሃድ አይተናል::

በአሜሪካ ወታደራዊ ፕሮግራም ዕቅድ መሠረት ለቋሚ ሬዳር ጣቢያ ተብሉ ቦታ ለማጥናትና ቅየሳ ለማድረግ አንድ ቡድን ተልኮ ጥናት እንዳደረገና የተቀየሱት ቦታዎችም የአየር ፎቶግራፍ ተነስተው እንደ ተላኩ ቀደም ብሎ ተገልጿል:: የጥናቱ ውጤት ግን ለባለመብቱ ለኢት ዮጵያ አየር ኃይል አልተላከም::

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ አሁን እንደሚገነዘበው በወዳጆቻችን በኩል የተደ ረገው የቦታ ቅየሳ ጥናት የአየር መከላከያ እንዲቋቋም ሳይሆን ሌላ ዓላማ የነበረው መስሎ ታይቷል:: ይህን ድብቅ ዓላማ ወደፊት ጊዜ ይገልጸው ይሆናል::

ከዚህ በላይ የቀረበውን ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረቡት ኮሎኔል ሽፈራው ወርቁ እንዳርጌ የአየር ኃይሉ የመገናኛ መኮንን ከመሆናቸው ሌላ፣ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ በአጠቃላይ ለመከላከያ ሚኒስቴሩና ለጦር ኃይሎች በሚቋቋምበት ጊዜ ታላቅ ሚና ተጫውተዋል:: በተለይ በሬዳር





ጥበብ ላይ የተመሠረተ "የአየር መከላከያ ድርጅት" ለሀገር መከላከያ አስፈላጊነቱን ቀደም ሲል ንጉሠ ነገሥቱ በተገኙበት ለመከላከያ ከፍተኛ መኮንኖች ገለጻ አድርገዋል::



ኮሎኔል ሽፈራው ወርቁ

የደርግ መንግሥት እንደተቋቋመ መሪዎቹ በሚገኙበት የአየር መከላከያ ድርጅት ማቋቋም አስፈላጊነቱን ያለመሰልቸት አሳስበው፣ ወታደራዊ መንግሥት መሣሪያ እንዲገዛ አደረጉ:: መሣሪያው ከአየር ኃይል ግቢ ደርሶ ከሳጥን ሳይወጣ ኮሎኔል ሽፈራው በጡረታ ተገልለው በግል ሥራ ተሠማርተዋል::


## የ1969 የሶማሌ ጦርነት

የመከላከያ ኃይላችንን በበለጠ ለማጠናከርና ለአየር ክልላችን ተጨማሪ ዋስትና ለመስጠት አየር ኃይሉ ቀደም ብሎ በ1960 ዓ.ም ቢ-52 (ካምቤራ) የተባሉትን ከባድ ቦምብ ጣይ አይሮፕላኖች ከእንግሊዝ ሀገር በመግዛት፣ ለግዳጅ ብቁ ያደረጋቸው ሲሆን የአየር ኃይላችን በዚህ መሣሪያ መታጠቅ በአካባቢው ባሉት ጠላቶቻችን ላይ በወቅቱ የሞራል ውድቀት አስከትሏል::

በየካቲት ወር 1966 ዓ.ም የኢትዮጵያ አብዮት ከፈነዳ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ አየር ኃይሉ ራዳር እንዲኖረው ተደረገ:: ከ17 ዓመት በላይ



ኰሎኔል ሽፈራው ወርቁ



ብ/ጄኔራል ታየ ጥላሁን
የመከላከያ ሚኒስትር።




ኮሎኔል ኃይለጊዮርጊስ ኃይለማርያም
የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም።




ኮሎኔል ፈንታ በላይ
የአየር ኃይል አዛዥ።







ዝነኛው ቦንብ ጣይ አይሮፕላን ቢ-52 ካንቤራ።



በምሥራቁና ደቡብ ጦር ግንባር ከፍተኛ ሚና የተጫወተው ኤፍ 5 ኢ።

ለሚሆን ጊዜ ታድሶ የማያውቀውንና በአስጊ ሁኔታ ላይ ይገኝ የነበረውን የሐረር ሜዳ አይሮፕላን ማረፊያ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር አውጥቶ እንዲታደስና እንዲሻሻል አድርጓል። የአየር ኃይሉን የዓመት በጀት በሁለት ዓመት ዕድሜ ውስጥ ከዚያ በፊት በነበረው ላይ ከ50% በላይ አሳድገዋል። 10 ከቀድሞዎቹ የተሻሻሉ ኤፍ-5ኢ አይሮፕላኖች ግዢ ቢፈጸምም ግማሾቹ ብቻ መጥተው፤ የቀሩት ሳይመጡ አሜሪካ ባደረገችብን የጦር መሣሪያ እገዳ መሠረት ሳናገኛቸው ቀረን።

አሜሪካ ይህን የጦር መሣሪያ እገዳ ያደረገችው ኢትዮጵያ ያካሄደችውን ለውጥ በመቃወም ነበር። የኢትዮጵያን ኃይል በተለይም አየር ኃይላችንን በመሣሪያ ብቻ ሳይሆን በመለዋወጫ ዕቃ እንዲሁም አዲስ በመጡት ኤፍ–5ኢ አይሮፕላኖች ላይ በቂ ትምህርት ሳይሰጥ ለግዳጅ እንዳይበቁ ለማድረግ የተፈጸመ ሴራ መሆኑ ግልጽ ነው። ሆኖም በቴክኒክ ሙያ የዳበረና ለረጅም ዘመን ከፍተኛ የሥራ ልምድ ያለው የአየር ኃይል ሠራዊት፤ በእነዚህ አይሮፕላኖች በቂ የበረራና የቴክኒክ ትምህርት ባያገኝም፤ በራሱ ጥረት ከስድስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለዘመቻ ግዳጅ ብቁ አድርጓቸዋል። ስለሆነም የሶማሊ መንግሥት በሐምሌ ወር 1969 ዓ.ም በፈጸመው ግልጽ ወረራ በነዚህ ጥቂት አይሮፕላኖች የሶማሌን አየር ኃይል ለመደምሰስ ተችሏል።

በሚያዝያ 23 ቀን 1969 በእንግሊዝኛ የወጣውን «ኢትዮጵያን ሔራልድ» ጋዜጣ መነሻ በማድረግ በጊዜው በአሜሪካ መንግሥት ለተደረገው የጦር መሣሪያ እገዳ ኩሉኔል መስፍን በላይ የሚከተለውን ያስታውሳሉ። «በሶማሌ ጦርነት ወቅት የአሜሪካ መንግሥት የከፈልንበትን የ100,000,000 (መቶ ሚሊዮን) የአሜሪካ ዶላር የሚያወጣ አይሮፕላኖችና የጦር መሣሪያዎች ካገደ በኋላ (በወቅቱ የወጡትን አዲስ ዘመንና ሔራልድ ያጤኗል) በኤፍ-5 አይሮፕላንና ካንቤራ በታወቁ አብራሪዎቻችንና ቴክኒሽያኖቻችን የረቀቀ ችሎታ ሶማሌ ግዛት ድረስ በመግባት ጠላትን ለማንበርከክ የበቃነው ከተወሰነ በረራ በኋላ መለወጥ ያለባቸው የተወሰኑ መለወጫዎች ከችግር የተነሳ ጊዜ እየተራዘመላቸው የበረራ ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ በማድረግ ነበር።»

በዚህ በሶማሌና በአየር ኃይሉ ውጊያ ወቅት በኢትዮጵያ አየር ኃይል የታየው የአየር ለአየርና ከአየር ምድር ውጊያ ትርኢት ምናልባት ተቀርጾ ቢሆን ኖሮ የወቅቱ ዓለም ውጊያ ምሳሌ ሊሆን ይችላል ተብሎ ቢጠቀስ የተጋነነ አይሆንም። ምናልባትም ይህንኑ አባባል አይሮፕላኖቹን የሠራው ኩባንያ ሳይተርከው አይቀርም። በሶማሌ በኩል ሲሰማ እንደነበረው ፓይለቶቻቸው ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በሚግ-17/19





እና ሚግ-21 ተዋጊ ቦምብ ጣይ አይሮፕላኖች እጅግ እንደሠለጠኑ ብዙ መረጃ ከመድረሱም በላይ፣ እነሱም በመገናኛ አውታሮች ስለ ኃይላቸው ብዙ ተናግረዋል። በአንጻሩ ደግሞ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ኤፍ-5 ኤ እና ቢ የተቀበለው ቀደም ሲል ቢሆንም ኤፍ-5 ኢን በተረከበ ባጭር ጊዜ ውስጥ ነበሬ ጦርነቱ የተከፈተው። ያውም ከፊሉ ብቻ ስለደረሰ ፓይለቶቻችን በነዚህ አይሮፕላኖች ላይ ሰፋ ያለ ልምምድ ለማድረግ ጊዜ አልነበራቸውም። ሆኖም፣ የሱማሌን አየር ኃይል፣ የአየር ላይ ውጊያና ከአየር ወደ ምድር ውጊያ፣ ለመቋቋም እምብዛም አልተቸገሩም። ከናካቴው የኢትዮጵያ አየር ኃይል ፓይለቶች በኤፍ-5ኢ ተዋጊ አይሮፕላን በሱማሊያ አቅጣጫ በበረሩ ቁጥር በአንድ ጊዜ ቢያንስ ሁለት ሚግ አይሮፕላን በአየር ለአየር በረራው በሚሳይል ወይም በመትረየስ ጥለው ወደ ሥፍራቸው መመለስ፣ ዋና ተግባራቸው ሆኖ ነበር። ውሎአቸውን በድሬዳዋ አድርገው ወደ ማታ ጊዜ ለአዳር ወደ ደብረዘይት ሲመለሱ የሐረር ሜዳ የአየር ኃይል አባላት ጉንጉን አበባ አዘጋጅተው ጀብዱ ለሠሩና አይሮፕላን ለጣሉት ጀግና ፓይለቶች ሲያጠልቁላቸው ማየት የሁልጊዜ ታላቅ ትርኢትና አስደሳች ወቅት ነው።

ፓይለቶቻችን በኤፍ-5ኢ አይሮፕላን በቦምብና በመትረየስ የጠላትን ታንክ ተሽከርካሪና ሠራዊት ከአየር ወደ ምድር በሚያደርጉት ተኩስ አደባይተው በመመለስ የሚያሳዩት ጀብድ እጅግ አስደናቂ ነው። ካምቤራ ቦምብ ጣይ አይሮፕላንም ባለው ከፍተኛ የመሸከም ችሎታ በክንፎቹና በሆዱ ስር በሚይዛቸው ብዙ ልዩ ልዩ ቦምቦች የሱማሌን በርካታ የጦር መሣሪያና የሠራዊት ክምችት አውድሟል። ይህ ሁኔታ በኛ ብቻ የተተረከ ሳይሆን ጠላት ራሱ በልዩ ልዩ ወቅት መስክሮታል።

ስለ ሶማሌ ጦርነት ብ/ጄኔራል አበበ ወልደማርያም የሚከተለውን ያስታውሳሉ። *«ካራማራ ላይ በተተከለው ዘመናዊ ዳር መሪነት የኤፍ-5ኢ ተዋጊ ፓይለቶች ይፈጽሙ የነበረው የአየር ለአየር ውጊያ ትዝታ አሁን ካለፈ በኋላ ሲታወስ በዚያን ጊዜ ያንን የመሰለ ችሎታና ብቃት የቱን ያህል አስደናቂና አኩሪ እንደነበረ አሁንም የመንፈስ እርካታ ይሰጣል። በአንድ ወቅት ይህ የአየር ለአየር ውጊያ ሁኔታና ውጤት አስደስቷቸው የነበሩ የአየር ኃይል ባለሥልጣን በካራማራ ራዳር አማካይነት የአየር ለአየር ውጊያውን ዝርዝር አፈጻጸም በተጨባጭ ለመከታተል እንደሚፈልጉ ይገልጻሉ። የጣቢያው ኃላፊ ምቹ ጊዜ ፈልጎ «ሣ ላገናኞት ተዘጋጅቻለሁ፣ በሆት ላይን ይጠብቁ» ይላል።*

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በውስጥ ስልክ የእዝ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ኃላፊ ደውሉ፣ "አሁን ዝግጁ ስለሆነ ሆት ላይን ላይ ሲደውል ያንሱትና ይከታተሉታል" ይላቸዋል። ሆት ላይን ደወለ፣ ሲያዳምጡ የካራማራ

ራዳር ጣቢያ ኃላፊና የሁለት ኤፍ-5ኢ አይሮፕላኖች መሪ ፓይለት በሬዲዮ ይነጋገራሉ፣ በሆት ላይኑ ላይ ሲያዳምጧቸው "ሁለት ሚግ-21 የሱማሌ ተዋጊ አይሮፕላኖች ከናንተ ፊት ይገኛሉና በጥንቃቄ ተከታተሏቸው" ብለው የራዳር ኃላፊው ነገሩ:: ቆይቶ ፓይለቱ "አይታዩም" አሉ:: የራዳር ኃላፊው እንደገና ደገሙና "አሁን በዚህ ርቀት ብታማትር ታያቸዋለህ-አሁንስ! አየህ?" ሲሉ፣ ፓይለቱ "በቃ! በቃ! ከእንግዲህ ወዲህ ለኛ ተዋቸው" አሏቸው:: ከዚያ በኋላ የራዳሩ ኃላፊ "አሁን የኛ አይሮፕላኖች እየተጠጉ ነው በሃያ ማይል ተቀራርበዋል፣ የኛ ቀረቡ፣ የኛ ሚሳይል ተተኰሰ፣ የጠላት አይሮፕላን ተመታ፣ እየጨሰ ወረደ/ወደቀ/ፓይለቱ በፓራሹት እየወረደ ነው" አለው:: ይህንን የመሰለ የአየር ለአየር ውጊያን በራዳርና በሆት ላይን ሪሌይ መከታተል የቱን ያህል ስሜት እንደሚለውጥ ከሁኔታው ይታያል:: በዚህ አኳኋን ከተወሰኑ ቀናት ውጊያ በኋላ የሱማሌ አየር ኃይል ከአየር ላይ በሙሉ ተደምስሶ ጠፋ:: የኢትዮጵያ አየር ኃይልም አየሩን በሙሉ መቶ በመቶ መቆጣጠሩ ተረጋገጠ:: እነዚህ ኤፍ-5ኢ አይሮፕላኖች እጅግ ዘመናዊና ውስብስብ በሆኑ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ የሚሠሩና በቴክኖሎጂ ራስን ለመቻል ቢያንስ ከሦስት ዓመታት በላይ ትምህርት የሚጠይቁ ቢሆንም በራሪዎቻችንና ቴክኒሽያኖቻችን በአጭር ጊዜ ውስጥ መሠረታዊ ትምህርቶችን በማጠናቀቅ ትምህርቱንም ጦርነቱንም በአንድ ላይ በጦር ሜዳ በማድረግ በተለይ በመልሶ ማጥቃት ጦርነት ጠላትን በመደምሰስ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል:: ፓይለቶቻችን ድንበራችንን ጥሶ የገባውን የሱማሌን ጦር ከማስበርገግና ከመ ፍታትም በላይ ጠልቀው በመግባት ከፍተኛ ግዳጆችን ፈጽመው ጠላት አይቶት የማያውቀውን የአየር ላይ ትርኢት አሳይተው በመመለሳቸው ቀንደኛው ጠላት ሰይድ ባሬ እንኳን ሳይቀር "እኛ ለሰባት ዓመታት የተለማመድነውን ልንጠቀምበት አልቻልንም" በማለት በተዘዋዋሪ መንገድ ለኢትዮጵያ አየር ኃይል ያለውን ከፍተኛ አድናቆት ለመግለጽ ሞክሯል::»

በ1970 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያ አየር ኃይል እጅግ ዘመናዊ የሆኑትን ሚግ-21 እና 23 ተዋጊና ቦምብ ጣይ አይሮፕላኖች ታጠቀ:: የሶማሌ ጦር በድሬዳዋ አካባቢ ሰፍሮ ከተማዋን ለመያዝ አሰፍስፎ መምጣቱ በታወቀበት ምሽት ተጨማሪ ጦርና ስንቅ በዚያኑ ዕለት የማቅረብ አስፈላጊነቱ በማያሻማ ሁኔታ በታወቀበት ጊዜ የድሬዳዋ አይሮፕላን ማረፊያ ሜዳ መብራት ስለሌለው በኢትዮጵያ አየር መንገድ ማጓጓዙ አልታሰበም ነበረ:: ሆኖም በታህሳስ 1953 ዓ.ም ሽንጉሡ ነገሥቱ አስቸኳይ መልዕክት ለማድረስ ከአሥመራ አይሮፕላን ማረፊያ ዳርና ዳር መኪናዎችን አሰልፈው መብራታቸውን በመጠቀም በጨለማ





ዲሲ-3 አስነስተው ወደ ካርቱም ያበረሩት ካፕቴን አዳሙ መድኅኔ ነበሩ:: በዚህም ምሽት ተመሳሳይ ሃሳብ ያቀረቡት እሳቸው ሳይሆኑ አይቀሩም:: የድሬዳዋ ጣቢያ አዛዥ በከተማው ውስጥ የሚገኙ ጥቂት መኪናዎች አሰባስቦ በድሬዳዋ ማረፊያ ግራና ቀኝ ተሰልፈው መብራታቸውን እንዲያበሩ ተደርጎ ካፕቴን አዳሙ መድኅኔና ካፕቴን እፌወርቅ ወርቁ በዚያኑ ሌሊት የተፈለገውን ኃይል በማመላለስ ግዳጃቸውን ተወጥተዋል:: አየር መንገዱ «ሁለተኛው አየር ኃይል» ይባል የነበረው ይህን በመሳሰሉት ግዳጆች ነበረ::

በዚህን ጊዜ አየር ኃይሉ የነበረው የሰው ኃይል፣

| | | |
|---|---|---|
| መኰንኖች | 366 | |
| ባለሌላ ማዕረጎች | 58 | |
| ቴክኒሺያኖች | 1,456 | |
| አየር ፖሊስ | 633 | |
| ሲቪል | 820 | |
| ጠቅላላ ድምር | 3,333 | ነበሩ:: |



ኮ/ል መስፍን በላይ



ኮ/ል መስፍን በላይ

## አየር ኃይልና አየር መንገድ

የኢትዮጵያ አየር ኃይል አዛዥ መኰንኖች የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቦርድ አባል መሆን የጀመሩት ስዊድን ለአየር ኃይል አዛዥነት ጄኔራሎች መላክ በጀመረበት ጊዜ ነው። በኤክስፐርት ደረጃ በቴክኒክ ነክ ጉዳዮች በምክር የበላይ ቦርዱን እንደሚረዱ በመታወቁ የአየር ኃይል አዛዦች አባልነት እንደ ቋሚ የሥራ ዘርፍ ነበረ። ጄኔራል አሰፋ አየነ በአየር ኃይል አዛዥነታቸው ይዘውት የነበረውን የቦርድ አባልነት ወደ መከላከያ ሚኒስቴር ተሹመው ሲሄዱ በነበሩበትም ከፍተኛ ደረጃ የአየር መንገድ የቦርድ አባልነቱን አልቀቁም።

በስዊድኖች የበላይነት በሚካሄደው አየር ኃይልና አሜሪካኖች በሚመሩት አየር መንገድ መካከል ከተቋቋሙበት ከ1946/47 ዓ.ም እስከ 1951 ዓ.ም ጉልህ ሆኖ የሚታይ ትብብር አልነበረም። ሆኖም አየር ኃይል ተቀጥረው ይሠሩ የነበሩ የቢሮ ሠራተኞችና በዛ ያሉ ቴክኒሺያኖች በየጊዜው በግል እያመለከቱ አየር መንገድ ተቀጥረዋል። ከ1951 ጀምሮ የአየር ኃይል ፓይለቶች ወደ አየር መንገድ በመላክ ከውጭ ይመጡ የነበሩትን ፓይለቶች ደረጃ በደረጃ ለማስቀረት ተችሏል። የአየር መንገዱን አመራር ኢትዮጵያውያን ከአሜሪካኖች ከተረከቡ ጊዜ ጀምሮ በተከታታይ ለሦስት ጊዜ በዋና ሥራ አስኪያጅነት የመሩት የቀድሞ የአየር ኃይል መኰንኖች ናቸው።

የአየር ኃይል ቴክኒክ ክፍል ቀደም ሲል የነበሩትን የቢ-17 ሞተሮች አር-1830 የማ ደስ ድርጅትና ችሎታ አካብቶ ስለነበረ አየር መንገዱ የዲሲ-3 ሞተሮች ወደ ውጭ ሀገር ከመላክ ተገላግሎ አየር ኃይል በማደሱ ብዙ የውጭ ምንዛሪ አድኗል። ወደኋላ ጊዜ የራሱን የሞተር ማደሻ አስመጥቷል። አየር መንገዱ የራሱን የበረራ ትምህርት ቤት ካቋቋመም በኋላ በአዛዥነትና በአስተማሪነት ያሰማራው ከአየር ኃይሉ በዝውውርና በቅጥር የተገኙ ፓይለቶችና የቴክኒክ ባለሙያዎች ነው።





# ክፍል 2

# የኢትዮጵያ አየር መንገድ